በእርግጥ እግዚአብሔር እስራኤልን እንደገና ያስባል፤ በአሁኑ ጊዜም ለዚህ ማረጋገጫ የሚሆኑ በርካታ ምልክቶች እየታዩ ነው። ከዚህ በኋላ ያሉት ዘመናትም «እግዚአብሔር ለሕዝቡ የገባውን ተስፋ በሙላት የሚፈጽምባቸው ናቸው» ለማለት የሚያስችሉ አያሌ ማስረጃዎች መጥቀስ ይቻላል። የዚህ መጽሐፍ ቀጣይ ክፍሎችም ስለዚሁ ነገር በትኩረት የሚዳሰስባቸው ናቸው።

ለእስራኤል ሰላም ይሁን!

ሠዳስተኛው ክፍል

የትላንትና ወደፊት የሚሆነው

የትላንትና የወደፊት አበይት ክንውኖች!

ማውጫ	ገጽ
መግቢያ	186
ምዕራፍ ፲፯	
አሁን ያለው	188
ሴቲቱ የመጀመሪያው ምልክት?	192
ቀዩ ዘንዶ	197
ወንዱ ልጅ	199
የሴቲቱ ሽሽት	201
መቼ ይሆናል?	202
ምዕራፍ ፲፰	
መነጠቅና የጊታ መምጣት	204
መነጠቅ፣ ድንገት	213
ከመነጠቅ የሚቀሩ አነማናቸው?	216
የክርስቶስ የፍርድ ወንበር	218
የአማኝ የአምልኮ ሥርዓት	221
የአማኝ ሕይወትና ሥራ	223
የአማኝ ንግግር	224
ጽኑ መሠረት	226
አክሊሎችና ሽልማቶች	228
የደስታና የድል አክሊል	231
የማይጠፋ አክሊል	233
የክብር አክሊል	235
የሕይወት አክሊል	237
የጽድቅ አክሊል	239
መነጠቅና መሰብሰብ	242
የሰይጣን ወደ ምድር መጣል	249

ማውጫ	ገጽ
ምዕራፍ ፲፱	
ታላቁ መከራ	256
ከታላቁ መከራ በፊት ያለ የመከራ ጊዜ	257
ሐሰተኛ ሃይማኖት፣ መሲሆችና ነብያት	259
ጦርነትና የጦርነት ወሬ	262
ረሀብና የምድር መናወጥ	266
የወንጌል በዓለም ዙሪያ መሰበክ	269
መዳናችሁ ወደ አናንተ እጅግ ቀርቧል	273
የታላቁ መከራ ዐበይት ምልክቶች	277
የታላቁ መከራ አሰቃቂነት	279
ሁለቱ ምስክሮች	289
የቃል ኪዳኑ ታቦት	279
ሰባቱ ምልክቶች	294
ሰባቱ የቁጣ ጽዋዎች	295
ምዕራፍ ፳	
አውሬዎቹ	297
ከባሕር የሚወጣው አውሬ	298
ዘንዶውና አውሬው	303
ከምድር የሚወጣው አውሬ	311
666	314
ቺፕ አስደርግ	320
ምዕራፍ ፳፩	
ታላቂቱ ባቢሎን	324
ባቢሎን ማን ትሆን?	328

መግቢያ

አንግዲህ ያየኸውን፣ አሁን ያለውን፣ ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን ጻፍ[1]

በዚህ አራተኛ መጽሐፍ፣ በዮሐንስ ራእይ ከተነገሩ ትንቢቶችና መልዕክቶች በመነሣት፣ አሁን ስላለውና ወደፊት እንደሚሆን ስለ ተነገረው ነገር በትኩረት እንመረምራለን። የዮሐንስ ራእይ ከትንቢተ ዳንኤል ጋር ያለው ትስስር እጅግ በመሆኑ፣ በሮኛው መጽሐፍ ያነሣናቸው አንዳንድ ጭብጦች በዚህኛው መጽሐፍ የበለጠ ግልጥ የሚሆኑልን ይመስለኛል። ይኼ ፬ኛው መጽሐፍ የራእይን መጽሐፍ መሠረት በማድረግ የወደፊቱ አበይት ተስፋዎች የሚዳሰሱበት ነው።

የዮሐንስ ራእይ በአዲስ ኪዳን የተጻፈ ብቸኛው የትንቢት መጽሐፍ ሲሆን፣ በአጻጻፍ ዘይቤው ከትንቢተ ዳንኤልና ከትንቢተ ሕዝቅኤል መጻሕፍት ጋር እጅግ የሚመሳሰል ነው። ሆኖም አያሌ ክርስቲያኖች ለመረዳት አስቸጋሪ መጽሐፍ አድርገው ስለሚቆጥሩት፣ ጠለቅ ብለው ሊያጠኑት ብዙም ሲደፍሩ አይታይም። በእርግጥም እስከ ዛሬ ሁለት መቶ ዓመት ድረስ የነገረ መለኮት ተማሪዎች እንኳ ስለመጽሐፉ ጥልቅ ግንዛቤ ያልነበራቸው ከመሆኑ በላይ ስለምን እንደሚያወራ ለመረዳት ይቸገሩ እንደነበር ይነገራል። በአንጻሩ ከዛሬ ሁለት መቶ ዓመታት ወዲህ ባሉት ጊዜአት መጽሐፉ ስላዘለው ጥብቅ ሚስጥር ለመረዳት፣ ከሌላው ጊዜ ይልቅ እግዚአብሔር ለአገልጋዮቹ የላቀ መገለጥ እየሰጣቸው እንደ ሆነ ይታያል። ያም ቢሆን የአንዳንድ ትርጉሞች መለያየትና አንዱ ከሌላው ጋር ፈጽሞ መቃረኑ እስከ አሁን ድረስ ስለመጽሐፉ ያለውን መረዳት ውስብስብ እንዳደረገው መካድ አይቻልም።

ምንም እንኳ የራዕይ መጽሐፍ ለትርጓሜ አስቸጋሪ የሆነ መስሎ ይታይ እንጂ፣ መሠረታዊው ቁልፍ ከተገኘ ለመረዳት ያን ያህል አደናጋሪ ያልሆነ መጽሐፍ እንደ ሆነ ይሰማኛል። በበኩሌ በቅንነት ለሚፈልጉት ሰዎች እግዚአብሔር ራሱን የሚደብቅበት ምክንያት ያለ

[1] ራዕ1:19።

አይመስለኝም። መጽሐፉ አስቸጋሪ መስሎ እንዲታይ የሆነበት ምክንያት ግን የአጻጻፍ ዘይቤው «አቡቀለምሲሳዊ» በመሆኑ ሊሆን ይችላል። ሆኖም ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኚዎች እንደሚያምኑት የራእይን መጽሐፍ በሚገባ ለመረዳት፣ በመጽሐፉ ውስጥ ያለውን ቁልፍ ቃል መረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው። ይኼው ቁልፍ ቃል በመጽሐፉ የመጀመሪያ ምዕራፍ የሚገኝ ሲሆን፣ «አንግዲህ ያየኸውን፣ አሁን ያለውን፣ ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን ጻፍ» የሚለው ነው።

በወቅቱ ዮሐንስ «ያየኸው» የተባለው፣ በምዕራፍ አንድ ላይ የተጻፈውና የኢየሱስ ክርስቶስን መለኮታዊ ክብርና ልዕልና የተመለከተበት ክፍል ሲሆን «አሁን ያለው» የተባለው ደግሞ ከምዕራፍ ሁለትና ሦስት ላይ የተጠቀሱትን አብያተ ክርስቲያናት የሚመለከት ነው፤ «ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን» የተባለው ደግሞ ከምዕራፍ አራት እስከ ፍጻሜው ያለውን ሲሆን፣ የሚያወራው ሰባኛው ሱባኤ ከገባ በኋላ ባሉት ሰባት ዓመታት ውስጥ ስለሚከናወኑ የተለያዩ ድርጊቶችና ከዚያ በኋላ በዓለም ላይ ስለሚሆን አዲስ ሥርዓት ነው።

ምዕራፍ ፲፯

[illegible]

ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ96 ዓ.ም አካባቢ ዮሐንስ፣ ራዕይውን ከጌታ ኢየሱስ ሲቀበል በወንጌል ምክንያት ፍጥሞ ወደምትባል ደሴት በግዞት ተወስዶ ታስሮ ነበር። በወቅቱ ከመጀመሪያዎቹ የጌታ አስራ ሁለት ሐዋርያት መኻል በሕይወት የተረፈው እርሱ ብቻ እንደሆነ ይነገራል። ታዲያ በዚያ አስቸጋሪ ስፍራ ሳለ ኢየሱስን አስቀድሞ ከሚያውቀው በተለየ ክብር በራእይ ተመለከተው። ደግሞም ነብዩ ዳንኤል ታላቅ ራእይ በተገለጠለት ጊዜ ራሱን እንደሳተው ዮሐንስም ራሱን ከመሳቱም በላይ እንደ ሞተ ሰው ሆኖ ነበር። ጌታ ግን በብዙ ካበረታው በኋላ ያየውን በጠቅላላ በጊዜው «ታናሹ ኢስያ» ተብሎ በሚታወቀውና የአሁኗ ቱርክ በምትገኝበት ስፍራ ለነበሩት ሰባት አብያተ ክርስቲያናት ጽፎ እንዲልክ አዘዘው።

ዮሐንስ፣ በፍጥሞ ደሴት ሆኖ ራዕዩን ባየበት ዘመን፣ በታናሹ ኢስያ ይገኙ የነበሩት ሰባት አብያተ ክርስቲያናት፣ ከአሕዛብ ወገን ወደ ክርስትና የመጡ ሲሆኑ፣ እያንዳንዳቸው የተለያየ መንፈሳዊ አቋም እንደነበራቸው ይታያል። ጌታ ኢየሱስም ለእያንዳንዳቸው በላከላቸው መልዕክት ጥንካሬአቸውን ሲያበረታታ፣ ድካማቸውን ገስጿል፤ ከስህተታቸው በንስሃ የሚመለሱበትን መንገድ ጠቁሞ፣ የማይመለሱ ከሆነ የሚጠብቃቸውን ቅጣት አመላክቷቸዋል፤ በመጨረሻም ለድል ነሺዎች ብቻ የተዘጋጀውን ተስፋና ሽልማት አሳይቷቸዋል። ሆኖም ለእነዚህ ሰባት አብያተ ክርስቲያናት የተላከው መልዕክት በወቅቱ በታናሹ ኢስያ ለነበሩ አማኞች ብቻ ሳይሆን፣ ጆሮ ያለው ሁሉ እንዲሰማው ተደርጎ የተነገረ ነው።[2] ደግሞም የትንቢቱን ቃል የሚሰማ፣ የሚያነብና የተጻፈውን የሚጠብቅ፣ ሰው እጅግ የተባረከ

[2] ራእ፤3። ዘመኑ ቀርቦአል፤ እንግዲህ ይህን የትንቢት ቃል የሚያነብ ብፁዕ ነው፤ የሚሰሙትና የተጻፈውንም የሚጠብቁ ብፁዓን ናቸው።

እንደሚሆን ተገልጧል። አንዳንድ የራእይን መጽሐፍ በጥልቀት የመረመሩ ሰዎችም፣ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የተጻፉት መልዕክቶች ከቤተ ክርስቲያን ምስረታ እስከ ታላቁ መከራ ያሉትን ዘመናት ገልጠው የሚያሳዩ ትንቢታዊ ተምሳሌቶች ናቸው፣ በማለት እንዲህ ያሉበትን ምክንያት በማስረጃ አስደግፈው ያቀርባሉ።[3]

እንደነዚህ ሰዎች አሳብ ከሆነ፣ ለምሳሌ ኤፌሶን፣ ከቤተ ክርስቲያን ምስረታ እስከ 100 ዓ.ም የነበረችውንና የቀድሞ ፍቅሯን የጣለችውን የሐዋርያት ዘመን ቤተ ክርስቲያን ስታመለክት፣ ሰምርኔስ ደግሞ ከ100 ዓ.ም እስከ 312 ዓ.ም ድረስ በታላቅ ስደትና መከራ ውስጥ ያለፈችው ቤተ ክርስቲያን ምን ትመስል እንደነበር ትጠቁማለች፣ ማለት ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ያለፉት ዘመናት ቤተ ክርስቲያን ሁለንተናዊ ጥንካሬና ድካም ከዚህ የጊዜ አተረጓጎም አንጻር ሲቃኝ አሳማኝነቱ ሚዛን የሚደፋ ይመስላል። ለምሳሌ ለጴርጋሞን የተጻፈው መልዕክት ከ312 እስከ 606 ዓ.ም የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ሲሆን፣ ይህም ዘመን ቤተ ክርስቲያን ከዚህ ምድር መንግሥታት ጋር ጋብቻ የፈጸመችበት፣ እውነት ተገፍታ ወደ ውጪ የተጣለችበት ዘመን እንደነበር የሚታወቅ ነው። በዚያ ዘመን የጀመረው የቤተ ክርስቲያን ድንዛዜም ዛሬ በዓለም ላይ ታላቅ ሆኖ ለሚታይ ሃይማኖት መፈጠርና መስፋፋት ያደረገው አስተዋጽኦ ቀላል አይደለም።

ከ606 እስከ 1520 ያለው ዘመን ደግሞ «ዘመነ ትያጥሮን» በመባል ይጠራል። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ዘመኑ የጨለማው ዘመን እንደሆነ ይታሰባል። በእነዚያ ዓመታት ብዙ እውነተኛ ክርስቲያኖች በሐሰተኛ «ክርስቲያኖች» ተጨፍጭፈዋል፣ በዚያ ላይ እስልምና በብዙ አገሮች ለመስፋፋት ችሎ፣ የክርስትና ዋና ተቀናቃኝ የመሆን አቅም ያገኘው በዚሁ ዘመን ነው። ታዲያ በጊዜው ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት በነበሩባቸው ስፍራዎች የነበሩ ሕዝቦችን ጨምሮ ሰሜን አፍሪካ፣

[3] REVELATION TEE by Mina Moen and Tim Fellw, 1995

መኻከለኛው ምሥራቅ፣ ከአውሮፓ የተወሰነው ክፍል የነበሩ በርካታ አገሮች እስልምናን በወረራና በኃይል ለመቀበል ተገደዋል፤ ቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም ተማርካ፣ ቀድሞ ቤተ መቅደሱ በነበረበት አንጻር አወዛጋቢው መስኪድ የተሠራው በተጠቀሰው ዘመን ውስጥ ነው። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በእውነተኛ ክርስቲያኖችና በአይሁዳውያን ላይ አሰቃቂ ጭፍጨፋም የፈጸመችው በዚሁ ዘመን ነው። በአጭሩ በራእይ መጽሐፍ ላይ እንደተመለከተው፣ ዘመኑ የኤልዛቤልና የኤልዛቤላውያን ነበር ማለት ይቻላል።

ከ1520 እስከ 1750 ያለው ጊዜ፣ የሰርዴስ ዘመን በመባል ይጠራል። ዘመኑ ከቤተ ክርስቲያን አንጻር ሲታይ፣ ሕያው እንደሆነች የሚገልጥ ስም ያላት፣ ግን በሥራዋ የሞተችበት ዘመን እንደሆነ እንገነዘባለን። ያም ሆኖ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንዳንድ ትሩፋኖች የነበሩበት ዘመን ነበር። እነዚህም ትሩፋን፣ የክርስቶስን እውነተኛ ወንጌል በአስደናቂ ሁኔታ መግለጥ የቻሉ ናቸው። ለአብነት ያህል በዚያ ጊዜ በአውሮፓ የተቀጣጠለውን የተሃድሶ እንቅስቃሴ በዋቢነት ይጠቀሳል። ሆኖም የተሃድሶው እንቅስቃሴም ቢሆን፣ በብዙ ችግሮች የተተበተበና በቀጣይነት ሌላ የተሃድሶ ሥራ ያስፈለገው እንደነበር እንረዳለን። ዘመኑም «ሕያው እንደ መሆንህ ስም አለህ፣ ነገር ግን ሞተህማል» የሚለውንና ለሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን መሪ የመጣለትን ቃል የሚያስታውስ ነው።

ከ1750 እስከ ንጥቀት ያሉት ዘመናት ለፍልድልፊያ ቤተ ክርስቲያን ዘመንነት ተምሳሌት እንዲሆኑ ሲሰጡ፣ ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ ታላቁ መከራ ድረስ ያሉት ዓመታት ለሎዶቅያ ይቀሩላታል። ከራእይ አንጻር ዘመናትን እንደሚተነትኑ ሰዎች እምነት፣ ከ19ኛው እስከ ንጥቀት ዘመን ድረስ ያለው ዘመን «የፍልድልፊያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን» በመባል ነው የሚገለጠው። በመሆኑም ያለንበት ዘመን የፍልድልፊያና የሎዶቅያ ዘመን በአንድ ላይ ተደባልቀው፣ እየተጋፉ የሚኖሩበት ዘመን ነው ማለት ይቻላል። ይኼ ማለት፣ ስለራሷ ባላት የተጋነነ ግምት ተወጥራ፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ከትጥር ጊቢዋና ከአውደ ምህረቷ አስወጥታ፣ ራሷ ነግሣ የምትታየው

ሎዶቂያ ኃይሏ ታናሽ ከሆነችውና ለሥራ ጥቂት በሮች ከተከፈቱላት ፍልድልፊያ ጋር አብራ የምትጓዝበት ዘመን ነው፣ ማለት ነው።

የቱንም ያህል የእነዚህን ሰዎች አተረጓጎም ለመቀበል አስቸጋሪ ቢሆን እንኳ፣ ባለፈው ዘመንም ሆነ፣ አሁን በምድር ላይ ባለችው ቤተ ክርስቲያን ያለው እውነት ከሚሉት ጋር እጅግ ተመሳሳይ እንደ ሆነ መካድ ግን አይቻልም። በመሆኑም በራእይ መጽሐፍ ተመርኩዘው ዘመናትን እንደሚተነትኑ ሰዎች ትንታኔ ያለንበት ዘመን «አሁን ያለው» የተባለው ሲሆን፣ በራእይ መጽሐፍ ምዕራፍ ሁለትና ሦስት ላይ ምን እንደሚመስል ታውቋል።

የራእይው ሦስተኛ ክፍል የሆነውና «ከዚህ በኋላ ሲሆን ያሰው» ተብሎ በዮሐንስ የተጠቀሰው፣ ማለትም ከምዕራፍ አራት እስከ ምዕራፍ ሃያ ሁለት ያለው ክፍልም ሰባኛው ሱባኤ ከገባ በኋላና ከዚያ ቀጥሎ በዓለም ላይ ስለሚሆኑ ነገሮች የሚናገር ነው። በዚሁ መሠረት 4ኛው ምዕራፍ፣ በዙፋኑ ስለተቀመጠው ጌታ ሲናገር፣ 5ኛው ምዕራፍ፣ ደግሞ ስለታተመው መጽሐፍና ስለታረደው በግ ይተርካል፤ ከምዕራፍ 6 እስከ ምዕራፍ 19 ያሉት ምዕራፎች ስለሰባቱ ማህተሞች፣ ስለሰባቱ መለከቶች፣ ስለሰባቱ ምልክቶች፣ ስለሰባቱ ጽዋዎች፣ ስለሰባቱ ፍርዶችና ስለአርማጌዶን ጦርነት ትንታኔ የሚሰጡ ናቸው። ከዚያም ከምዕራፍ 20፣ እስከ ምዕራፍ 22፣ ስለ ሺ ዓመቱ መንግሥት፣ የሰይጣን ሽንፈትና መታሰር፣ ስለነጩ ዙፋን ፍርድ፣ እንዲሁም ስለአዲሲቱ ሰማይና ምድር ይተርካል። ከዚህ በተጨማሪ የራዕይ መጽሐፍ፣ በየመኻሉ ጣልቃ የገቡ የሚመስሉ አንዳንድ አሳቦች አካቶ ይዟል።

ሴቲቱ፣
የመጀመሪያው ምልክት

[4]

በራዕዩው እኩሌታ ዮሐንስ፣ ታላቅና አስደናቂ ምልክት በሰማይ ተመለከተ፣ ምንም እንኳ ይህ ምልክት ከሌሎች ስድስት ምልክቶች ጋር የሚቆጠር ቢሆንም፣ በአስደናቂነቱ ከሁሉም የላቀ ስፍራ ያለው ነው። ዮሐንስ ፀሐይን የለበሰች፣ ጨረቃንም ከእግሯ በታች ያደረገች እንዲሁም አስራ ሁለት ኮከቦችን በራሷ ላይ የደፋች አንዲት ሴት አየ፣ ሴቲቱ ነፍሰ ጡር ስትሆን፣ ልትወልድ ተጨንቃ ትጮህ ነበር። ጥቂት ቆይቶ ሕዝቦችን ሁሉ በብረት በትር የሚገዛ ወንድ ልጅ ወለደች፣ ልጁ ግን ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተወሰደ።

«ይህቺ ሴት ማናት?» ለሚለው ጥያቄ ብዙ ሰዎች የራሳቸውን ግምትና መላ ምት ሲያቀርቡ ኖረዋል። በዚሁ መሠረት አንዳንድ ሰዎች ሴቲቱ «ቅድስት ማርያም ናት» ይላሉ። እንዴት ሆኖ? ሲባሉ ጌታ ኢየሱስን መውለዷንና ከእርሱም ጋር ወደ ግብፅ ያደረገችውን ስደት ይጠቅሳሉ። በሴቲቱ ራስ ላይ ያለው ኮከብ፣ ፀሐይን ተጎናጽፋ ጨረቃንም ረግጣ መቆሟ፣ ለቅድስት ማርያም ብፅዕናና ክብር የሚመጥን ገለጣ እንደሆነም ያስባሉ። ልጁ ከተነጠቀ በኋላ እንደ ተሰደደች የሚያወሳውን የራእይውን ክፍል ሲያስረዱ *«በወቅቱ፣ ልጇ በአካል ወደ ግብፅ ቢሰደድም፣ በመንፈስ ግን ወደ ሰማይ ተነጥቆ ነበር»* በማለት ይከራከራሉ። በሌላም በኩል የሴቲቱ ስደት፣ ማርያም ከዚህ በፊትም ሆነ አሁን *«ለእርሷ ከማያምኑ ወይም ከፀረ ማርያሞች ወይም ከ«መናፍቃን» ወገን የደረሰባትንና እየደረሰባት ያለውን <u>ስደት</u> ለመግለጥ ወይም ለማጋለጥ የተነገረ ነው»* ይላሉ። [5]

[4] የሐንስ ራእይ ምዕራፍ 12።

[5] ዓመደ ሃይማኖት ከብርሃኑ ገበና።1985። ገጽ 103። አንባቢህ ዲያቢሉስ በአመቤታችን ተቀጥቶ "የአግዚአብሔርን ትዕዛዛት የሚጠብቁትን የኢየሱስም ምስክር የሆኑትን ከአመቤታችን ከዘርዋ የሆኑትን ማለት በአማላጅነትዋ የሚተማመኑትን ሲዋጋ ሄደ ከባሕር አሸዋ ሳይ ቆመ ማለት በመናፍቃን ልቦናና አንደበት ሳይ ቆመ፣ የአመቤታችንን ልጆች ሲቃወም።

ዳሩ ግን እንዲህ የሚያምኑና የሚያስተምሩ ሰዎች ያላስተዋሏቸው ወይም ሆን ብለው ወደ ጎን ያሏቸው አንዳንድ ክፍተቶች ይታያሉ። እንዲያውም ከእነዚህ ሰዎች ብዙዎቹ በክርስቶስ «አንድ ባህርይነት» የሚያምኑ ሆነው ሳለ፣ ኢየሱስ በምድር በነበረበት ዘመን *«ይሄን ያደረገው በሥጋው፣ ይሄን ያደረገው ደግሞ በመንፈሱ ወይም በአምላክነቱ ነበር»* ማለታቸው ስለክርስቶስ «በአንድ አካል ሁለት ባሕርይ» ብለው የሚያምኑ ያስመስላቸዋል። በሌላም በኩል *«ማርያምን አሳደጿት»* እየተባሉ የሚከሰሱት ሰዎች፣ እንዲህ ለመባል ሰበብ የሆናቸው «የማርያምን ምልጃ» ያለመቀበላቸው ብቻ ከሆነ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ትምህርት ይበልጥ የሚጻረር ይሆናል።

ሌሎች ደግሞ ሴቲቱ «ቤተ ክርስቲያን ናት» ብለው ያምናሉ። አስራ ሁለቱ ከዋክብት፣ አስራ ሁለቱ ሐዋርያት ናቸው ብለው ሲያስተምሩ የሴቲቱ ውበትና ስደትም ለቤተ ክርስቲያን ማንነት የተገባ እንደ ሆነ ያስባሉ። አንዳንዶቹም «ሴቲቱ የወለደችው ልጅ፣ ክርስቶስ ነው» በሚለው አይስማሙም። እኔ ግን ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ዕርገት በኋላ፣ መንፈስ ቅዱስ የወረደ ዕለት እንደተመሠረተች እንደማመኔ እነዚህ ሰዎች የሚያቀርቡት መከራከሪያ ያን ያህል አሳማኝ ሆኖ አላገኘሁትም። እንዲያም ሆኖ ከፊተኞቹ ተርጓሚዎች ይልቅ እነዚህ ቢያንስ ምክንያታዊ መስለው ይታዩኛል።

ሴቲቱን በተመለከተ ከሚነገሩ ሁሉ «ሴቲቱ እስራኤል ናት» የሚለው ትርጉም፣ በአሁኑ ጊዜ በብዙዎች ዘንድ እምነት ያገኘ ሆኗል። ከዚህ ቀደም የእስራኤልን የትውልድ ሐረግ ስንከተል እንዳገኘነው፣ ዮሴፍ የተባለው የያዕቆብ ልጅ፣ በህልሙ ፀሐይና ጨረቃን ጨምሮ አስራ አንድ ኮከቦች ሲሰግዱለት ተመልክቶ ነበር። በወቅቱ ዮሴፍ ያለመው ህልም ስለእናቱ፣ አባቱና ወንድሞቹ እንደሚያወራ ግልጥ ነበር። ወንድሞቹም የዚያን ያህል ጠልተውት ለእስማኤላውያን እንዲሸጡት ምክንያት የሆናቸውም ይኸው ህልሙ ነበር። ምንም እንኳ ዮሴፍ፣ በህልሙ ያየው አስራ አንድ ከዋክብት ብቻ ቢሆንም፣ እርሱ ራሱ ተጨምሮ ሲቆጠር አስራ ሁለት እንደሚሆኑ ለማስተዋል ግን ከባድ አይደለም። እነዚህ የዮሴፍ ልጆች ደግሞ የእስራኤል ነገድ መገኛ

በመሆናቸው ሀልሙ የሚናገረውን ለመረዳት ቀላል ነው። ስለዚህም ከብዙ ዘመናት በኋላ ዮሐንስ በሰማይ ላይ ያያት ሴት ተምሳሌትነቷ ለእስራኤል ስለመሆኑ ከዚህ የተሻለ ማስረጃ ማቅረብ የሚቻል አይመስልም። ልጇም፣ ከዘመናት በፊት ከእስራኤል የተገኘው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ እርግጥ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከእስራኤላዊቷ ብጽዕት ድንግል ማርያም መወለዱና እስራኤልም እርሱን ከመውለዷ በፊት፣ ለአያሌ ዓመታት በጽኑ ምጥ ተይዛ እንደነበር አያከራክርም። ለነገሩ እስራኤል በምድር ከተከሰተች አንሥቶ ጭንቀትና ጩኸት መች ተለይቷት ያውቃል? በዚያ ሁሉ ዘመን ግን ከጭንቀት የሚገላግላት ወንድ ልጅ እንደሚሰጣት ወይም እንደሚወለድላት ትንቢት ነበራት። ያም ልጅ አለቅነት በጫንቃው ላይ የሆነ፣ ስሙም ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የሰላም አለቃ ተብሎ የተጠራ ነው።

በሌላም በኩል እስራኤል እንዲህ ባለ ሁኔታ ከመገለጥዋ በፊት ባለው የዮሐንስ ራእይ 11ኛ ምዕራፍ የቃል ኪዳኑ ታቦት በሰማይ መታየቱ ሁለቱ ጉዳዮች የተቆራኘ ታሪክ እንዳላቸው የሚጠቁም ይመስላል። እንደሚታወቀው እስራኤላውያን የቃል ኪዳኑን ታቦት ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኙት፣ እግዚአብሔር አምላክ በባርነት ከሚኖሩበት ግብፅ አውጥቶ፣ ከነአን ወደ ተባለችው አገር ሊያገባቸው መንገድ በጀመሩ ጊዜ ነው። ታቦቱም ለብዙ ዘመናት በእግዚአብሔርና በእስራኤል መኻል ላለው ጽኑ ቃል ኪዳን ምልክት እንዲሆን የተሰጠ የኪዳን ውልና ስምምነት መታሰቢያ ነበር። ደግሞም ሙሴ፣ በሲና ተራራ ላይ ቆይቶ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ንግግር በፈጸመ ጊዜ በእግዚአብሔር ጣት ሕጉ የተጻፈባቸውና ከድንጋይ የተሠሩ ሁለት ጽላቶችን ተቀብሎ ነበር።[6] የቃል ኪዳኑ ታቦት በሙሴ በኩል ለእስራኤል ሕዝብ በተሰጠበት ጊዜም፣ ታላላቅ ምልክቶች ሆነዋል። ከነዚያም ምልክቶች መኻል ከበድ ያለ የነጎድጓድ ድምፅና መብረቅ፣

[6] ዘጸ31:18። እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ለሙሴ መናገሩን ከፈጸመ በኋላ፣ በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈባቸውን የድንጋይ ጽላቶች፣ ሁለቱን የምስክር ጽላቶች ሰጠው።

እጅግ የበረታ የቀንደ መለከት ድምፅ እንዲሁም ደመናው በዋነኝነት የሚጠቀሱ ናቸው። በጊዜው ነገሩን ባዩና በሰሙ ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ስለ ወደቀባቸው ይንቀጠቀጡ የነበረ ሲሆን፣ እግዚአብሔር የተገለጠበት ተራራ ሳይቀር ይጤስና ይናወጥ ነበር። የሚገርመው ግን ይኸው እጅግ አስገራሚ ኹነት፣ የቃል ኪዳኑ ታቦት በሰማይ በታየ ጊዜ ዳግመኛ መከሰቱ ነው። ዮሐንስ ለዓለም ባስታወቀው በዚህ የራእይው ክፍልም በሰማይ ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ሲከፈት ታቦቱ በዚያ እንደ ታየና እንደ ቀድሞ ሁሉ፣ አስደናቂ የመብረቅ ድምፅ፣ ነጎድጓድም፣ የምድር መናወጥና ታላቅ በረዶ እንደ ሆነ ተናግሯል።[7]

በመጨረሻው ዘመን ስለ ታቦቱ በዚህ መልክ መወሳቱና በሰማይ መታየቱ፣ እስራኤላውያን ከከፊል ድንዛዜ ወጥተው ሙሉ ለሙሉ ወደ አዲሱ ኪዳን እንደሚገቡ ለማስረገጥ ይሆን? በዚያ ላይ ሕዝቅኤል በስደት ለነበረው የእስራኤል ሕዝብ ቢተናገረው ትንቢት እግዚአብሔር ሕዝቡን ከበተነበት ዳግመኛ መልሶ እንደሚሰበስብ ሲተነብይ ድርጊቱን የሚገልጠው ሕዝቡ ከግብፅ ምድር የወጣበትን ሁኔታ በዋቢነት በመጥቀስ እንደነበር [illegible]

ከዚህ ጋር አብሮ የተጠቀሰና ቸል [illegible] የሚያገባው ሌላው ነገር ደግሞ ከዘንዶው ጋር ብርቱ ውጊያ አድርጎ ሊቲቱን የሚታደጋት መልአክ ጉዳይ ነው። እንደሚታወቀው መልአኩ ሚካኤል ከእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ጋር የተለየ ትስስር ያለው መልአክ ነው። እንዲያውም በዳንኤል መጽሐፍ እርሱ የእስራኤል ሕዝብ ጠባቂ እንደ ሆነ በግልጥ ተነግሮአል።[9] አንዳንድ ሰዎችም፣ እስራኤላውያን ከግብፅ ምድር በወጡበት ጊዜ ይመራቸው የነበረው ይኼው መልአክ እንደ ሆነ ያምናሉ።[10] ምናልባት ከረጅም ዓመታት በኋላ መልአኩ ሚካኤል

[7] ዘጸ16:16-19።ራእ11፥19 ::
[8] ሕዝ20:34-36። የቃል ኪዳኑ ታቦት የሚሰውን ርዕስ ይመለከቷል።
[9] ዳን12:1። በዚያን ዘመን ስለ ሕዝብህ የሚቁመው ታላቁ አስቃ ሚካኤል ይነሣል።
[10] ዘጸ14:19 ከዚያም ከእስራኤል ሰራዊት ፊት ሰፊት ሆኖ ሲሄድ የነበረው የእግዚአብሔር መልአክ፣ ተመለሰና ወደ ኋላቸው መጣ፣ የደመናውም ዓምድ አንዲሁ ከፊት ተነሥቶ ከኋላቸው ቆመ፣

ከዚህች ሴት ጋር እንደገና መጠቀሱ፣ ሴቲቱ እስራኤል ስለመሆኗ ሌላው ማስረጃ እንዲሆን ታስቦ ይሆን?

ከዚህም ሌላ እግዚአብሔር ከዘመናት በፊት እስራኤላውያንን ከግብፅ ምድር ባወጣበት ተመሳሳይ መንገድ፣ በመጨረሻው ዘመን ሴቲቱንም በንስር ክንፍ ተሸክሞ እንደሚታደጋት የቀረበው ገለጣ አስገራሚ ነው። በቀደመው ዘመን ለሕዝቡ «በግብፃውያን ያደረግሁትን፣ በንስር ክንፍ አንደ ተሸከምኳችሁ፣ ወደ አኔም አንዳመጣኋችሁ አይታችኋል» ብሏቸው እንደ ነበር የሚታወስ ነው። በዚያን ጊዜ እስራኤላውያን በፈርኦንና በሠራዊቱ እየተሳደዱ የነበረ ከመሆኑም ሌላ፣ ከፊት ለፊታቸው ባለው የኤርትራ ባሕር ምክንያት እጅግ ተጨንቀው እንደነበር የሚረሳ አይደለም። ልክ እንዲሁ፣ በሚመጡት የመጨረሻ ዘመናት ዘንዶው ወደ ምድር በተጣለ ጊዜ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት ያሳድዳታል፣ ነገር ግን ወደ በረሀ ወደተዘጋጀላት ስፍራ በርራ መሄድ እንድትችል ሁለት የታላቁ ንስር ክንፎች ይሰጣታል። እግዚአብሔር ሴቲቱን በምድረ በዳ ውስጥ ከሚያሳድዳት ዘንዶ እጅ የሚታደጋት፣ ከዘመናት በፊት እስራኤላውያንን ከግብፃውያን እጅ ባዳነበት ሁኔታ መሆኑ እጅግ ያስገርማል።[11]

[11] ራእ12:14። ዘጸ19:4።

ቀይ ዘንዶ

12

አነሆ፣ ሰባት ራሶችና አስር ቀንዶች የነበሩት፣
በራሶቹም ላይ ሰባት አክሊል የደፋ ታላቅ ቀይ ዘንዶ ታየ።

ዮሐንስ፣ ሌላ ተጨማሪ ምልክት በሰማይ ተመለከተ፤ ይኸውም፣ ሰባት ራሶችና አስር ቀንዶች የነበሩት ትልቅ ቀይ ዘንዶ ነው። ይህም ዘንዶ በራሶቹ ላይ ሰባት ዘውዶች ጭኖ ነበር፤ በጅራቶቹም የኮከቦችን አንድ ሦስተኛ ስቦ ወደ ምድር ጣላቸው። በምትወልድበት ጊዜ ልጅዋን ለመዋጥ አስቦ ልትወልድ ወደተቃረበችው ሴት ሄደና ከፊት ለፊትዋ ቆመ። ይኼን ዘንዶ በተመለከተ በመጀመሪያ ዘመን በነበሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች ላይ ያለው ገለጣ ትንሽ ለየት ያለ ሲሆን፣ ዘንዶው፣ በአሁኑ ጊዜ በምድር በማይገኝ፣ ነገር ግን በተረት መጽሐፍ ላይ በሚጠቀስና በእነዚያ ዘመናት ግን በሚገባ በሚታወቅ የተለየ አውሬ ስያሜ ነበር የሚታወቀው። በዚያ ዘመን የነበሩ ዕብራውያንም ይኼን አውሬ «ረአብና ሌዋታን» እያሉ ይጠሩት እንደነበር ይነገራል። አውሬው የባሕር ውስጥ ዘንዶ ወይም አሦ እንደሆነ ሲታሰብ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የእግዚአብሔርም ሆነ የእስራኤል ጠላቶች በስሙ ተጠርተዋል።[13]

የዘንዶው መልክ «ቀይ» መሆን ለዘመናት ደም ሲያፈስ እንደኖረ የሚያጋልጥ ቢሆንም ከዚህም በኋላ እንኳ ለታላቅ ጥፋትና ግድያ የተዘጋጀ ሆኖ ይታያል። ሰባት ራሶችና አስር ቀንዶች እንዳሉት ሆኖ መታየቱ፣ በጥንት ዘመን ይነገሩ ከነበሩ አፈ ታሪኮችና ተረቶች ጋር በቀጥታ የሚያያዝ ነገር አለው ተብሎ ይገመታል። ምክንያቱም በእነዚያ ዘመናት «ሌዋታን» የተባለው አውሬ፣ ብዙ ቀንዶች እንደ ነበሩት ይታሰብ ስለነበር ነው። ከዚህ ሌላ ዘንዶው ሰባት ራሶች ያሉት ሆኖ መገኘቱ፣ ምናልባት በአንድ ወቅት የነበረውን ፍጽምና

[12] ራእ12:3።
[13] ኢዮ3:8፣ 41:1-10። መዝ74:14። የሌዋታንን ራሶች አደቀቅህ፡

ወይም የላቀ የማሰብ ችሎታውን ሊገልጥ ይችላል። በተጨማሪም ራሶቹ ብዙ መሆናቸው፣ ዘንዶውን ለመግደልም ሆነ ለማጥፋት እጅግ አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል ይጠቁማል። በራሶቹ ላይ ያሉት ቀንዶችም፣ ገዢነቱንና የግዛት ክልሉን ስፋት ነው የሚያሳዩት።

እንደሚታወቀው ከድሮ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁንም ድረስ ነገሥታት በበዓለ ሲመታቸው ወቅት ዘውድ መድፋታቸው የተለመደ ነገር ነው። ቀንድ ደግሞ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍትም ሆነ በጥንት ታሪኮች ውስጥ ሥልጣንን ወክሎ ሲያገለግል ኖሯል። ነገር ግን የሰባቱ ራሶችና የአስሩ ቀንዶች ሚስጥር ከዚህም በላይ ነው። ምክንያቱም ይህ ዘንዶ ቀድሞ «አባብ» ተብሎ ይጠራ የነበረው ዲያቢሎስ ነውና። እርሱም ከድሮ ጀምሮ የእግዚአብሔርና የሰው ጠላት ሆኖ ነው የኖረው። በዚህ ምድር ላይ በተለያየ ዘመን በተነሡ ነገሥታት ውስጥ ሆኖ ቅዱሳንን ያሳደደ፣ ያሰቃየና የገደለም እርሱ ራሱ ነው። በጅራቱ ከሰማይ ከዋክብት ሲሶውን መጣሉም፣ ከዚህ ዓለም ፍጥረት በፊት ወደ ምድር በተጣለ ጊዜ ከእርሱ ጋር በዐመጽ የተባበሩትን የሰማይ መላክእክት ይዞ እንደ ወደቀ[14] ወይም በመጨረሻው ዘመን ዘንዶው ከእግዚአብሔር ቅዱሳን ጋር በሚያደርገው ጦርነት የሚያገኘውን ጊዜያዊ ድልና ቀጥሎ የሚገጥመውን ሽንፈትም የሚያመለክት ሊሆን እንደሚችል ይታሰባል።[15] «ታላቅ» የተባለውም የግዛት ክልሉ ሰፊ የነበረ በመሆኑ፣ እንዲሁም ለዘመናት በምድር ነገሥታት ሁሉ ላይ ሲሠለጥንባቸው በመቆየቱ ምክንያት ነው።

[14] ኢሳ14፡12። አንተ የንጋት ልጅ፣ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፤ አንዲት ከሰማይ ወደቅህ! አንተ ቀድሞ መንግሥታትን ያዋረድህ፡ አንዲት ወደ ምድር ተጣልህ!
[15] ራዕ12፡7።

ወንዱ ልጅ

16

አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያሰውን ወንድ ልጅ ወሰደች፤ ልጂም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ።

ዘንዶው በምትወልድበት ጊዜ ልጂን ለመዋጥ አስቦ፣ ልትወልድ ወደ ተቃረበችው ሴት ሄደና ከፊት ለፊትዋ ቆመ፤ ሴቲቱ ግን ሕዝቦችን ሁሉ በብረት በትር የሚገዛ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ልጅዋም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተወሰደ፤ እርሷም ወደ በረሀ ሸሸች። እዚያም አንድ ሺ ሁለት መቶ ስልሳ ቀን የምትሸሸግበት ስፍራ እግዚአብሔር አዘጋጅቶላት ነበር።

ማንም እንደሚያውቀው፣ ከሰው ውድቀት በኋላ እግዚአብሔር ወደ አዳም መጥቶ ነበር፤ አዳም ግን ለውድቀቱ ምክንያት በመደርደር እግዚአብሔር ሊሰጠው ያሰበውን ተስፋ ለመስማት ዝግጁ ሳይሆን ቀረ። ወደ ሔዋንም በመጣ ጊዜ የሆነው ተመሳሳይ ነገር ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር ለአባቡ ወይም ለሰይጣን «በአንተና በሴቲቱ መካከል፣ በዘርህና በዘሯ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ ከሴቲቱ የሚወለደው አርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፣ አንተም ሰኮናውን ትነክሳለህ»[17] አለው። እንግዲህ ከዚህ ክስተትና ተስፋ በኋላ ነው፣ ሰይጣን የሰው ጠላትና ባላንጣ የሆነው። በመሆኑም እግዚአብሔር አስቀድሞ ለሰው ሁሉ፣ ቀጥሎ ለእስራኤል በተለይ የገባው ኪዳን እንዳይፈጸም ጋሬጣ ሆኖ ቆየ። ከሌላው ሕዝብ በተለየ ለእስራኤል ሕዝብ ጠላት የሆነበት ምክንያት፣ ከሴቲቱ የሚወለደው ልጅ ራስ፣ ራሱን እንደሚቀጠቅጠው ስለሚያውቅ ነው። በተለያዩ ዘመናት በክርስቶስ የትውልድ ሀረግ ውስጥ የተቆጠረ እያንዳንዱ ቤተሰብ በጭንቅና በመከራ ያለፈበት ምክንያት ግልጥ የሚሆንልን ይኼን የዲያቢሎስ አሳብ የተረዳን እንደሆነ ነው።[18] ሌላው ቀርቶ ክርስቶስ በማርያም ማህፀን አድሮ ወደ ምድር በመጣ

[16] ራእ12፡5
[17] ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 3።
[18] ማቴ1፡1-17። ሉቃ3:23-38።

ጊዜ እርሱን ለማስገደል ምን ያህል እንደጣረ እናውቃለን። አስቀድሞ በሕጉ በኩል አናቱን ቅድስት ማርያምን በድንጋይ ለማስወገር ፈልጎ ነበር፤ እጮኛዋ ዮሴፍ ግን ጻድቅ ሰው ነበርና ሊገልጣትም ሆነ ሊያጋልጣት ባለመውደዱ ሊሳካለት አልቻለም። ከተወለደ በኋላም በሄሮድስ በኩል ሊያስገድለው ወዶ ጦር አዝምቶበታል፤[19] ግን ይኼም ሳይሳካለት ቀረ። ኢየሱስ ለአገልግሎት ሊወጣ በተሰናዳባቸው የመጨረሻ ቀናት ወደ እሱ ቀርቦ፣ ከዓላማው ሊያስተጓጉሉ የሚችሉ አሳቦችን እንደ በጎ አሳቢ በማቅረብ፣ በልዩ ልዩ ፈተና ፈትኖታል። አገልግሎት ከጀመረ በኋላም ብዙ ጊዜ አይሁድን በማነሣሣት ወደ ገደል ሊጨምረውና በድንጋይ ሊያስወግረው ጥረት አድርጓል። ሆኖም አንዱ እንኳ አልሰመረለትም። እግዚአብሔር የቀጠረው ዘመን በደረሰ ጊዜ፣ በአስቆሮቱ ይሁዳና በፈሪሳውያን እንዲሁም በሮማውያን ልብ የነበረውን ሴራ ያጠነጠነና ጉዳዩንም ያስፈጸመ እርሱ ነው። ዳሩ ግን ኢየሱስ አሕዛብን ሁሉ በብረት በትር የሚገዛ ወንድ ልጅ ነው እንጂ፣ ሰይጣን እንዳሰበው ተራ ህፃን ብቻ አልነበረም፤ ስለዚህም መንገዱን በመስቀል በኩል አድርጎ ወደ ዘላለማዊ ዙፋኑ ተነጠቀ።

[19] ማቴ 2:13።

የሴቲቱም ሽሽት

ሴቲቱም ለአንድ ሺ ሁለት መቶ ስልሳ ቀን በዚያ እንዲመገቢት በእግዚአብሔር ተዘጋጅቶላት ወደነበረው ስፍራ ወደ በረሀ ሸሸች።

ዘንዶው ልጇን ሊበላ አስቦ ባልተሳካለት ጊዜ፣ ኃይሉንና ጉልበቱን አስተባብሮ ሴቲቱን ማሳደድ ይጀምራል። ሆኖም ለተወሰነ ጊዜ ተሸሽጋ የምታመልጥበት ስፍራ በበረሀ ስለተዘጋጀላት ፈጽሞ ሊጎዳት አይችልም። ያም ጊዜ ሲሰላ አንድ ሺ ሁለት መቶ ስልሳ ቀን ወይም ሦስት ዓመት ተኩል ያህል ይሆናል። ከዚህ አንጻር ከላይ የተጠቀሰው ምንባብ፣ በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ አስራ ሁለት ቁጥር ስድስት ላይ የሚገኝ ይሁን እንጂ፣ በቁጥር አምስትና በቁጥር ስድስት መካል በጊዜ ተሰልቶ ያልተጠቀሰ ሰፊ ዘመን እንዳለ ግን ይታያል። ይኼም ዘመን አሁን ያለንበት የቤተ ክርስቲያን ዘመን ሲሆን፣ በዮሐንስ ራእይ የመጀመሪያ ምዕራፍ «አሁን ያለው» ተብሎ የተገለጠው ነው። በሌላም በኩል በሁለቱ ቁጥሮች መካል ያለው ዘመን፣ በዳንኤል መጽሐፍ ስለሰባው ሱባኤ በተነገረበት ክፍል በስልሳ ዘጠነኛውና በሰባኛው ሱባኤ መካል ያለውን ዘመን ይመስላል።

ከዚህ በፊት በመጠኑ እንዳየነው፣ ሰባኛው ሱባኤ ሲገባ እስራኤል ለሰባት ዓመት የሚቆይ ስምምነት ከመጨረሻው ዘመን መሪ ጋር ትፈራረማለች፤ ዳሩ ግን ሲጀመር ገና ስምምነቱ በማታለል የተሞላ ነው የሚሆነው። ደግሞም አስቀድሞ በታቀደው መሠረት ከሦስት ዓመት ተኩል ቆይታ በኋላ መሪው ስምምነቱን ያፈርስና የገባውን ቃል ሁሉ ይሽራል፤ በዚህም ምክንያት ጊዜው ለእስራኤል የጽኑ መከራና የስደት ወቅት ይሆንባታል። እንግዲህ በዚያን ጊዜ ነው፣ ለሦስት ዓመት ተኩል ጥበቃ ወደሚደረግላት ስፍራ የምትሸሸው። በአንጻሩ ይህ ዘመን እግዚአብሔር ለእስራኤል የገባውን ኪዳን እንደ ገና የሚያስብበት ከመሆኑም በላይ ለሕዝቡና ለኢየሩሳሌም ከተማ የተቀጠሩት ሰባ ሱባኤዎች የሚፈጸሙባቸው ዓመታት ናቸው።

መቼ ይሆናል?

ጌታ ኢየሱስ ወደ ምድር ከመምጣቱ ጥቂት ዓመታት በፊት፣ ንጉሥ ሄሮድስ፣ ዘሩባቤል ሠርቶት ኤጲፋንስ ያነሳቆለውን ቤተ መቅደስ በማሳደስ ተግባር ተጠምዶ ነበር። ምናልባትም ሄሮድስ ይኼን ያደረገው የአይሁዳውያኑን ልብ ወደ እርሱ ለማሸፈት አስቦ ሊሆን ይችላል። በጌታ አገልግሎት የመጨረሻ ዓመታት መቅደሱ መታደስ ከጀመረ አርባ ስድስት ዓመት አልፎት ነበር። አንድ ቀንም ኢየሱስ በመቅደሱ ተገኝቶ ሳለ፣ አንዳንድ ሰዎች «ይህ ቤተ መቅደስ አንዳት ውብ ነው፣ በከበሩ ድንጋዮችና ለአግዚአብሔር በቀረቡ ስጦታዎች አጊጧል» በማለት እያደነቁ ይነጋገሩ ነበር። እርሱ ግን «ይህ የምታዩት ሁሉ፣ ድንጋይ በድንጋይ ሳይ ተነባብሮ የማይቀርበት ጊዜ ይመጣል፤ አነዚህ ድንጋዮች ሁሉ አንድ ቀን ይፈርሳሉ»[20] አላቸው። እነርሱም «መምህር ሆይ! ይህ የሚሆነው መቼ ነው? ይህ የሚሆንበት ጊዜ መቃረቡን የምናውቅበት ምልክት ምንድን ነው?» ሲሉ ጠየቁት። በወቅቱ ሰዎቹ ከሦስት ያላነሱ ጥያቄዎች የጠየቁት ሲሆን፣ ኢየሱስም ሰፊ ማብራሪያ ሰጥቶአቸዋል። ደቀ መዛሙርቱም ብቻቸውን በሆኑ ጊዜ ወደ እሱ ቀርበው ሌሎች ተጨማሪ ጥያቄዎች አክለውበታል።[21]

ኢየሱስ የዓለም መጨረሻና የመምጣቱ ምልክቶች መኻል አንዱና ዋነኛው የኢየሩሳሌም መደምሰስ፣ የመቅደሱ መፍረስና የሕዝቡ መበተን እንደሆነ ለደቀ መዛሙርቱ ነግሯቸዋል። ሆኖም ኢየሩሳሌም እንደገና እንደምትሠራና መቅደሱም እንደሚገነባ አስታውቋቸዋል።[22] ዳሩ ግን ይኼን ሲናገር፣ ኢየሩሳሌም ከነክብሯ በዝናዋ የነበረች በመሆንዋ ዳግም የምትፈርስ አትመስልም ነበር፣[23] ዕድሳቱ ገና ያልተጠናቀቀው ቤተ መቅደስም ቢሆን ከነውበቱና ተስፋው ቆሞ ሲታይ ለዘላለም የሚኖር ነበር የሚመስለው። ስለዚህ በጊዜው የነበሩ ሰዎች እርሱ የሚለውን ነገር ለመረዳትም ሆነ ለማመን አስቸጋሪና

[20] ሉቃ21:5-7። ማቴ24:1፣2።
[21] ማቴ24:3።
[22] ሉቃ21:24። የአሕዛብ ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ኢየሩሳሌም በአሕዛብ የተረገጠች ትሆናለች
[23] መቅደሱ ያሰቀው በ64 ዓ.ም ነው።

ውስብስብ ሳይሆንባቸው አልቀረም። እርሱ ግን ይህ ሁሉ የሚሆነው መቼ እንደ ሆነ መሠረታዊ ጥቆማዎችን ሳይሰጥ አላለፈም። ከነዚህም መኻል በተለይ የኢየሩሳሌምን መፍረስ ተከትሎ ብዙዎች በሰይፍ እንደሚገደሉ፣ ሌሎችም ተማርከው ወደየአገሩ እንደሚሰደዱና የአሕዛብ ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ኢየሩሳሌም በአሕዛብ የተረገጠች እንደምትሆን የተናገረው ይጠቀሳል። ይኼም ትንቢት፣ በ70 ዓ.ም በሮማውያን በኩል ተፈጽሟል። ዳሩ ግን ከአሁን በኋላ መፈጸም የሚገባው ሌላ ዋና የትንቢት ክፍል አለ። ይህም መጨረሻው ሲቀርብ የሚሆን ነው። ኢየሱስ «የጥፋት አርኩሰት በተቀደሰው ቦታ ቆሞ ስታዩ አንባቢው ያስተውል» ብሏል። ሆኖም በ70 ዓ.ም ኢየሩሳሌም ወድማ መቅደሱ በፈረሰ ጊዜ፣ ይኼ ትንቢት እንደ ተፈጸመ አይታይም። ስለዚህም ከዚህ በኋላ የጥፋት አርኩሰት በተቀደሰው ስፍራ ገና የሚቆም ከሆነ፣ አስቀድሞ ከተማዋና መቅደሱ የመሠራት ተስፋ አላቸው ማለት ነው። መቅደሱ በስፍራው የሚሠራ ከሆነ ደግሞ፣ እስራኤል እንደገና እንደ አገር መመሥረት አለባት።

በእኛ ዘመን ሆነን ታሪክ ስናጠና፣ እስራኤል በ1948 ከ2500 ዓመታት በኋላ እንደ አገር የተመሠረተች በመሆኑ፣ በአሁኑ ጊዜ የትንቢቱ አብዛኛው ክፍል እንደ ተፈጸመ እያየን ነው። በዚያ ላይ ኢየሩሳሌም በ1967 በእስራኤል ቁጥጥር ስር ሆናለች። ታዲያ ምን ቀረ? የመቅደሱ መሠራት ብቻ! ክርስቲያን አማኞች ግን የሚጠ ብቁት ሌላ ታላቅ ተስፋ አላቸው፤ . . . መነጠቅ . . .

የዚህን ተስፋ ዝርዝር ሁኔታ ለመረዳት ከናፈቁ፣ መጽሐፉን ማንበብ ይቀጥሉ፣

ምዕራፍ ፲፯

ያለዓለመቅና የጌታ መምጣት

ሰማይና በውስጧ የምታድሩ ሁሉ ደስ ይበላችሁ፤ ስምድርና ስባሕር ግን ወየውላችሁ ዲያቢሎስ ጥቂት ዘመን አንደቀረው አውቆ በታላቅ ቁጣ ወደ አናንተ ወርዷልና[24]

በዛሬው ጊዜ የጌታን የመምጫ ቀን አስመልክቶ አንዳንድ "ሰዎች" የሚሠሩት ስህተት እጅግ የሚያሳፍርና የሚያሸማቅቅ እየሆነ ነው። አንድ ቀን ለምሳሌ፣ አንድ የማያምን ሰው *«ለመሆኑ አስቴድየም አካባቢ ዓለም በ2012 እንደምትጠፋ በትልቅ ቢል ቦርድ ጽፈው የለጠፉት የአናንተ ሰዎች ናቸው እንዴ?»* ብሎ ጠየቀኝ። እኔም ነገሩ ሊሆን እንደማይችልና ማንም ሰው በዚህ ወርና ቀን ብሎ የጌታን መምጫም ሆነ የዓለምን መጥፋት ሊያውቅ እንደማይችል ለማስረዳት ሞከርኩ። ሆኖም የተባለው ነገር በእርግጥ በምኖርበት ከተማ ተደርጎ እንደ ሆነ ለማወቅ ጉጉት ስላደረብኝ ስቴድየም ድረስ ሄጄ በቀለመ ወርቅ ህንፃ ላይ የተባለውን «ባነር» በዓይኔ ፈለግሁት። ይሁን እንጂ ጽሑፉ ቀድሞ ተነሥቶ ስለነበር በዓይኔ ልመለከተው አልቻልኩም። በኋላ ላይ እንደተረዳሁት ግን የዚህ አሳብ አቀንቀኞች የዚህ ዓለም ሳይንሲስቶች እንጂ፣ ሰውየው እንዳለው «የእኛ ሰዎች» እንዳልሆኑ አወቅሁ። እንዲያውም አንድ ወዳጄ ስለጉዳዩ የተጻፈች አጭር ወግ ሰጥቶኝ፣ እየተደነቅሁ አነበብኳት።[25]

ይህ ከሆነ ከጥቂት ቀናት በኋላ ግን «ሮዝ»[26] በተሰኘ መጽሔት ላይ አንድ የዲላ ሰው *«ዓለም በዚህ ጊዜ ትጠፋለች»* ብሎ በእርግጠኛነት የጻፈውን አነበብኩ። በ15ኛው ቀን ደግሞ ሌላ ሰው፣ ከዚያ በፊት

[24] ራእ12:12።
[25] 20 አስራ ሁለቱ የጽሕመት ቁጠር ወንና ሥነ ገፅም፡ 2002 ሙሴ ያዕቀብ ጸ/ር
[26] ሮዝ መጽሔት ቁጽ 4 ቁጥር 60 መጋቢት 2002 ዓ.ም።

በወጣው ጽሑፍ እጅግ እንደተበሳጨ ከገለጠ በኋላ *«ነገሩ እውነት እንኳ ቢሆን፣ አንዳችም ተሰፋ ሳታሳዩን ለምን የዓለምን መጥፋት ብቻ ትነግሩናላችሁ?»* ሲል በመጽሔቱ አዘጋጆችና በጸሐፊው የተሰማውን ቅሬታ በምሬት ጽፎ አነበብኩኝ።

በእርግጥ እኔም ብሆን ሁለተኛው ሰው ባለው እስማማለሁ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች ዋና ዓላማ፣ ስለዓለም ፍጻሜ መናገር ብቻ ሳይሆን፣ ከዓለም ፍጻሜ በፊት ሰዎች ተዘጋጅተው እንዲጠብቁ ማሳሰብና ከፍጻሜውም በኋላ ስለሚኖረው ዘላለማዊ ሕይወት መጠቆም እንደሆነ ስለማምን ነው። ደግሞም ማንም ይሁን ማን *«ዓለም በዚህ ዓመትና ወር ትጠፋለች»* ብሎ ቀንና ሰዓቱን ለመናገር ቢሞክር ገና ከመጀመሪያው እሱ ሐሰተኛ ይሆናል። ለምን ቢሉ፣ ጌታ ኢየሱስ ራሱ ያቺን ሰዓትና ቀን ማንም እንደማያውቅ ተናግሯልና ነው። ከምልክቶቹ መፈጸም ወይም መሆን በመነሣት ብንናገር እንኳ፣ መገመት የምንችለው የቀኑን መቅረብ ብቻ ነው።[27]

እንዲህ ማለት ግን ስለጌታ መምጣትና ስለዓለም ፍጻሜ የሚነገሩትን ትንቢቶች ሁሉ ቸል እንበላቸው ወይም ጆሯችንን እንፈጋቸው ማለት አይደለም። እንዲህ ዓይነቱ አሳብ የሰይጣን እንደሆነና እሱም አጥብቆ የሚፈልገው መሆኑን ደግሞ መዘንጋት የለብንም። እንዲያውም ዛሬ በብዙ ስፍራዎች ስለጌታ ኢየሱስ ዳግመኛ መምጣት የሚነገረውን ነገር ሰዎች በቸልታ የሚመለከቱበት አንዱ ምክንያት፣ እንደነዚህ ዓይነት ትምህርት አይሉት መገለጥ አገር ምድሩን ስለሞሉት ነው፣ ማለት ይቻላል። ለምሳሌ ከዓመታት በፊት አንድ ጓደኛችን ቤተ ክርስቲያን ደርሶ ሲመለስ ለእናቱ *«ይገርምሻል እማዬ፣ ዛሬ አቡ "መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሃ ግቡ" ተብሎ ተሰበከ»* ይላቸዋል። እናቲቱ ግን በልጃቸው ማደነቅ እጅግ ተገርመው *«አይ አንተ፣ ታዲያ ምኑ ነው የሚገርመው? ይሺ ዘመንግሥቱ ንዋይ ግርግር ጀምሮ ሲነገር የነበረ አይደለምን?»*[28] ብለውት እርፍ አሉ።

[27] ማቴ 24፣36-37።
[28] የመንግሥቱ ነዋይ ግርግር፡ በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር በ1953 ዓ.ም የሆነ ነው።

መጠኑ ይለያይ እንጂ፣ በዚህ ዘመን በብዙ ክርስቲያኖች ዘንድ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት መቅረብ ያለው አስተሳሰብ፣ ከኂህ እናት አመለካከት ብዙም የማይለይ ነው። ይህ ዓይነቱ አመለካከት ደግሞ መንፈሳዊ ድንዛዜን ከማስከተሉ በላይ፣ አማኞች ምድር ተኮር እንዲሆኑ አበረታቷቸዋል የሚል አሳብ አለኝ። በአንጻሩ በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ከሚሆነው ነገር የተነሣ ሁሉ ነገር የተጨረሰ መስሎ ነው የሚታየው። ሆኖም ብዙ ሰዎች ይኼን ስለማያስተውሉ፣ ዘመኑ የኖኅን ዘመን ይመስላል። በዚያን ጊዜ ኖኅ ዘመኑ እንደ ተፈጸመ አውቆ፣ ለዓመታት መርከብ በመሥራት ሥራ ተጠምዶ ነበር። አንዳንዶች እንደሚሉት ኖኅ መርከቡን ሠርቶ እስኪፈጽም፣ ከመቶ ዓመታት በላይ አስፈልጎታል። ትንቢቱ በመዘግየቱ ይመስላል ከአሱና ከቤተሰቡ በቀር ሊሆን ያለውን ነገር የሚጠባበቅ አልነበረም። ጌታ ኢየሱስ ከሺ ዓመታት በኋላ ስለመጨረሻው ዘመን ሲናገር፣ አብነታዊ ማስረጃ አድርጎ የጠቀሰው የኖኅን ዘመን መሆኑ ደግሞ፣ ያለንበት ዘመን፣ ከዚያ ዘመን ጋር ምን ያህል እንደሚመሳሰል ያሳያል።

> ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም። የኖኅ ዘመን እንደነበረ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና። በዚያች ወራት ከጥፋት ውኃ በፊት፥ ኖኅ ወደ መርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ፥ ሲበሉና ሲጠጡ ሲያገቡና ሲጋቡም እንደ ነበሩ፥ የጥፋት ውኃም መጥቶ ሁሉን እስከ ወሰደ ድረስ እንዳላወቁ፥ የሰው ልጅ መምጣት ደግሞ እንዲሁ ይሆናል። በዚያን ጊዜ ሁለት ሰዎች በእርሻ ይሆናሉ፤ አንዱ ይወሰዳል አንዱም ይቀራል፤ ሁለት ሴቶች በወፍጮ ይፈጫሉ፤ አንዲቱ ትወሰዳለች አንዲቱም ትቀራለች። [29]

ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በምድር ላይ በቆየባቸው የመጨረሻ ቀናት፣ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው ተስፋ እጅግ የሚያጽናና ነበር። እሱ «አሳዳስሁ፣ ተመልሼም ወደ አንናንተ አመጣለሁ» አላቸው። ከዚህ የተነሣ የጌታ ዳግመኛ መምጣት ጉዳይ ምንም የሚያጠራጥር አይደለም። በዚያ ላይ ከዚህ ቀደም ስለመጀመሪያው መምጣቱ ተነግረው ከነበሩ ትንቢቶች

[29] ማቴ24:36-41

አንዳቸውም ሳይዛነፉ መፈጸማቸውን የየ ሰው፣ ዳግመኛ የመምጣቱን ጉዳይ ጥያቄ ውስጥ አያስገባውም። ዳሩ ግን «እንዴትና መቼ ነው የሚመጣው?» የሚለው ጉዳይ ነው፣ እስከ ዛሬ ድረስ ሲያወዛግብ የኖረው። ሆኖም ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች በጻፈው የመጀመሪያ መልዕክቱ ስለጌታ መምጣት እንዲሁም እንዴት ባለ ሁኔታና ከየት እንደሚመጣ ይጠቁማል።[30] ጳውሎስ የሚሰጠው ገለጣም ወንጌላዊው ሉቃስ አስቀድሞ ከመላእክቱ ሰምቶ ከዘገበው ጋር ይስማማል። በወቅቱ ጌታ ኢየሱስ፣ ወደ ሰማይ ሲያርግ ከእርሱ ጋር የነበሩ ደቀ መዛሙርት ሁሉ በአድናቆት ትኩር ብለው ያዩት ነበር፣ በሰዓቱ ከሰማይ ተልከው የመጡት መላእክትም ተሰብስበው ለነበሩት ሰዎች፣ ወደ ሰማይ ሲሄድ ያዩት ጌታ፣ በተመሳሳይ ሁኔታ ተመልሶ እንደ ሚመጣ ነግረዋቸዋል።

በሰባኛው ሱባኤ መግቢያ ዋዜማ እንደሚሆኑ ከሚጠበቁ ክስተቶች መኻል ንጥቀትና የጌታ መምጣት የተባሉትን ነገሮች ጨምሮ በብዙ ጉዳዮች ላይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሠረታዊ የሚባሉ ልዩነቶች አሉ። ይሁን እንጂ እነዚህ ልዩነቶች የዶክትሪን ልዩነት ያህል የሚጋነኑ አይደሉም። ሌላው ቀርቶ በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አብረው በሚያገለግሉ አማኞች መኻል እንኳ የአመለካከት ልዩነት ሊከሰት ይችላል፣ አንዳንድ ጊዜም ሰዎች በአንድ ወቅት ከተቀበሉት የተለየ አመለካከት ይዘው ይገኛሉ። በመሆኑም ማንም ሰው ንጥቀት የሚሆንበትን ጊዜ በተመለከተ ባለው ዕይታ ብቻ ሊወገዝ ወይም እንደ የስህተት አስተማሪ ሊቆጠር አይገባውም የሚል እምነት አለኝ።

እርግጥ ነው፣ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች፣ ቤተ ክርስቲያን የምትነጠቀው የሰባኛውን ሱባኤ መግባት ተከትሎ እንደሚሆን ይስማማሉ። ይሁን እንጂ «በየትኛው ጊዜ?» በሚለው ጉዳይ መቼም የሚስማሙ አይመስሉም። ይኼም ልዩነት ከቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ጋር አብሮ ከሚከሰተው ወይም በሰባኛው ሱባኤ እንደሚሆን ከሚጠበቀው የ«ታላቁ መከራ» ኹነት ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ የቤተ

[30] ዮሐ14:1-4። 2ኛተሰ4:16። ሉቃ1:10፣11።

ክርስቲያን መነጠቅ፣ ከመከራው በፊት? በመከራው እኩሌታ? ወይስ ከመከራው በኋላ? ነው የሚሆነው? የሚለው ጥያቄ ሁሌም አከራካሪ ሆኖ ነው የኖረው:: እኔም ብዙ ጊዜ *«በነዚህ ጉዳዮች ከመከራከር ይልቅ ጥቂት ታግሶ ፍጻሜውን ማየት ጥሩ ሳይሆን አይቀርም»* እያልኩ ሳስብ ብኖርም፣ እንደዚህ ጽሑፍ አቅራቢነቴ ግን አቋሜን የግድ መግለጥ ያለብኝ መስሎ ይሰማኛል:: ከዚህ አንጻር በበኩሌ ቤተ ክርስቲያን የምትነጠቀው ከታላቁ መከራ በፊት ነው፣ ብዬ ነው የማምነው:: ከዚህ በኋላ የሚንጸባረቁት አሳቦቼም ከዚሁ እምነቴ የሚነሡ መሆናቸውን አስቀድሜ ማስታወቅ እወዳለሁ::

በዮሐንስ ራእይ መልዕክት ከተላከላቸው ሰባት አብያተ ክርስቲያናት መኻል የፍልድልፊያና የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያናት በዘመናቸው ከነበራቸው መንፈሳዊ ሁኔታ ባለፈ የመጨረሻውን ዘመን ክስተት ቀድመው ይጠቁማሉ ተብሎ እንደሚታመን ከዚህ በፊት አይተናል:: በዚህ አመለካከት አቀንቃኞች ዘንድ ፍልድልፊያ ከአስራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ ንጥቀት ያለውን ዘመን የምታመለክት ቤተ ክርስቲያን እንደሆነች ነው የሚታሰበው:: ምንም እንኳ ይህቺ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሰምርኔስ ሁሉ፣ ያለ ነቀፋ የነበረች ቢሆንም የመጣላት ተስፋ ግን ከሰምርኔስ ፍጹም የተለየ እንደሆነ ግልጥ ነው:: በዚያ ክፍል በትዕግሥት የጸኑና እስከ መጨረሻው ትዕዛዙን የጠበቁ፣ በምድር የሚኖሩትን ሁሉ ሊፈትናቸው ከሚመጣው የፈተና ሰዓት እንደሚጠበቁ ጌታ ተስፋ ሰጥቷል:: ይኼም ተስፋ ከፊፍልድልፊያ ባለፈ ቤተ ክርስቲያን ከታላቁ መከራ በፊት ተነጥቃ እንደምትወሰድ ከተሰጡት ተስፋዎች አንዱ ሆኖ ይጠቀሳል::

በሌላም በኩል «የዐመፅ ሚስጥር አሁን አንኳ እየሠራ ነውና፤ ነገር ግን ይህ የሚሆነው ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ ብቻ ነው፤ በራሱ ጊዜ ደግሞ ዘንድ አሁን ምን እንደሚከለክለው ታውቃላችሁ» የሚለው የጳውሎስ የተሰሎንቄው መልዕክት ካነሣነው አሳብ አንጻር በትኩረት ሊጠና የሚገባው ክፍል ነው:: ደግሞም ከልካይዋ፣ እንዲሁም በሆነ ጊዜ፣ ለተወሰኑ ዘመናት የምትወገደው ቤተ ክርስቲያንና በእርሷ የሚሠራው መንፈስ ቅዱስ መሆኑን የምናምን ከሆነ፣ ከዚህ በመነሣት ብቻ ቤተ ክርስቲያን

ከመከራው በፊት እንደምትነጠቅ እንድናስብ እንገደዳለን:: በተጨማሪ ጳውሎስ[31] «አሁን በደሙ ከጸደቅን፣ ይልቁኑማ ከእግዚአብሔር ቁጣ እንዴት እንድንም! አግዚአብሔር ድነትን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት እንድናገኝ ነው እንጂ ሰቁጣ ወስኖ አሳስቀመጠንምና» ማለቱ፣ ወቅቱ የእግዚአብሔር ቁጣ ጊዜ እንደሆነና ሆኖም በደሙ የጸደቁ አማኞች የቁጣ ሰለባ እንደማይሆኑ የሚያስረዳ ነው፣ ተብሎ ይታሰባል::

«ቤተ ክርስቲያን፣ የምትነጠቀው ከታላቁ መከራ በፊት ነው» ለሚለው፣ መረዳት ተጨማሪ ማስረጃ ተደርጎ የሚወሰደው፣ በራእይ መጽሐፍ ከምዕራፍ 4 በኋላ አንዲም እንኳ ስሟ አለመጠቀሱ ነው:: በእርግጥም ነገሩ በአጋጣሚ የሆነ አይመስልም:: ምናልባትም ቤተ ክርስቲያን ሰባኛው ሱባኤ ከመግባቱ ቀድሞ የተነጠቀች መሆኗን ለማመልከት ሆን ተብሎ የተደረገ ነው የሚመስለው:: ከዚህም ሌላ እነዚያ በራእይ መጽሐፍ ውስጥ ከፍተኛ ሽፋን ያገኙት ወቅቶች ለእስራኤልና ከእርሷ ጋር በመጨረሻው ዘመን ለሚፋጠጡ የዓለም መንግሥታት የተተው ወራት መስለው ነው የሚታዩት::

ይሁን እንጂ *«በቤተ ክርስቲያን መነጠቅና በጌታ መምጣት መኻል ግልጽነተኛ ልዩነት አለ? ወይስ የለም?»* የሚለው ነገር እጅግ መጠናት የሚገባው ጉዳይ ነው:: በመሠረቱ ጳውሎስ፣ ጌታ ኢየሱስ በታላቅ ትዕዛዝ፣ በመላእክት አለቃ ድምፅና በእግዚአብሔር የመለከት ድምፅ ከሰማይ እንደሚወርድ በተናገረ ጊዜ፣ የዚያን ዘመን ሥርዓት ምን እንደሚመስል ጭምር አስታውቆናል:: እርሱ እንደሚለው አስቀድሞ በክርስቶስ አምነው የሞቱት ይነሡና፣ በወቅቱ በሕይወት ለመኖር ከሚታደሉት፣ ዳሩ ግን በቅጽበተ ዓይን ከሚለወጡት አማኞች ጋር ጌታን በአየር ለመቀበል፣ በደመና ተነጥቀው ይሄዳሉ፤ ለዘላለምም ከጌታ ጋር ይሆናሉ፣ ይኼም በጌታ መምጣትና በመነጠቅ መኻል ያለው ልዩነት ፍንጭ ይሰጣል:: ሆኖም በንጥቀት ጊዜ ጌታ ኢየሱስ በቀጥታ ወደ ምድር የሚደርስ መስሎ አይታይም:: እንዲያውም ወደዚህ ከመድረሱ አስቀድሞ በምድር ላይ መሆን የሚገባቸው

[31] 2ኛተሰ2:1-4:: ራዕ ምዕ 2 እና ምዕ 3 :: ራዕ3:10:: ሮሜ5:9::

አበይት ነገሮች አሉ። በተጨማሪም ጳውሎስ፣ ኢየሱስ የሚመጣው ሁላችን ከሞትን ወይም ካንቀላፋን በኋላ አለመሆኑን ሲያስገነዝብ «እነሆ አንድ ሚስጥር እነግራችኋለሁ»[32] ይለናል። ሚስጥር የተባለው ነገር ደግሞ፣ የኋለኛው ወይም የመጨረሻው መለከት ሲነፋ፣ በምድር ላይ በሕይወተ ሥጋ የተገኙ አማኞች በቅጽበተ ዓይን መለወጣቸውን እና በዚያው ሰዓት በጌታ ሆነው ያንቀላፉ ሙታን ደግሞም ለዘላለም የማይበሰብሱ ሆነው እንደሚነሡ የሚያመለክት ነው።

ኢየሱስ ወደ ምድር መምጣት ሲጀምር፣ ከሚሆኑ ነገሮች፣ በተለይ አራቱ ትኩረት የሚስቡ ናቸው። በዚሁ መሠረት የመጀመሪያው፣ በየትኛውም ጊዜ በክርስቶስ አምነው የሥጋ ሞትን የቀመሱ አማኞች ከያሉበት የማይበሰብሱና የማይፈርሱ ሆነው የሚነሡበት ሥርዓት ነው። ይህም በሰው ወግና ደንብ በሚገባ ተገንዞ ከተቀበረው ጀምሮ አውሬ የበላው፣ እሳት ያቃጠለው፣ በውኃ የተወሰደውና ሌላም ዓይነት ሞት የቀመሰውን ሁሉ የሚመለከት ነው። ይህ የሚሆንበትን ቀን ማሰብ በራሱ ምንኛ ያጓጓል!

ሁለተኛው አጓጊ ታምር፣ እስከ ንጥቀት ቀን ድረስ በሕይወተ ሥጋ ተጠብቀው በምድር ላይ የሚቆዩ ዕድለኛ አማኞች፣ በቅጽበተ ዓይን ተለውጠው የትንሣኤውን አካል የሚለብሱበት ሥርዓት ነው። በዚያን ጊዜ እያንዳንዱ አማኝ በምድር ለብሶት የኖረው ሥጋ ለዘላለማዊ አገርና መንግሥት በሚመጥን ሰውነት ይለወጣል። በወቅቱ አማኞች የሚለብሱት የትንሣኤው ሥጋ ለዘላለም የሚኖር አካል የሚሆንላቸው ሲሆን ከሙታን ተቀስቅሰው ከሚነሡት ጋር አንድ ዓይነት ሰውነትና ክብር ይኖራቸዋል።

ከዚህ ቀጥሎ የሚጠበቀው ሦስተኛው ነገር፣ ከሞት የተቀሰቀሱትና በምድር ሲኖሩ ተገኝተው በቅጽበት የተለወጡት አማኞች ጌታን ለመቀበል ወደ አየር የሚነጠቁበት ሂደት ነው። ታዲያ በዚህ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ጌታ ወዳለበት ስትነጠቅ፣ ጌታም ከሰማያት ወርዶ

[32] 1ኛተሰ4:13-18። 1ኛቆሮ15-55። እነሆ አንድ ሚስጥር እነግራችኋለሁ፣ ሁላችን አናቀላፋም፣ ነገር ግን ሁላችን እንለወጣለን።

ቤተ ክርስቲያኑን በአየር ላይ ይቀበላታል። ሆኖም ጌታና ቤተ ክርስቲያን የሚገናኙበት ስፍራ በአየር ላይ እንደሆነ ከመገለጡ በቀር፣ ስለስፍራው ዝርዝር ማብራሪያ ማግኘት አይቻልም። ምንም እንኳ ይህ «አየር» የተባለውን ስፍራ «እዚህ ቦታ ነው» ብሎ ማመልከት ፈጽሞ የማይቻል ቢሆንም በቅዱሱ መጽሐፍ «አየር» እና «ሰማይ» የሚሉት ቃላት ግን ለአንድ ዓይነት ስፍራ ጥቅም ላይ እንደዋሉ መረዳት ይቻላል። ከዚህ አንጻር ለምሳሌ ጳውሎስ ሰይጣንና ሠራዊቱ አሁን የሚገኙበትን ቦታ ሲያስረዳ በ«ሰማያዊ ስፍራ» እንደሆነ ሲጠቁም፣ ዮሐንስ ደግሞ በመጨረሻው ዘመን ሰይጣን ወደ ምድር ከመጣሉ በፊት ከሚካኤል ጋር ተዋግቶ የሚያጣው ስፍራ «ሰማይ» እንደሆነ ይገልጣል። ዮሐንስ በተጨማሪ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሰማይ በምትነጠቅበት በዚያ ቅጽበት፣ ዲያቢሎስ ወደምድር እንደሚጣልና በዚያ ጊዜ በሰማይ ታላቅ ደስታ በምድርና በባሕር ደግሞ ታላቅ መከራ እንደሚሆን ተናግሯል፣[33] ምክንያቱም ዲያቢሎስ ወደምድር ሲጣል፣ ከዚያ በኋላ ጥቂት ጊዜ እንደሚቀረው አውቆ በታላቅ ቁጣ ስለሚሞላ ነው። ይኼም ሳይነጠቁ በምድር ለቀሩ ሰዎች ጊዜውን፣ የመከራ ጊዜ ያደርግባቸዋል።[34]

ከንጥቀትና ከጌታ መምጣት ተከትሎ የሚሆነው ስድተኛ ነገር ደግሞ ይህ ነው። ቤተ ክርስቲያን ተነጥቃ፣ ጌታም በአየር ወይም በሰማይ ላይ ከተቀበላት ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ፣ ጌታ ኢየሱስ ከተነጠቁት ቅዱሳን ጋር አብሮ ወደ ምድር ይመጣል። ይህም «ኢየሱስ እንደሞተና እንደተነሣ ካመንን፣ እንዲሁ ከኢየሱስ ጋር ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋል»[35] ተብሎ እንደተጻፈው ማለት ነው። ዮሐንስም ጌታ ኢየሱስ ወደ ምድር በሚመለስበት ጊዜ ስለሚሆነው ነገር ሲገልጥ፣ በነጫጭ ፈረሶች ላይ የተቀመጡ፣ ነጭና ቀጭን ልብስ የለበሱ የሰማይ ሠራዊት እንደሚከተሉት ይነግረናል። እነዚህ ጌታን በዚህ

[33] ኢፌ6:12። ምክንያቱም ተጋድሎአችን ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን ከዚህ ከጨለማ ዓለም ገዦች ከሥልጣናትና ከጎይላት አንዲሁም በሰማያዊ ስፍራ ካሉ ርኩሳን መናፍስት ሰራዊት ጋር ነው። ራእ12:7። በሰማይም ጦርነት ሆነ፣ መላእክቱ ከዘንዶው ጋር ተዋጉ...በሰማይም የነበራችውን ስፍራ አጡ..

[34] ማቴ24:20-22። በዚያን ጊዜ፣ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ሆኖ የማያውቅ፣ ከዚያም በኋላ የሚሆን ታላቅ መከራ ይሆናል።

[35] 1ኛተሰ4:14።

ሁኔታ የሚከተሉት «ሠራዊቶች» ደግሞ አስቀድሞ ከምድር ከተነጠቁ በኋላ ለጥቂት ጊዜአት ከእርሱ ጋር በአየር ወይም በሰማይ ላይ የቆዩ ነው የሚመስሉት። አለባበሳቸው በራዕይ መጽሐፍ በክርስቶስ አምነው በቅድስና እንደኖሩ ከተመሠከረላቸው ሌሎች ሰዎች አለባበስ ጋር አንድ ዓይነት መሆኑ ማስረጃ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው።[36]

> ነገር ግን ልብሳቸውን ያላረከሱ በሰርዴስ ጥቂት ሰዎች ከአንተ ጋር አሉ፥ የተገባቸውም ስለ ሆኑ ነጭ ልብስ ለብሰው ከእኔ ጋር ይሄዳሉ። ድል የነሣው እንዲሁ በነጭ ልብስ ይጐናጸፋል፥ ስሙንም ከሕይወት መጽሐፍ አልደመስስም፥ በአባቴና በመላእክቱም ፊት ስለ ስሙ እመሰክርለታለሁ።

በመሠረቱ በጌታ መምጣትና ወደ እርሱ በመነጠቅ ጊዜ ስለሚሆኑት ነገሮች በትኩረት ማጥናት ተገቢ ስለመሆኑ ባያጠያይቅም፣ አማኞች ግን «የጌታ ቀን ደርሷል» ብለው ቶሎ በአእምሮአቸው የሚናወጡ መሆን የለባቸውም። ይኼን ሰበብ አድርጎም ማንም በምንም ዓይነት እንዳያታልላቸው በማስተዋል መመላለስ ይጠበቅባቸዋል። ምክንያቱም አስቀድሞ ዐመፅ ሳይነሣ፣ ለጥፋትም የተመደበው የዐመፅ ሰው ሳይገለጥ ያ ቀን አይመጣምና። እሱም አምላክ ከተባለና ከሚመለከው ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ፣ የክርስቶስ ተቃዋሚ ሲሆን፣ ጊዜው ሲደርስ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ተቀምጦ «እኔ አምላክ ነኝ» እያለ፣ ዐዋጅ እንደሚያስነግር ይጠበቃል።[37]

[36] ራእ.3:4 ራእ.3:5
[37] 1ኛተሰ4:14።

መንጠቅ ድንግል

ምንም እንኳ ዮሐንስ ባየው ራዕይ ውስጥ ሰፊ ስፍራ የተሰጠው በሰባኛው ሱባኤ ስለሚሆኑ ነገሮች ቢሆንም፣ በመጽሐፉ 2ኛና 3ኛ ምዕራፍ ውስጥ አማኞች ንጥቀትና የጌታ መምጣት እስኪሆን ድረስ እንዴት ባለ የሕይወት ሥርዓት መመላለስ እንዳለባቸው በቂ ግንዛቤ ሰጥቷል። ጌታ ኢየሱስም ከመነጠቅና ከእርሱ ዳግም መምጣት በፊት በዓለም የሚታዩ አበይት ምልክቶችን በተመለከተ ለደቀ መዛሙርቱ ሰፊ ጊዜ ወስዶ አስተምሯል።[38] በአሁኑ ጊዜም አስቀድሞ እንደሚሆኑ ከተነገሩት ምልክቶች አብዛኛዎቹ የተፈጸሙ ቢሆንም በተለይ የሁለቱ ምልክቶች ፍጻሜ ግን የዓለምን መጨረሻ እጅግ እንደሚያቻኩለው መረዳት ያሻል። ከአበይት ምልክቶቹ የመጀመሪያው የእስራኤል እንደ አገር መመሥረት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በሜድትራሊያን አካባቢ ባሉ አስር አገሮች ላይ የሚሾመው፣ እንዲሁም ከአስራኤልና ከቀረው ዓለም ጋር ለአንድ ሱባኤ የሰላም ስምምነት የሚፈራረመው የዚያ ዘመን ታላቅ መሪ መገለጥ ናቸው። ከዚሁ ሰው ጋር በአንድ ዘመን አብረው እንደሚነግሡ የሚጠበቁት አስር መንግሥታትም፣ ሮምን ጨምሮ አንዳንድ የደቡብ አውሮፓ አገራትንና የተወሰኑ የሰሜን አፍሪካ መንግሥታትን ያቀፈ የኮንፌዴሬሽን ጎብረት ሊሆን እንደሚችል ይገመታል።[39] ከዚህ በተለየ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ የተለያዩ መንግሥታት ጎብረቶች፣ ማለትም እንደአውሮፓ ጎብረት፣ የዓረብ ሊግ፣ የአፍሪካ ጎብረትና የመሳሰሉትን የሚያካትት ሊሆን ይችላል። ካልሆነም ሌሎች ይሆናሉ። ያም ሆነ ይህ የመንግሥታቱ ቁጥር አስር መሆኑና ጎብረቱም ሮምን የሚጨምር መሆኑ ግን የተረጋገጠ ነው።

ይሁን እንጂ መነጠቅ የሚባለው ነገር ድንገት የሚከሰት በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ ፍጹም ግልጥ የሆኑ ምልክቶችን መጠበቅ የለብንም።

[38] ማቴ24እና25፣ ሉቃ21።
[39] ዳን2:41-43።

እንዲያውም መነጠቅን በማስመልከት ለአማኞች የተሰጡ ምሳሌዎች ማንም ሰው «*በዚህ ቀን ይሆናል*» በማለት እርግጠኛ እንዳይሆን የሚከለክሉ ሆነው ይታያሉ። በኖኅ ዘመን[40] እንደታየው ማለትም፣ የጥፋት ውኃ መምጣቱን ተረድቶ ኖኅ ወደ መርከቡ ከመግባቱ በፊት ሰዎች እንደተለመደው ሲበሉ፣ ሲጠጡ፣ ሲያገቡና ሲያጋቡ እንደ ነበረው፣ መነጠቅም እንዲሁ እንደሚሆን ነው የሚጠበቀው። የጥፋት ውኃ መጥቶ ጠራርጎ እስኪወስዳቸው ጊዜ ድረስ፣ የዚያ ዘመን ሰዎች ጥፋቱ ያን ያህል በደጅ መቅረቡን አላወቁም ነበር።

ኢየሱስ የጊዜውን ድንገትነት ሲያስረዳ «*የዚያን ጊዜ ሁለት ሰዎች በእርሻቸው ላይ ሳሉ፣ አንደኛው ሲወሰድ ሌላኛው ይቀራል፤ ሁለት ሴቶች በአንድ ወፍጮ ሲፈጩ፣ አንዷ ስትነጠቅ፣ ሌላኛዋ ትቀራለች። ባለቤት በየትኛው ጊዜ ሌባ ወደቤቱ እንደሚመጣ ቢያውቅ ኖሮ ቤቱን ይጠብቅ ነበር*» በማለት አስጠንቅቋል። ስለዚህ ቀኑ መቼ እንደሆነ ስለማይታወቅ ያለው ብቸኛ መፍትሄ ሁልጊዜ ተዘጋጅቶ መኖር ብቻ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ኢየሱስ ስለደጉና ክፉው አገልጋይ፣ ስለአስሩ ቆነጃጅቶች እንዲሁም ከጌታቸው ዘንድ መጠኑ የተለያየ መክሊት ስለተቀበሉ ሦስት አገልጋዮች የተናገረው ምሳሌ በጠቅላላ የነገሩን በድንገት መሆን የሚገልጡ ናቸው።[41]

ሆኖም የኢየሱስ መምጫ «እንደ ሌባ ነው» መባሉ፣ ወይም ጨርሶ አለመታወቁ እሱን ተቀብለው፣ በእርሱ ለሚኖሩ ሰዎች አሳሳቢ ነገር አይደለም። ምክንያቱም ማንም በኢየሱስ አምኖ አዳኝነቱን የተቀበለ ሰው፣ የብርሃንና የቀን ልጅ ነው እንጂ፣ የጨለማ ልጅ አይደለምና ነው።[42] በመሆኑም ከጨለማ ወጥተው የብርሃን ልጆች በሆኑት ላይ ቀኑ እንደ ሌባ አይደርስባቸውም። በመሠረቱ ጌታ እንደ ሌባ የሚመጣባቸው ሰዎች፣ በዚህ ዓለም ደስ ለመሰኘት ከመፈለጋቸው በቀር፣ ስለእርሱ የመስቀል ሥራም ሆነ ስለዳግመኛ መምጣቱ ምንም ግድ የሌላቸው ናቸው። እነዚህም ሰዎች «ሰላምና ደኅንነት ነው» ሲሉ

[40] ማቴ24:37-39።
[41] ማቴ24:37-39። ሉቃ17:26:27። ማቴ24:45-51። ሉቃ12:42-46።
[42] 1ኛተሰ5:4። ሁላችሁም የብርሃን ልጆች የቀንም ልጆች ናችሁና . . .

ምጥ እርጉዝን ድንገት እንደሚይዛት ጥፋት ይመጣባቸዋል። ያም ቀን በምድር የሚኖሩ ሰዎችን ሁሉ እንደ ወጥመድ ተዘጋጅቶ ስለ ሚያጠምዳቸው ፈጽሞ አያመልጡም። የኢየሱስ ተከታዮችም ቢሆኑ፣ ከእነዚህ ሰዎች ጋር አብረው እንዳይጠፉ ሁልጊዜ በአግባብና በመጠን መኖር ይጠበቅባቸዋል። ስለዚህ በመብልና በመጠጥ ብዛት፣ በስካርም በመባከን፣ ወይም ስለዓለማዊ ኑሮ በመጨነቅ ልባቸው እንዳይዝል መጠንቀቅ አለባቸው። አለያ ግን በዓለም እንደወጥመድ የሚመጣው ያ ቀን በእነሱም ላይ በድንገት ሊመጣባቸው ይችላል። ስለዚህ ከሚመጣው ክፉ ነገር ለማምለጥ እንዲችሉና በእሱ በአዳኛቸው ፊት ለዘላለም ለመቆም እንዲችሉ ዘወትር እየጸለዩ መትጋት ይገባቸዋል።

ከመንግስተ ሞሚቀሩ እነማን ናቸውና?

ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፤ የሰው ልጅ በማታስቡት ሰዓት ይመጣልና[43]

ለተወሰኑ ዓመታት በየሳምንቱ ከጥቂት አዛውንቶች ጋር የወንጌል ቃል አብረን እናጠና ነበር። ታዲያ ሁልጊዜ ስለጌታ መምጣት፣ ስለታላቁ መከራና ስለንጥቀት ከተነሣ፣ አንደኛዋ ሴት ምኞታቸው ሰማዕት ሆኖ ማለፍ እንደሆነ ሲገልጡ፣ ሌላኛዋ ሴት ደግሞ መነጠቅ ብቻ እንደሚፈልጉ ሳይገልጡ አያልፉም። እኔም፣ መነጠቅም ሆነ በታላቁ መከራ ውስጥ ማለፍ የምርጫ ጉዳይ ባለመሆኑ በእነርሱ ፍላጎት የሚወሰን እንዳልሆነ ላስረዳቸው እሞክራለሁ። ዳሩ ግን ከብዙ ጊዜ በኋላ ያ ርዕስ በአጋጣሚ እንደገና ሲነሣ፣ ሁለቱም በዚያው አቋማቸው እንደ ጸኑ አገኛቸዋለሁ።

ምንም እንኳ፣ መነጠቅም ሆነ በታላቁ መከራ ውስጥ ማለፍ የእኛ ምርጫ ባይሆንም ከጌታ ጋር ለመኖር ውሳኔው ግን በእጃችን ነው። ደግሞም አንድ አማኝ *«ክቡተ ክርስቲያን ወገን ሳይነጠቁ የሚቀሩ ሰዎች ይኖሩ ይሆን?»* በማለት አላብ ይገባው ይሆናል። ምናልባት የዚህ ሰው ጥያቄ ስለራሱ ከሆነ፣ ከዚህች ሰዓት ጀምሮ ሕይወቱን በጌታ ፊት በመመርመር በቃሉ መሠረት ማድረግ የሚጠበቅበትን ማድረግ ብቻ ነው የሚገባው። ሆኖም በሚመጣው ጊዜ ሳይነጠቁ የሚቀሩ አንዳንድ ሰዎች እንዳሉ መጠራጠር የለበትም።

ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያኑን ወደራሱ ሲነጥቅ በምድር እንደሚቀሩ አስቀድሞ ከታወቁት መኻል ዋነኞቹ የማያምኑ ሰዎች ናቸው። ከዚህ በተለየ ግን በጌታ አምነናል ብለው ሲያበቁ፣ በትምህርቱ የማይሄዱ፣ እውነተኛውን ሕይወት ቸል ያሉ ወይም ጨርሰው የካዱ ሰዎች ጉዳይ በጥንቃቄ ሊመረመር የሚገባው ነው። ደግሞም የእነዚህ ሰዎች

[43] ማቴ 24:44።

ዕድል ካላመኑ ሰዎች ጋር የሚሆን መስሎ ይታያል። እንዲያውም የእግዚአብሔር ቁጣ በእነርሱ ላይ እንደሚበረታ ነው የሚጠበቀው።[44]

እነዚህ ሰዎች፣ ጌታ ስለመጨረሻው ዘመን ሲያስተምር የጠቀሳቸውን ሰነፍ ልጃገረዶች ይመስላሉ። በኢየሱስ ምሳሌ መሠረት አስሩም ልጃገረዶች የሙሽራውን መምጣት የሚጠባበቁ ቆነጃጅት ሲሆኑ፣ አምስቱ ብልሆች፣ አምስቱ ሰነፎች ነበሩ። ምንም እንኳ ሙሽራው ከታሰበው በላይ እጅግ ቢዘገይም፣ ብልሆቹ ግን መብራታቸውን አብርተው፣ ለመጠባበቂያም የሚሆን ዘይት ሞልተው መምጣቱን ይጠባበቁ ነበር፤ ሰነፎቹ ልጃገረዶች ግን በቂ የመጠባበቂያ ዘይት ሳይዙ ተዘናጉ። በእኩለ ሌሊትም *«ሙሽራው እየመጣ ነው፣ ወጥታችሁ ተቀበሉት»* የሚል ኹካታ ተሰማ። በዚህ ጊዜ ቆነጃጅቶቹ ሁሉ ተነሥተው መብራታቸውን አብርተው ሙሽራውን ሊቀበሉ ተጣደፉ። ሰነፎቹም በቂ ዘይት ስላልነበራቸው ወደ ብልሆቹ ቆነጃጅት ቀርበው *«መብራታችን ሊጠፋብን ስለሆነ አባካችሁ ከዘይታችሁ አካፍሉን»* አሏቸው፤ ጎበዞቹ ቆነጃጅት ግን *«ያለን ዘይት ለእኛና ለእናንተ ላይበቃ ስለሚችል፣ ሂዳችሁ ከሻጮች ለራሳችሁ ግዙ»* አሏቸው። እነርሱም ዘይት ሊገዙ ሄዱ። ዳሩ ግን በዚህ መኻል ሙሽራው ደረሰ፤ ተዘጋጅተው የነበሩት ልጃገረዶችም አብረው ወደ ሠርጉ ግብዣ ገቡ፤ በሩም ተዘጋ። ዘግየት ብለው ዝንጉዎቹ ልጃገረዶች መጥተው *«ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ አባክህን ክፈትልን»* አሉት። እሱም መልሶ *«እውነት እላችኋለሁ፣ አላውቃችሁም»* አላቸው። ኢየሱስም ለደቀ መዛሙርቱ ይኼን ምሳሌ ከመሰለ በኋላ «ቀኒቷንና ሰዓቲቱን አታውቁምና አንግዲህ ንቁ»[45] አላቸው።

[44] ዕብ6:4-6። ዕብ10:26-29። የአውነትን ዕውቀት ከተቀበልን በኋላ ሆን ብለን በኀጢአት ጸንተን ብንመሳሰስ ከአንግዲህ ሰኀጢአት የሚሆን ሌላ መሥዋዕት አይኖርም፤ የሚቀረው ግን የሚያስፈራ ፍርድና የአግዚአብሔርን ጠላቶች የሚበላ ብርቱ አሳት መጠበቅ ብቻ ነው። የሙሴን ሕግ የናቀ ማንኛውም ሰው ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ከመሰከሩበት ያለ ምሕረት ይገደል ነበር ታዲያ የአግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ተራ ነገር የቆጠረ የጸጋንም መንፈስ ያከፋፋ እንደ ምን ያለ የባሰ ቅጣት ይገባው ይመስሰኝኃል?

[45] ማቴ 25:13

የክርስቶስ
የፍርድ ወንበር

46

ሰማይና በውስጧ የምትኖሩ ደስ ይበላችሁ! ምድርና ባሕር ግን ወየውላችሁ!»

የበጉ ሠርግ ስለደረሰና የእርሱም ሙሽራ ስለተዘጋጀች ደስ ይበለን፡፡ ደስታም አናድርግ፣ አናክብረውም

ቤተ ክርስቲያን ወደ ሰማይ ተነጥቃ ጌታን በአየር ላይ ከተገናኘች በኋላ፣ በሰማይና በምድር ፍጹም ተቃራኒ የሆኑ የኑሮ ሥርዓቶች ይከሰታሉ፡፡ በወቅቱ፣ ተነጥቀው በሰማይ የተገኙ አማኞች በበጉ ሠርግ በታላቅ ደስታ ውስጥ ሲያልፉ፣ በዚያችው ሰዓት ደግሞ በምድር ታላቁ መከራ ይሆናል፡፡ ታዲያ ያ ጊዜ ዘንዶው፣ ከባሕር የሚወጣው አውሬና ከምድር የሚወጣው ሌላኛው አውሬ፣ አንድም ሦስትም ሆነው ምድርን የሚያተራምሷት ዘመን በመሆኑ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ምድር ለኑሮ አስቸጋሪና የስቃይ ስፍራ ትሆናለች፡፡

ቤተ ክርስቲያን ከተነጠቀች በኋላ፣ በአየር ላይ ወደሚጠባበቃት ጌታ ስትደርስ፣ የዚያን ጊዜ በቤተ ክርስቲያንና በክርስቶስ መኻል ይፋዊ ጋብቻ ይፈጸማል፡፡[47] እስከዚያው ቀን ድረስ ግን፣ ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያን በእጮኝነት መቆየታቸው የግድ ነው፡፡ ጳውሎስ የቆሮንቶስ አማኞችን «በእግዚአብሔር ቅናት አቀናሳችኋለሁ፤ አናንተን፣ አንደ ንጽሕት ድንግል ለክርስቶስ በማቅረብ ለአንድ ባል አጭቻችኋለሁ»ማለቱ በእርግጥ አሁን ላለችው ቤተ ክርስቲያን ፍጹም ተመጣጣኝ ገለጣ ሲሆን፣ እርስዋም ከጌታዋ ጋር ሙሉ ጋብቻዋ እስክትፈጽም ድረስ እንዴት ባለ ሥርዓት መኖር እንዳለባት የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ በእጮኝነት ጊዜ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ እንዳይሆንባት እጅግ ልትጠነቀቅ እንዲሁም ከብዙ ነገር ልትታቀብ ይገባታል፡፡

[46] ራእ12:12፡፡
[47] ራእ19:7፡፡ 2ኛቆር11:2፡፡

ከቤተ ክርስቲያን ንጥቀት በኋላ በሰማይ ከሚሆኑ ዋና ዋና ነገሮች መኻል ተነጥቀው በሰማይ የተገኙ አማኞች በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት የሚቀርቡበት ሥርዓት፣ በዋነኝነት ሊጠቀስ የሚገባው ነው፡፡ ሆኖም ወደፊት ስለሚሆኑ የፍርድ ሥርዓቶች በተመለከተ ከ«ክርስቶስ የፍርድ ወንበር» ሌላ ሁለት የተለዩ የፍርድ ጊዜአት እንደሚኖሩ በቅዱሱ መጽሐፍ ተገልጧል፡፡ እነሱም «የአሕዛብ ፍርድ» እና «የታላቁ የነጭ ዙፋን ፍርድ» የሚባሉ ናቸው፡፡ በዚሁ መሠረት ከታላቁ መከራ በኋላ ለአይሁዳውያን እንዳደረጉት ቸርነት መጠን በአሕዛብ ላይ የሚሆነው የፍርድ ሥርዓት «የአሕዛብ ፍርድ» ሲባል፣ ከሺው ዓመት ፍጻሜ በኋላ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ በምድር የኖሩ ሙታን ሁሉ ተቀስቅሰው በእግዚአብሔር ፊት ለፍርድ የሚቀርቡበት ሥርዓት ደግሞ «የታላቁ የነጭ ዙፋን ፍርድ» ይሰኛል፡፡[48]

እነዚህም ወደ ዘላለም ፍርድ፣ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ፡፡

ከዚህ በኋላ ታላቅ ነጭ ዙፋንና በእርሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ ምድርና ሰማይ ከፊቱ ሸሹም፤ ስፍራም አልተገኘላቸውም፡፡

ሙታንን ታላላቆችንና ታናናሾችን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ፤ መጻሕፍትም ተከፈቱ፤ ሌላም መጽሐፍ እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ተከፈተ፤ ሙታንም በመጻሕፍቱ ተጽፎ በተገኘው መሠረት እንደ ሥራቸው መጠን ተፈረደባቸው፤ ባሕርም በውስጡ የነበሩትን ሙታን ሰጠ፤ ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ውስጥ የነበሩትን ሙታን ሰጡ፡፡ እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ተፈረደበት፡፡ ከዚያም በኋላ ሞትና ሲኦል ወደ እሳት ባሕር ተጣሉ፤ የእሳቱ ባሕር ሁለተኛው ሞት ነው፡፡ ስሙ በሕይወት መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘ ሁሉ ወደ እሳት ባሕር ተጣለ፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ውጤቱ ምንም ይሁን ምን፣ ከሁሉ ቀድሞ በሚሆነው የፍርድ ሥርዓት ማለትም «በክርስቶስ የፍርድ ወንበር» ፊት መቅረብ በራሱ ለአማኞች ትልቅ ዕድል ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ የፍርድ ሥርዓት የሚያልፉ ሰዎች፣ የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት ተቀብለው በምድር የኖሩ ሲሆኑ፣ ከተነጠቁ በኋላ ጌታን በአየር

[48] ማቴ25:31-46፡፡ ራእ19:11-15፡፡

የሚቀበሉ በመሆናቸው፣ እሱን ፊት ለፊት ለማየት ዕድል ያገኛሉና ነው። ሆኖም ግን አማኞች በዚህ የፍርድ ወንበር ፊት በቀረቡ ጊዜ በምድር ሳሉ፣ በእምነታቸው በኩል ስላደረጉት ወይም ስላላደረጉት ነገር አክሊልና ሽልማቶችን ያገኛሉ ወይም ያጣሉ። የአንዱ ኮከብ ክብር ከአንዱ እንደሚለይ፣ በዚያን ጊዜ የአማኞች ክብርም ሆነ ሽልማት እኩል አይሆንም።

ከቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በኋላ፣ በሰማይ በበጉ ሰርግ የሚታደሙ አማኞች፣ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ሲቆሙ የሚጠየቁባቸውን ምክንያቶች ካወቁ፣ በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ እንዴት ባለ ሥርዓት መኖር እንዳለባቸው ግንዛቤ ይጨብጣሉና ከዚሁ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ማንሣት ተገቢነት አለው ብዬ አስባለሁ። ለመሆኑ አንድ አማኝ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ሲቀርብ የሚጠየቅበት ጉዳይ ምን፣ ይሆን?

የአማኝ
የአምልኮ ሥርዓት

አንተስ በወንድምህ ሳይ ስለምን ትፈርዳለህ?
ሁላችንም የክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት አንቆማለንና[49]

እያንዳንዱ ሰው፣ የጌታ ኢየሱስን አዳኝነት ከተቀበለ በኋላ የተለያዩ ሥርዓቶች በመፈጸም በእሱ ፊት ለአምልኮ መቅረቡ የተለመደ ነው። ደግሞም የአምልኮው ሥርዓት ወይም ልማድ ሌላው ከሚያቀርበው የላቀና የተሻለ መስሉ እየተሰማው «*ይኼ ከሁሉም ይልቅ ጌታን ደስ ያሰኝዋል*» ብሎ ሊያስብ ወይም ሊናገር ይችላል። ሆኖም ማንም በምድር ሲኖር ላቀረበው ማናቸውም ዓይነት አምልኮ አንድ ቀን ዋጋ እንደሚቀበልበት መርሳት የለበትም። ይኼም እንደ መብላትና መጠጣት፣ እንዲሁም የቀናት አከባበር በማስመልከት የሚደረጉ ቀኖናዊ የአምልኮ ልማዶችን ጭምር የሚመለከት ነው። ለምሳሌ አንዳንድ ሰው አትክልት ብቻ የሚበላው፣ ሥጋ ባለመብላቱ ጌታን የበለጠ ደስ የሚያሰኝ ወይም የሚያከብር መስሎ ስለሚሰማው ሊሆን ይችላል። ሌላው ግን ሥጋም ሆነ አትክልት ቢበላ በአምልኮው ላይ ምንም የሚጨምርለትም ሆነ የሚቀንስለት እንደሌለ አድርጎ ያስባል። በሌላ በኩል አንዳንዱ አማኝ ከቀናት መኻል መርጦ «*ይኼኛው ቀን የተለየ በመሆኑ በዚህ ቀን ጌታ የበለጠ ይከብራል*» ብሎ ሊያስብ፣ ሌላው ደግሞ ቀናት ሁሉ እኩል እንደሆኑ አድርጎ ሊያምን ይችላል። በመሆኑም እነዚህ የተለያየ ዕይታ ያላቸው ሰዎች፣ መሠረታዊውን የደንነት አሳብ እስካላፋለሱ ድረስ በአምልኮ ሥርዓታቸው ተቀባይነት ማግኘት ወይም ማጣት የመጨረሻውን ብያኔ የሚሰጠው ባለቤቱ ብቻ እንደ ሆነ መዘንጋት የለብንም። ደግሞም በእነዚህ ጉዳዮች ማንም በማንም ላይ እንዲፈርድ ሥልጣን ያልተሰጠው ከመሆኑም ሌላ፣ የማንንም ልብ መዝኖ የሚፈርድ ጌታ ብቻ በመሆኑ፣ እስከዚያ ቀን ድረስ

[49] ሮሜ14:11።

ታግሶ መጠበቅ ነው የሚሻለው። እርሱም ሰዎች፣ ምን ሲያደርጉ እንደኖሩ ሳይሆን፣ ለምን ሲያደርጉ እንደነበር ወይም የልባቸው አሳብና ተነሣሽቶት ምን እንደነበር ያውቃል። ስለዚህ በተለይ ሥርዓታዊ በሆኑ ጉዳዮች እስከ ፍርድ ቀን ድረስ፣ ማንም ሰው *«ትክክሉ ወይም አግዚአብሔር የሚቀበለው የአኔን የአምልኮ ሥርዓት ብቻ ነው»* ብሎ ራሱን በማዋደድ፣ የሌላውን አምልኮ ማጣጣልም ሆነ በሌላው መፍረድ አይገባውም። ምክንያቱም ሁሉም ሰው በምድር ሲፈጽመው ለኖረው አምልኮ፣ አንድ ቀን በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ይቆማልና ነው። ይሁን እንጂ ማንኛውም የአምልኮ ሥርዓት በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእውነትና በመንፈስ ካልቀረበ፣ ፍጹም እንደሌለው አያጠያይቅም።

አንድ ቀን ኢየሱስ፣ ይሁዳን ትቶ ወደ ገሊላ ሲያቀና በሳምራውያን አውራጃ መሻል ያልፍ ነበር፤ ስድስት ሰዓት ሲሆን «ሲካር» በሚባለው የያዕቆብ የውኃ ጉዳጓድ አጠገብ አረፍ አለ። አንዲት ሳምራዊት ሴት፣ ውኃ ልትቀዳ መጣች፤ ይህቺ ሴት ብዙ ችግሮች የነበሩባት ቢሆንም ዋና ጥያቄዋ ግን የአምልኮ ነበር፣ ወገኖቿ ሳምራውያን *«አግዚአብሔር የሚቀበለው አምልኮ ከገሪዛን የሚቀርብለትን ብቻ ነው»* ሲሉ፣ አይሁዳውያን ደግሞ *«ለአግዚአብሔር የሚቀርብ ስግደት ወይም አምልኮ ከኢየሩሳሌም ሊሆን ይገባዋል»* ብለው ያምኑ ነበር። ሴቲቱም ለእግዚአብሔር አምልኮና ስግደትን ማቅረብን እጅግ ብትመኝም፣ ትክክለኛውን ስፍራ ለማግኘት ግን አልቻለችም። ስለዚህም ኢየሱስን እንደ ነብይ በቆጠረችው ጊዜ፣ ግራ መጋባቷን አቅርባለት ነበር። ኢየሱስ በዚያን ቀን ለእሷ የመለሰላት መልስ ግን ለእሷ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን በእውነት ለማምለክ ለሚሹ ሁሉ የሚሆን ነው።[50]

እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም
በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።

[50] ዮሐ.4:24

የእማኝ
ሕይወትና ሥራ

መልካም ቢሆን ወይም ክፋ አንዳደረገ፣ አያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን
በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባል[51]

ማንም አማኝ፣ በጌታ ከሆነ በኋላ በሥጋው ለፈጸመው ማናቸውም ተግባር በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ይቀርባል። ይኼን አትርሱ፣ እያንዳንዱ አማኝ የራሱን ሰውነት ከአምላኩ በአደራ ተቀብሎታል እንጂ፣ የራሱ አይደለም። ጌታም በራሱ ፈቃድ የአማኙን ሰውነት ቤተ መቅደሱ አድርጎታል። አማኙ ደግሞ ይኼን ቤተ መቅደስ እንዲጠብቀውና እንዲንከባከበው አደራ ተጥሎበታል። አማኙ ግን፣ ብልቶቹን የዐመፃ ዕቃ አድርጎ ቢጠቀምና ቤተ መቅደሱን ቢያቆሽሽ ወይም ጨርሶ ቢያፈርስ፣ ስለዚህ ተግባሩ አንድ ቀን በጌታ ፊት ይጠየቅበታል።[52] ደግሞም፣ በሥጋው መልካም ካደረገ፣ ስላደረገው መልካም ነገር ከጌታው ዘንድ ብድራቱንና ሽልማቱን ይቀበላል።

እንግዲህ ይኼ ሁሉ አንድ ቀን በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ወይም ዙፋን ፊት በቀረብን ጊዜ የሚከናወን ነገር ነው። እስከዚያው ድረስ ግን ሰው ሁሉ ብልቶቹን የክብር እንጂ፣ የዐመፃ ዕቃ አድርጎ እንዳይጠቀም ጠንቃቃ መሆን አለበት። አማኝ፣ በንቃትና በጥንቃቄ መኖር ያለበት ያ ቀን ሲመጣ ላለመቆጨትና ላለማዘን ነው። የዚያን ቀን የሚሆነው ሽልማት እጅግ ደስ እንደሚያሰኝ ሁሉ፣ በትንሽ ስህተት ምክንያት የከበረ ዋጋን ማጣት እጅግ የሚያስቆጭና የሚያሳዝን እንደሆነ ከአሁኑ ጥርት ብሎ ይታያል።

[51] 2ኛቆሮ5:10።
[52] 1ኛቆሮ3:16፤17።

የአማኞች ኃጣፊር

ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ፣ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል። ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህ፤ ከቃህ የተነሣ ትኮነናለህ።[53]

ብዙ ጊዜ አንደበታችን እንዳመጣልን እንናገራለን፣ አንዳንድ ጊዜም በመሰለኝ ስሜት በሰዎች ላይ የፈለግነውን አስተያየት እንሰጣለን፣ ሌላም ጊዜ አፋችንን በከንቱና በማይረቡ ቃላት እንከፍታለን። ከምሬትና ከሐዘን ወይም በቁጣ ተነሣስተን *«ይህ እንዲህ ነው፣ ያም እንዲያ ነው»* ማለታችን የተለመደ ነገር ስለሆነ ስህተት እንደሠራን እንኳ ያን ያህል ላይሰማን ይችላል። ግን ለመሆኑ ስለምንናገራት ስለእያንዳንዷ ቃል በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት በቀረብን ጊዜ መልስ እንደምንሰጥ ምን ያህል እናስተውላለን? በእርግጥ በዚያ ቀን የምንቆመው ዓይኖቹ እንደ እሳት ነበልባል በሆኑና ልብንና ኩላሊትን ጠልቆ መመርመር በሚችል አምላክ ፊት ነው፤ እርሱን በአንደበት ቅልጥፍና ወይም በንግግር ችሎታ ልንረታው አንችልም።

በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ ስለምን ጉዳይ ምን እንደምንናገር ብንጠነቀቅ ይበጀናል። ለምሳሌ በመግቢው ላይ በተጠቀሰው ክፍል ኢየሱስ አንድ በአጋንንት ተይዞ ማየትና መናገር የማይችልን ሰው ከፈወሰ በኋላ ከሆነው ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው። በወቅቱ ኢየሱስ ስለፈወሰው፣ ሰውየው ማየትና መናገር ችሎ ነበር። ታዲያ ይኼን ያዩ አንዳንድ ሰዎች ተደንቀው *«ይህ ሰው የዳዊት ልጅ ይሆን?»* ተባባሉ። ፈሪሳውያን ግን *«አጋንንትን የሚያወጣው በአጋንንት አለቃ ወይም በብዔልዜቡል ነው»* በማለት፣ በድፍረት አስተያየታቸውን ይሰጡ ነበር። በዚህን ጊዜ ጌታ፣ ለፈሪሳውያኑና በዚያ ለነበሩት ሁሉ አስቀድሞ ስለፈውስና የአጋንንት አስተዳደር ጥልቅ ትምህርት ካስተማረ በኋላ «ዛፍ ሁሉ በፍሬው ስለሚታወቅ፣ መልካም ፍሬ አንድታገኝ መልካም ዛፍ ይኑራችሁ፤ መጥፎ ዛፍ ቢኖራችሁ ግን መጥፎ ፍሬ ታገኛላችሁ። አናንት የእፉኝት ልጆች፣ አናንተ ክፋዎች

[53] ማቴ12:36።

ስትሆኑ መልካም ነገር መናገር አንዴት ትችላላችሁ? በልብ ውስጥ የሞላውን አንደበት ይናገረዋልና። መልካም ሰው በልቡ ካከማቸው መልካም ነገር፣ በጎ ነገር ያወጣል፤ ክፋ ሰው በልቡ ካከማቸው ክፋ ነገር፣ መጥፎ ነገር ያወጣል» በማለት የሰዎቹ ችግር ከልባቸው ውስጥ ካለው ክፉትና አለማመን የሚመነጭ እንደሆነ አስገንዘባቸው። በተጨማሪም ይህ የአንደበት ችግር፣ ጊዜአዊ ብቻ ሳይሆን ዘለቄታዊ መዘዝ እንዳለው አሳሰባቸው። ይኼም ሰዎች፣ ከተናገሩት አንዳር ሊፈረድላቸው ወይም ሊፈረድባቸው እንደሚችል የሚያስገነዝብ ነው። ከዚህ አንጻር መቼም ቢሆን፣ ባልገባን ወይም ባልተገለጠልን ነገር በድፍረት አስተያየት ከመስጠት መቆጠብ መልካም ነው።

በእርግጥ ካነሳነው ጭብጥ አንጻር፣ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት የሚቀርቡ ሰዎች፣ አስቀድመው የዳኑ በመሆናቸው እነዚህ ነገሮች ከመዳን ጋር በቀጥታ የተያያዙ ላይሆኑ ይችላሉ። ሆኖም በጌታ ፊት ቀርቦ ሽልማትና አክሊል አለማግኘት በራሱ ታላቅ ጸጸት እንደ ሆነ ማሰብ ብልህነት ነው። በሌላ በኩል ያየነው እንደሆነ ግን ሰዎች ወደ ዘላለማዊው ድነት የሚገቡት ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ተግባራትን በመከወናቸው እንደሆነ እንረዳለን። ለምሳሌ በአንደበት የሚነገር ነገር ከመዳን ጋር ያለውን ትስስር በተመለከተ ጳውሎስ ለሮም ሰዎች እንዲህ ብሏቸው እንደነበር እናስተውላለ፡፡[54]

በአፍህ በልብህም ሆኖ ቃሉ ቀርቦልሃል፤ ይህም የምንሰብከው የእምነት ቃል ነው። ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ ሰው በልቡ ያምና ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና። መጽሐፉ በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም ይላልና።

ሆኖም እነዚህ ጉዳዮች ከመዳን ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የላቸውም ብሎ ቸል ማለት ወይም እንደ ቀላል ነገር መቁጠር አደጋው ብዙ ነው። በመሆኑም እያንዳንዱ ሰው ዘወትር በሰማይ ጽኑ መሠረት እንዳለው ሊያረጋግጥ ይገባል። ቀጥሎ ያለውን አሳብ ልብ ይሏል።

[54] ሮሜ10:8-11።

ጽኁፍ መመሪያ

...ማንም ግን በዚህ መሠረት ሳይ በወርቅ ቢሆን በብርም፣ በከበረ ድንጋይም፣ በአንጨትም በሳርም ወይም በአገዳ ቢያንጽ፣ የአያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል። በእሳት ስለሚገለጥ ያ ቀን ያሳያልና፣ የአያንዳንዱም ሥራ አንዲት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋል። ማንም በእርሱ ሳይ ያነጸው ሥራ ቢጸናስት ደመወዙን ይቀበላል። የማንም ሥራ የተቃጠለበት ቢሆን ይገዳበታል፤ እርሱ ራሱ ግን ይድናል፤ ነገር ግን በእሳት አንደሚድን ይሆናል። [55]

ከላይ የተዘረዘሩት ፍርዶች፣ አማኞች በመጨረሻው ዘመን ባለው የመጀመሪያ የፍርድ ሥርዓት፣ ማለትም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት በቀረቡ ጊዜ የሚሆኑ ናቸው። ምንም እንኳ የአማኙ መሠረት ክርስቶስ ቢሆንም በዚያ መሠረት ላይ የሚገነባበት ቁስ፣ የፍርድ ምክንያት መሆኑ አይቀርም። ስለዚህ እያንዳንዱ አማኝ ልብ ሊለው የሚገባ አንድ ነገር በዕለታዊ ምልልሱ እንዴት ባለ ቁስ ሕይወቱን እየገነባ እንደሆነ ነው። በእርግጥ ዛሬ ላይ ሆነው ሲመለከቱት ነገሩ ያን ያህል የማያሳስብና ቀላል መስሎ ቢታይም በመጨረሻው ቀን የሚገኘው ውጤት አማኙን ከደኅንነት ባለፈ የተዘጋጀለትን አክሊልና ሽልማት ሊያሳጣው እንደሚችል ግን መርሳት የለበትም። በዚያ ቀን እያንዳንዳችን ለዚህ ምድር ያለን አስተሳሰብና የሕይወት ፍልስፍና ሁሉ በእሳት ውስጥ ያልፋል።

እንግዲህ፣ የክርስቶስን የፍርድ ወንበር አስፈሪ የሚያደርገው ይኸው ነው። እያንዳንዳችን ዛሬ፣ መልካም መሠረት በሆነው በክርስቶስ ትምህርት፣ ሕይወታችንን እንድናንጽ ዕድል ተሰጥቶናል። ዳሩ ግን ለማነጽ የመረጥነው ግብአት ማንነታችንን እንደሚወስነው መዘንጋት የለብንም። አንድ ቀንም ለዚሁ የሚሆን ደመወዝ ወይም ዋጋ ከጌታ እጅ እንቀበላለን። ደግሞም የእያንዳንዳችን ሥራ በእሳት ውስጥ እንዲያልፍ ስለሚደረግ፣ ማንም ስለሥራው ለማስረዳት ዕድል እንኳ

[55] ፣ኖቆር3:12-17።

አያገኝም። እናም ሥራው በእሳት ውስጥ አልፎ የጸናለት፣ በሠራው ሥራ ሽልማትን ሲያገኝ፣ የተቃጠለበት ግን እጅግ ያዝናል።

እርግጥ ነው፣ ዛሬ ላይ ሆነን፣ በእሳት ባለፈ ጊዜ የትኛው ሥራችን እንደሚጸናልን መናገር ባንችልም፣ ቃሉና መንፈሱ በልባችን በቀረቡ ሰዓት ግን እውነቱን ለመረዳት አያስቸግረንም። በዚሁ መሠረት ለገንዘብ፣ ለዝና ወይም ከንቱ ውዳሴን ፈልገን እንዳደረግነው ወይም ለራሱ ለክርስቶስ ክብር እንዲሆን ብለን ያደረግነው እንደ ሆነ፣ . . . ብቻ ሁሉም ነገር በእሳት ተፈትኖ ይታወቃል። ዛሬ በሰው ፊት ስለ ጥራቱ በግራም በቀኝም ብዙ የተባለለት ነገር ሁሉ፣ እውነተኛ የጥራት ልኩ የሚታወቀው፣ ወደፊት በእሳት ውስጥ ባለፈ ጊዜ ነው። ምናልባትም የዚህን ዓለም የጥራት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለማግኘት የደከሙት ድካምና የለፉት ልፋት፣ ለዚያኛው ምንም እንደማይጠቅማቸው ሲያውቁ፣ ቀኑ ለብዙዎች የቁጭትና የጸጸት ሊሆን እንደ ሚችል ይጠበቃል። አዎ! የኖርነው ኑሮ፣ የሕይወት ዘይቤአችን፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለኅብረትና ለፍቅር የነበረን ዝንባሌና ፍላጎት በእሳቱ ውስጥ ባለፈ ጊዜ የጥራት ደረጃና ልኩ በእርግጥ ይታወቃል።

መቼም ቆም ብለው ሲያዩት፣ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት መገኘት አስደሳችም፣ አስፈሪም ነገር ነው። አስደሳችነቱ፣ እዚያ የሚገኙ ሰዎች በክርስቶስ ኢየሱስ የጽድቅ ሥራ ብቻ የዳኑ ስለሆኑ፣ የዘላለም ሕይወታቸው ምንም ጥያቄ ውስጥ ስለማይገባ ሲሆን፣ አስፈሪነቱም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ቀርበው የሚመዘኑበት በመሆኑ ነው። እንዲያም ሆኖ በዚያ ተገኝቶ ሥራው የተቃጠለበትም ቢሆን ሽልማቱ ይቀርበታል እንጂ፣ እርሱ ራሱ ግን ይድናል። ይሁን እንጂ የሚድነው በእሳት ውስጥ በጭንቅ እንደሚያልፍ ሆኖ ነው።

አክሊሎችና ሽልማቶች

56

አነሆ በቶሎ እመጣለሁ፤ ማንም አክሊልህን አንዳያጠፋብህ ያለህን አጽንተህ ያዝ።

አማኞች በመጨረሻው ቀን የሚቀበሉትን ሽልማት በመጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ስፍራዎች «አክሊል» እየተባለ ይጠራል። በዚሁ መሠረት ወደፊት በሚሆን አንድ ዘመን አማኞች ለልዩ ልዩ ተግባሮቻቸው የሚመጥን አክሊልንና ሽልማቶችን ከአምላካቸው እጅ እንደሚቀበሉ ተገልጧል። እንዲያውም ቤተ ክርስቲያን ከተነጠቀች በኋላ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት መቅረብን አስደሳች ከሚያደርጉት ምክንያቶች አንዱ፣ አማኞች እንደየሥራቸው ተመዝነው የሚሰጣቸው አክሊልና ሽልማት ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ በክርስትናችን ምክንያት በምድር የከፈልነው ዋጋ፣ የጽድቅና የቅድስና ኑሮአችን በከንቱ እንደማይቀር ማሰብ በራሱ ምንኛ የሚያስደስት ነገር ነው። ስለዚህም ዘወትር የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል በማስተማር፣ በሥራው የማያሳፍርና የማያፍር ሠራተኛ በመሆን፣ ፈተናን ሁሉ ማለፋችን በእግዚአብሔር ፊት እንዲረጋገጥ፣ በሁሉ ነገር ትጋታችንን ማሳየት አለብን።[57] ይሁንና በትናንት ትጋታችን ዛሬ ካልኖርንበት ሽልማት ለማግኘት ዋስትና ሊሆነን አይችልምና አክሊላችንን ማንም እንዳይወስድብን ዘወትር መጠንቀቅ አለብን።

በመሠረቱ እያንዳንዱ ሰው የሚጠየቀው፣ ከጌታ ዘንድ እንደተሰጠው ወይም እንደተቀበለው መክሊት ያህል ነው። የጌታ ብቻ በሚሆን በዚያ ቀን፣ ሁሉም እንደ ታማኝነቱ መጠን ተመዝኖ ዋጋውን ከእጁ ይቀበላል። የእያንዳንዱ ሰው አገልግሎትም ሆነ ኑሮ፣ በክርስቶስ የቃሉ ሚዛን ተመዝኖ ሽልማትና አክሊል ለሚገባው እንዲሁ ይሰጠ

56 ራእ3፡11።
57 2ኛጢሞ2፡15። እንደማያፍርና የእውነትን ቃል በትክክል እንደሚያስረዳ የተመሰከረለት ሠሪተኛ ራስህን በእግዚአብሔር ፊት ለታቀርብ ትጋ።

ዋል። ይኼም ማለት ሰው በሕይወት ዘመኑ ያስተማረው ትምህርት፣ የዘመራቸው ዝማሬዎች፣ የተነበያቸው ትንቢቶች፣ የሰጣቸውና የተቀበላቸው ይቅርታዎች ሁሉ፣ አንድ ቀን ዋጋቸው ምን ያህል እንደ ሆነ ይታያል ማለት ነው። የዚያኑ ያህል ሥራችንና አገልግሎታችን ዘላለምን ማዕከል ያደረገ ሆኖ ካልተገኘ ፍሬው በምድር ላይ ብቻ የሚታፈስ ሆኖ ይቀራል።[58]

ሆኖም እንዲህ ዓይነቱን ጊዜ ፈርተን «አርፌ እቀመጣለሁ» ብንል እንኳ ከተጠያቂነት የምናመልጥ አይደለንም። ኢየሱስም ስለዚሁ ጉዳይ ለደቀ መዛሙርቱ ባስረዳ ጊዜ የሚመስጥ ምሳሌ ተናግሯል። በምሳሌውም፣ አንድ ሩቅ አገር ለመሄድ የፈለገ ሰው፣ በቤቱ ያሉ አገልጋዮቹን ሁሉ ጠርቶ ለእያንዳንዳቸው የተለያየ መጠን ያለው መክሊት ከሰጣቸው በኋላ፣ ሲመጣ እንደተሳሰባቸው የሚተርክ ነው። ሰዎቹም ከጌታቸው እጅ የተቀበሉትን መክሊት ከነትርፉ ማስረከብ ይጠበቅባቸው ነበር። በምሳሌው ላይ የተጠቀሱት ሦስት ሰዎች፣ እያንዳንዳቸው የተለያየ መጠን ያለው መክሊት የተቀበሉ ሲሆን፣ የመጀመሪያው፣ አምስት፣ ሁለተኛው፣ ሁለት፣ ሦስተኛው ደግሞ አንድ መክሊት በእጃቸው ገብቶ ነበር። የአገልጋዮቹ ጌታ የሆነው ሰው ከሄደበት ተመልሶ መጥቶ ሒሳቡን ሲተሳሰብ፣ አምስትና ሁለት መክሊት የወሰዱት ሰዎች በየተራ ቀርበው ከነትርፉ ሲያስረክቡ፣ አንድ መክሊት የተቀበለው ግን «ጌታ ሆይ ካልዘራህበት የምታጭድ ካልበተንህበት የምትሰበስብ መሆንህን አውቃለሁ፤ ስለዚህ ፈራሁም፤ ሄጄም መክሊትህን በምድር ቀበርኩት» በማለቱ፣ ጌታው ተቆጥቶ «አንተ ክፉና ሀኬተኛ ባሪያ ካልዘራህበት አንዳጭድ ካልበተንኩበትም አንድሰበስብ ታውቃለህን? ስለዚህ ገንዘቤን ለሰዋጮች አደራ ልትሰጥ በተገባ ነበር፤ እኔም ከትርፉ ጋር አመጣድ ነበር» አለው።[59]

58 ማቴ7:22፤23። በዚያ ቀን ብዙዎች፣ ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህ አጋንንት አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ታምራት አላደረግንምን? ይሉኛል። በዚያ ጊዜ፣ ከቶ አላወቅኋችሁም፤ አናንት ከፋዎች፣ ከእኔ ራቁ ብዬ በግልጽ እነግራቸዋለሁ፡
59 ማቴ25:14-30።

በመሆኑም ማናችንም ብንሆን በምድር የተሰጠን አገልግሎት ምንም ዓይነት ሰበብና ምክንያት ሳያደናቅፈው እየተጓዘ ስለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ይገባናል። አንዳንድ ጊዜ የምንጓዝበት ጎዳና፣ ሕይወታችንን የሚያስከፍለን ቢሆን እንኳ ወደ ፊት ከመጓዝ በቀር ሌላ ዕድል የሌለበት ሕይወት እንደመረጥን ልንረሳ አይገባም። እስከመጨረሻው የጸናም ከጌታው እጅ አክሊልና ሽልማት እንደሚያገኝ ማስታወስ ያሻል። ደግሞም ማንኛውንም ነገር ለታይታ የምናደርግ ከሆነ፣ ወደ ፊት ከጌታ ዘንድ የሚቆይልን ዋጋ እንደሌለ ማወቅ አለብን። ይህም ጾምን፣ ጸሎትንና ምጽዋትን ጨምሮ ሌላም ዓይነት የአምልኮ እንቅስቃሴዎችን የሚመለከት ነው።[60] ስለዚህ አክሊልና ሽልማት ስለሚያስገኙ ጉዳዮች በተለይ ትኩረት ልናደርግ ይገባል።

[60] ማቴ6:1። ሰዎች እንዲያዩላችሁ፣ መልካም ሥራችሁን በፊታቸው ከማድረግ ተጠንቀቁ፤ አንዲህ ካደረጋችሁ ከሰማየ አባታችሁ ዋጋ አታገኙም። ራእ22:12። ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን አክፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር ነው።

የደስታና
የድል አክሊል

በምድር በኖሩበት ዘመን፣ ሰዎችን ወደ ጽድቅ ወይም ወደ ክርስቶስ የደኅንነት አሳብ ለሚመልሱ ሰዎች በመጨረሻው ዘመን የሚሰጣቸው የአክሊል ዓይነት፣ የደስታ ወይም የድል አክሊል ይባላል። ጳንኤልም በመጨረሻው ዘመን ለእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች በተለይ የተዘጋጀውን የደስታ መጠን ሲናገር «ጥበበኞች እንደ ሰማይ ጸዳል፣ ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ሰዘላለም ይደምቃሉ።»[61] ብሏል። ጳውሎስም በተለያየ ጊዜ በወንጌል ያገለገላቸውን አማኞች «ደስታዬና **አክሊሌ** የምትሆኑ ወንድሞቼ ሆይ» ሲላቸው፣ ሌሎቹንም «ተስፋችን ወይም የትምክታችን **አክሊል** ማነው? በጌታችን በኢየሱስ ፊት በመምጣቱ እናንተ አይደላችሁምን? እናንተ ደስታችንም ክብራችንም ናችሁ» ብሏቸዋል።

በዚሁ መሠረት እግዚአብሔር ለወንጌል አገልግሎት የጠራቸውና ወንጌልን በልዩ ልዩ መንገድ ለሰዎች ለማድረስ የሚተጉ ሰዎች፣ አንድ ቀን ከጌታ ዘንድ አስደናቂውን የደስታና የድል አክሊላቸውን ይቀበላሉ ነው። ይህም ደስታ አሁን በምድር ሆኖ በቃልና በአንደበት ለመግለጥ ከምንሞክረው በላይ እጅግ ታላቅና የተለየ መሆኑ እሙን ነው። በእርግጥ የትኛውም ዓይነት ሰው፣ በዚህ ዓለም እስካለ ድረስ ይኼን ደስታ መቼም ሊለማመደው አይችልም። እግዚአብሔር ግን በምድር ሳሉ በወንጌል አገልግሎት ሲተጉ ለነበሩ ምርጥ ባሪያዎቹ እንዲህ ዓይነቱን አክሊልና ሽልማት ሊሰጣቸው ወስኗል። ይህ ተስፋ በተለይ የሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልጋዮችን ምን ያህል እንደሚያጽናና እንደሚያበረታታ ሳስብ እኔ ራሴ ስለእነርሱ እጅግ ደስ ይለኛል። እንደሚታወቀው በሥጋ ዓይን ሲታይ በዚህ ምድር በእውነት ወንጌል እየሰበኩ ለወንጌል የሚኖሩ ሰዎች ኑሮ ያን ያህል የሚያስቀና ወይም የሚያጓጓ አይደለም። አንዳንድ የወንጌል አገልጋዮችም በወንጌል

[61] ዳን12:3። ፊል4:1። 1ኛተሰ2:19።

ሥራ ተጠምደው ደፋ ቀና ሲሉ ለራሳቸውና ለቤተሰባቸው የሚሆን በቂ ነገር ለማግኘት እየተቸገሩ፣ የሚያዝኑበትና ተሳቀው የሚኖሩበት አጋጣሚ ብዙ ነው። ከዚህ የተነሣ ማንም እነርሱን ያየ ሰው፣ ግድ ካልሆነበት በቀር የሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልጋይነትን የመጀመሪያ ምርጫው አድርጎ ሊቀበለው እስከማይችል ድረስ ጥሪው ብዙም የማይወደድ ነው። በዚህ ምክንያት አንዳንድ የወንጌል አገልጋዮች በአቋራጭ ሕይወታቸውን አስደላች፣ ስኬታማና የሰመረ ለማድረግ ሲሞክሩ፣ ቀስ በቀስ ቀድሞ የነበራቸውን የወንጌል ቅናትና ፍቅር ያጡታል። ሆኖም ይኼን ወንጌል በፍጹም ታማኝነት ያለመሸቃቀጥ ሲያገለግሉ እስከ መጨረሻው ድረስ ጸንተው የሚገኙ አገልጋዮች፣ ኢየሱስ በፍርድ ወንበሩ በተቀመጠ ጊዜ ለቅዱሳኑ የሚያድለውን የደስታና የድል አክሊል ይቀበላሉ። ኹነቱ ደግሞ ማንንም ሰው የሚያስቀናና «ምነው እነርሱን ባደረገኝ» የሚያስብል በመሆኑ፣ ወደፊት ይኼ ተስፋ የሚጠብቃቸው የወንጌል አገልጋዮች፣ እርስ በእርሳቸው ሊጽናኑ ይገባቸዋል።

ይህ ግለት ግን ተስፋው የሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልጋዮችን ብቻ የሚመለከት ነው ማለት አይደለም። እንዲያውም የሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልጋይነት ጥሪ ባይደርሰውም፣ እያንዳንዱ አማኝ ባለበት ስፍራ ሁሉ ወንጌልን የመስበክና የማሰራጨት አደራ እንዳለበት የሚያስገነዝብ ነው። ይህም በመጨረሻው ዘመን አስደላች ሽልማት ለራሱ የሚያቆይበት ዋነኛው መንገድ ነው። አንድ የእግዚአብሔር ሰው በአንድ ወቅት ስለዚህ ጉዳይ ሲናገር «*በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉም ይልቅ አስደሳች የሚመስለኝ፣ አንድ ሰው ወደ እናንተ ዘንድ መጥቶ «በዚህ የተገኘሁት አንተ በነገርከኝ የወንጌል ቃል ነውና አመሰግንሃለሁ!» ያላችሁ እንደ ሆነ ነው*» አለ።

የማይጠፋ
አክሊል

62

ሽልማቱን አንደሚቀበል ሰው ሩጡ፤ ሰውድድር የሚዘጋጅ ማንኛውም ሰው በሁሉም ነገር ራሱን ይገዛል። እነርሱ ወሳፊና ጠፊ የሆነውን አክሊል ለማግኘት ይደክማሉ፤ እኛ ግን ለዘላለም የማይጠፋውን አክሊል ለማግኘት እንደክማለን። ስለዚህ እኔ ግብ እንደ ሌለው ሰው በከንቱ አልሮጥም፤ ደግሞም ነፋስን እንደሚጉስም ሰው አንዲያው አልታገልም፤ ነገር ግን ስሌሎች ከሰበክሁ በኋላ እኔ ራሴ ውድቅ ሆኜ እንዳልቀር ሰውነቴን አየጉሰምሁ አንዲገዛልኝ አደርገዋለሁ።

ማንኛውም ሰው በክርስቶስ ካመነ በኋላ፣ ባሉት ዘመናት ተቀድሶ እንደሚገባ ከተመላለሰና ከጌታ የተሰጠውን ሩጫ በመሮጥ ወደ ግቡ የሚፈጥን ከሆነ አንድ ቀን ከጌታ ፊት ቀርቦ የማይጠፋውን አክሊል የመቀበሉ ጉዳይ የሚያጠራጥር አይደለም። ጳውሎስም «ታገኙ ዘንድ ሩጡ» የሚለው፣ ይኼን ዓይነቱን ሩጫ ነው። በመሠረቱ የአማኝ ሩጫ፣ ከዚህ ዓለም ሯጮች ጋር ሲነፃጸር፣ ልዩነቱ የግብ ወይም የሃላማ ሆኖ ይታያል። የዚህ ዓለም ሯጮች የሚሮጡት፣ የሚጠፋውን ሽልማትና አክሊል እንደሚያገኙ ተስፋ አድርገው ሲሆን፣ አማኞች ግን የማይጠፋውንና ዘላለማዊ የሆነውን አክሊልና ሽልማት የማግኘት ተስፋ ይዘው ነው። በዚህ ምክንያት በሁለቱ ሯጮች መኻል ያለው ልዩነቱ የትየለሌ ነው። ጻሩ ግን በዛሬው ጊዜ ሆኖ፣ ያንን ዘመን በሚታይ ማስረጃ መግለጥ ስለማይቻል፣ አንዳንድ ጊዜ ሩጫውን ተስፋ የማይታይበት ሊያደርገው ይችላል። በዚያ ላይ ከዚህ ዓለም ሥርዓት ውስብስብነት የተነሣ ብዙ ጊዜ በትክክለኛው መንገድ ለሚጓዙ ሰዎች ነገሮች ሁሉ አስቸጋሪና ውስብስብ ሲሆኑ ይታያሉ።

ስለዚህ ጉዳይ የዕብራውያን ጸሐፊ ሲናገር፣ የሩጫውን አስቸጋሪነትና የመጨረሻ ፍጻሜ ለማስረዳት የብሉይ ኪዳን የእምነት አባቶችን እንደ አብነታዊ ማስረጃ መጥቀስ አስፈልጎታል። ጸሐፊው እነዚህ

62 1ኛቆሮ9:24-26።

የእምነት አባቶች፣ በእያንዳንዱ አማኝ ዙሪያ እንደ ደመና ከበው እንዳሉ ከገለጠ በኋላ፣ አማኞች፣ ሸክም የሚሆንባቸውና በቀላሉ ተብትቦ የሚይዛቸውን ኃጢአት አስወግደው፣ በፊታቸው ያለውን ሩጫ በፅናት መሮጥ እንዳለባቸው ያሳስባል። ደግሞም በእያንዳንዱ የሩጫው ሰዓት *«የእምነታችሁ ጀማሪና ፍጹም አድራጊ የሆነውን ኢየሱስን ብቻ መመልከት አለባችሁ»* ይላል። ምክንያቱም ኢየሱስ በፊቱ ስላለው ደስታ መስቀሉን ታግሶ፣ ደግሞም ያን የመሰለ የመስቀል ውርደት ንቆ ካለፈ በኋላ፣ አሁን በእግዚአብሔርነቱ ዙፋን በቀኙ ተቀምጧል። እናም አማኞች በነፍሳቸው ዝለው ተስፋ እንዳይቆርጡ ከኃጢአተኞች የደረሰበትን እንዲህ ያለ ተቃውሞ የታገሰውን ኢየሱስ ሁልጊዜ ሊያስቡ ይገባል። የዚያን ጊዜ የሩጫቸውን ፋይዳና ተስፋ በቀላሉ ይረዳሉ።[63] እያንዳንዱ አማኝ ለሮጠው ሩጫ ከጌታ ዘንድ ሽልማትና አክሊል እንደተዘጋጀለት እያሰበ ደስ ሊለውና የጊዜውን ሐዘንና መከራ ታግሶ ሊፀና ይገባል። ያን ቀን ጌታ፣ ለአማኞች የሚሰጠው አክሊልና ሽልማት የማይጠፋና ለዘላለም የሚኖር መሆኑ እንዴት የሚያስደስት ነው?

[63] ዕብ12:1-3።

የክብር አክሊል

በእናንተ ኃላፊነት ሥር ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ የምትጠብቁትም ከእግዚአብሔር እንደሚጠበቅባችሁ በግድ ሳይሆን በፈቃደኝነት፣ ስጥቅም በመስገብገብ ሳይሆን፣ ለማገልገል ባላችሁ ጽኑ ፍላጎት ይሁን፤ እንዲሁም በዐደራ ስተሰጣችሁ መንጋ መልካም ምሳሌ በመሆን እንጂ፣ በላያቸው በመሠልጠን አይሁን። የአረኞች አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማይጠፋውን አክሊል ትቀበላላችሁ።[64]

በጥንት ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉ አገልግሎቶች ሁሉ፣ አስቸጋሪው አገልግሎት የእረኝነት ወይም የመሪነት አገልግሎት ስለነበር፣ ጥሪውን ለመቀበል አማኞች ያን ያህል ተነሳሽነትና ፍላጎት አይታይባቸውም ነበር። ይህንን የተረዱት ሐዋርያትም በተለያየ ጊዜ በጻፏቸው መልዕክቶች እረኞች ወደ ፊት የሚያገኙትን ክብርና ምስጋና እያሰቡ እንደተሰጣቸው ጸጋ መጠን በዚህ አገልግሎት ሊተጉ እንደሚገባ አደፋፍረዋል። ለምሳሌ ጳውሎስ «ማንም አጸደ ቆጶስነትን ቢመኝ መልካምን ነገር ይመኛል» ማለቱ፣ በወቅቱ አገልግሎቱ ምን ያህል ማነሣሣትና ማበረታታት ያስፈልገው እንደነበር የሚጠቁም ነው።[65]

እርግጥ ነው በየትኛውም ዘመን ለእውነተኛ እረኞች የመሪነት ስፍራ እንደዚህ ዓለም ሹመትና ሽልማት የሚያጓጓ ወይም የሚያስደስት ሆኖ አያውቅም። ስፍራው በራሱ ካለው ከፍተኛ የአገልግሎት ጫና በተጨማሪ፣ እረኛው ለተቀበለው ኃላፊነት ወደፊት በክርስቶስ ፊት ያለበት ተጠያቂነት የሚያስፈራ ነው። ከዚህም በላይ በየጊዜው በቤተ ክርቲያን ላይ የሚሆነው ስደትና መከራ የመጀመሪያ ገፈት ቀማሽ መሆን ስለሚያስከትል፣ ማንም በደስታ የሚመርጠው አልነበረም። እንዲያም ሆኖ አገልግሎቱን በታማኝነትና በእውነት የሚያገለግሉ ሰዎች፣ በምድር ምስጋና፣ ክብርና ጥሩ ስም ሲያገኙበት አይታይም። ብዙ ጊዜም፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉ ምዕመናን አብዛኞቹ

[64] 1ጴጥ5:1-4።
[65] 1ጢሞ3:1።

ፍላጎታቸው ከተሟላላቸውና ሁሉም ነገር ሰላም የሆነ ከመሰላቸው መሪዎቻቸው ያን ያህል ትዝ ላይሏቸውና ስለእነርሱም የማያላስባቸው ሲሆኑ ይታያሉ። በአንጻሩ ምዕመናን የሆነ ነገር እንደጎደላቸው ካሰቡ መሪዎችን ማማረራቸው፣ መተቸታቸውና ለሆነው ሁሉ እነሱን ተጠ ያቂ ማድረጋቸው የተለመደ ነው። ደግሞም በአንድ ጉባኤ ያሉ ሰዎችን ፍላጎት እኩል ማርካት ወይም ሁሉን ደስ ለማሰኘት መሞከር ምንኛ አስቸጋሪ ተግባር እንደሆነ መገመት ቀላል ነው። ከዚህም ሌላ በበርካታ ምክንያቶች ብዙ ጊዜ አረኞች ብቸኞች ከመሆናቸው በላይ ማንም ስለእነርሱ ግድ የሌለውና ስሜታቸውን የማይረዳቸው መስሎ እንዲሰማቸው ይሆናሉ። በየጊዜው በሕዝቡ መኻል በሚሆን ሐዘን፣ ግራ መጋባትና ጉዳት ምክንያት እነርሱ ምን ያህል አብረው እንደ ሚሰቃዩ ማንም የሚረዳ እንደሌለ እያሰቡ ተስፋ ሊቆርጡ፣ ሊያዝኑና ነገሩ ሲደጋገምም ቸልተኛ ሊሆኑ ይችላሉ።

ሆኖም ጴጥሮስ ስለዚህ ጉዳይ ሲናገር፣ ከሁሉ አስቀድሞ እረኞች መንጋውን ማገልገል ያለባቸው፣ ኃላፊነቱ በግድ እንደተጫነባቸው ሸክም በመቁጠር ሳይሆን፣ በፍቅርና በደስታ መሆን እንዳለበት ይመክራል፤ ቀጥሎም ለጥቅም ከመስገብገብ ይልቅ ለጌታና ለአማኞች ባላቸው ጽኑ ፍቅር የተነሣ መንጋውን እንዲያገለግሉም ያሳስባቸዋል። ጉዳዩን ልብ ብለን ስናስተውለው፣ ምናልባት «ማንም አክሊልህን አንዳይወስድብህ ያለህን አጥብቀህ ያዝ»[66] የሚለው ቃል ከማንም ይልቅ ለእነዚህ ሰዎች የላቀ ትርጉም ሳይኖረው አይቀርም። ከዚህ አንጻር ምንም እንኳ በዚህ ምድር ለአገልግሎታቸው የሚመጥን ክብርና ሽልማት ባያገኙም፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በመምራት ወይም በእረኝነት የሚያገለግሉ ሰዎች የእረኞች አለቃ የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በታላቅ ግርማውና ክብሩ በሚገለጥበት ቀን፣ የማያልፈውን የክብር አክሊል እንደሚቀበሉ በማሰብ በእምነትና በተስፋ መጽናት ይጠበቅባቸዋል።

[66] ራእ3:11።

የሕይወት አክሊል

በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ምክንያቱም ፈተናን ሲቋቋም
እግዚአብሔር ለሚወዱት የሰጠውን ተስፋ፣ የሕይወትን አክሊል ያገኛል።[67]

ቅዱስ ቃሉ «በክርስቶስ ኢየሱስ በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት መኖር የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ»[68]ይላል። በእርግጥም በተለያዩ ዘመናት በዓለም የኖሩ አማኞች በታላቅ ስደት፣ መከራ፣ ችግርና ሐዘን ውስጥ ማለፋቸው የተለመደ ነው፤ ምንም እንኳ በአሁኑ ጊዜ በብዙ ቤተ ክርስቲያናት በሚሰጡ ስብከቶችና ትምህርቶች፣ ጉዳዩ እጅግም ጎልቶ ባይሰማም ጌታ ኢየሱስ ራሱ ተከታዮቹ በዓለም ሳሉ ከፍተኛ ስደትና መከራ እንደሚደርስባቸው ደጋግሞ ተናግሯል። [69]

በክርስቶስ ተከታዮች ላይ ስደትና መከራ የሚደርስበት ምክንያት፣ እነርሱ የተለየ የሕይወት ፍልስፍና ስለሚከተሉና ይኼም ለዚህ ዓለም ሰዎች ስለማይመች ነው። ስለዚህ አማኞች መከራ ሲደርስባቸው ግራ መጋባትና ተስፋ መቁረጥ የለባቸውም፤ እንዲያውም በመከራ ውስጥ ሲያልፉ ከፊት ይልቅ መፅናት ይጠበቅባቸዋል። ምክንያቱም በፈተና መጽናት ታላቅ መባረክ ከመሆኑም በላይ ከፈተናውም በኋላ እግዚአብሔር ለሚወዳቸውና እነርሱም ለሚወዱት የሰጠውን ተስፋ፣ ማለትም የሕይወት አክሊል ስለሚያስገኝ ነው።

ስለዚህ አማኞች፣ በክርስቶስ ምክንያት የሚደርስባቸውን መከራ እንደ ድንቅ ነገር ከማጋነን ይልቅ፣ የመከራው ተካፋይ በመሆናቸው፣ የወደፊት ደስታቸው ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ማሰብ አለባቸው። በዚያ ላይ እግዚአብሔር ሁሌም ቢሆን ከፈተናው ጋር መውጫውን ያዘጋጃል። በመሆኑም ማንም ከሚችለው በላይ እንደማይፈተንና በፈተናው ጊዜ አስፈላጊ የሆነው የጸጋ አቅርቦት እንዳለ በመረዳት፣

[67] ያዕ1:12።
[68] 2ኛጢሞ3:12።
[69] ዮሐ15:18-21።ዓለም ቢጠላችሁ ከእናንተ በፊት አኔን እንደጠላኝ አወቁ።

መጽናት ይገባዋል። ደግሞም ከእያንዳንዷ ፈተና በኋላ ከጌታ ዘንድ የሚጠብቀውን የሽልማትና የአክሊል አስደሳችነት እያስታወሰ፣ በእምነቱ ከትናንት ይልቅ ሊተጋ ይገባዋል። መቼም ቢሆን መከራ ለጊዜው ደስ ባያሰኝም ከጊዜ በኋላ ውጤቱ ምን ያህል አስደሳች እንደ ሆነ ያዩትና የቀመሱት ያውቁታል። ይኼ ተስፋም በዓለም ሳለን ከምናውቀው ሁሉ የተለየ እንደሆነ እሙን ነው። ኢየሱስም ለደቀ መዛሙርቱ «ሥጋን ብቻ መግደል የሚችሉትን አትፍሩ» ማለቱ፣ ከዚህ ሕይወት በኋላ ሌላ እውነተኛ ሕይወት እንዳለ ያስረዳል።

ጌታ ኢየሱስ ሰውን ወደ ራሱ ሲጠራ፣ ያ ሰው ስለስሙ የሚቀበለውን መከራ እያሰበ ደስ የሚሰኝ ይመስለኛል። ለምሳሌ ለጳውሎስ ለሳከው ሐናንያ ለተባለ ሰው «ሰሰ ስሜ ስንት መከራ እንዲቀበል አነ አመሰክተዋለሁ» ነበር ያለው። ጳውሎስም ይኼን ከተረዳ በኋላ «ሰሰ አርሱ መከራ ልትቀበሱ እንጂ በአርሱ ልታምኑ ብቻ አይደሰም» ማለቱ፣ ጸንተው ለሚያከብሩት ምርጦቹ እግዚአብሔር ያዘጋጀው ክብር ታላቅ መሆኑን እንደተረዳ ያመለክታል። እንዲያውም በኋላ ላይ በክርስትና ሕይወቱ ጠልቆ በገባ መጠን በክርስቶስ መከራ መካፈልን እንደ አብረቅራቂ ሽልማት የቆጠረው ሁሉ ይመስላል።[70]

> አርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ፣ በመከራውም እንድካፈል፣ ወደ ሙታን ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ፣ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ።

[70] ሐዋ 9:16። ፊል 1:29፣ 3:10።

የጽድቅ አክሊል

71

> ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፣ ይህንንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነ ጌታ ያን ቀን ያስረክበኛል

ጳውሎስ ሁለተኛውን መልዕክት ለጢሞቴዎስ በሚጽፍበት ወቅት ለአያሌ ወራቶች ጽኑ መከራ እየተቀበለ በአስር ቤት እንደቆየ ይታመናል። የጢሞቴዎስ መልዕክት ደግሞ ለጳውሎስ የመጨረሻው መልዕክት እንደመሆኑ መጠን፣ ምናልባት ከዚያ በኋላ በምድር የቆየባቸው ወራት በጣት የሚቆጠሩ እንደነበሩ መገመት እንችላለን። ነገር ግን በጳውሎስ የመጨረሻ መልዕክት ውስጥ፣ ዕድሜ ልኩን አንድ ያጓጓውን ነገር ናፍቆ ያገኘ እንጂ፣ ሞት ደጃፉን የሚያንኳኳ ሰው ምስል አይታይም። እንዲያውም፣ በምድር ለኖረው ኑሮ፣ ተመጣጣኝ አክሊልና ሽልማት እንደሚያገኝ እርግጠኛና ልበሙሉ የሆነ ሰው ይመስላል። በዚያ ላይ ጳውሎስ ይኼ ተስፋ የተዘጋጀው፣ ለእርሱ ብቻ ሳይሆን የኢየሱስን መገለጥና ተመልሶ መምጣት ለሚናፍቁ ሁሉ እንደሆነ አበክሮ ያሳስባል። እንደሚታወቀው፣ ጽድቅ ማለት ትክክል ወይም እውነት ማለት ነው። ከዚህ አንጻር የአማኞች የምድር ኑሮ፣ ጌታ ኢየሱስ ወደ ፊት ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ ባለው የእውነተኛ ሥርዓት ተስፋ ላይ የተመሠረተ ከሆነ፣ የጽድቅ አክሊል ሽልማት እንደሚያገኙ ጥርጥር የለውም። ይህም በምድር ላይ እንደ እንግዳና መጻተኛ ለኖሩት ኑሮ ትክክለኛነት የሚሰጥ ሽልማት ነው።

በአንድ ወቅት ጌታ ኢየሱስ፣ ደቀ መዛሙርቱ ሳይታክቱ ዘወትር ተግተው መጸለይ እንዳለባቸው ለማስተማር ወደ፣ በአንድ ዐመጸኛ ዳኛ ምክንያት ፍርድ ስለተጓደለባት ሴት ምሳሌ ነግሯቸው ነበር። በምሳሌው የተጠቀሰችው ሴት የፈለገችው ነገር እስክታገኝ ድረስ፣ ዐመጸኛው ዳኛ የሚፈጽምባትን ግፍ ሁሉ ታግሳ በትጋት ትወተውት

[71] 2ኛጢሞ4:8።

ነበር። ያንን በማድረጓ ምክንያት ከብዙ ጊዜ በኋላም ቢሆን ከዚያ፣ እግዚአብሔርን ከማይፈራና ሰውን ከማያፍር ዳኛ እጅ ፍትህን አግኝታለች። እንደ ጌታ ትምህርት ይህቺ ሴት ያንን ሁሉ ዘመን ዳኛውን ለመወትወት አቅም ያገኘችው በውስጧ ታላቅ እምነትና ጽናት ስለነበራት ነው። ጌታም እንደዚች ሴት ቀንና ሌሊት ወደእሱ ለሚጮኹ ምርጦቹ ሁሉ እንደሚፈርድላቸው አስታውሶ *«ተመልሼ በምመጣበት ጊዜ በምድር ላይ እንዲህ ያለ እምነት አገኝ ይሆን?»* ሲል ጠይቋል።[72] በእርግጥ ጌታ ኢየሱስ በዚህ ስፍራ ከሰው የጠበቀው እምነት፣ ለፈውስ፣ ለታምራትና ለድንቃ ድንቅ ለመሳሰሉ ነገሮች ወይም ደግሞ እንደመብላት፣ መጠጣትና መልበስ ለመሳሰሉ ጉዳዮች የሚሆን እምነት መስሎ አይታየኝም። ለነገሩ አሁን ባለንበት ዘመን እንኳ ብዙ ሰዎች ስለእነዚህ ጉዳዮች በእግዚአብሔር በማመን በኩል እጅግ የተጋነነ ችግር እንደሌለባቸው ለሁሉ የተገለጠ ነው። ደግሞም ቀጥራቸው ቀላል የማይባል ሰዎች እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ እንደሚሰጣቸው ተስፋ በማድረግ በእርሱ እንደሚታመኑ ሲናገሩ መስማት የተለመደ ነው። በብዙ አብያተ ክርስቲያናት አውደ ምህረት በስፋትና በተደጋጋሚ የሚሰበከው አማኞች እንደዚህ ዓይነት እምነት እንዲኖራቸው ነው። በአንዳንድ ዘመናትም ይህ ዓይነቱ እምነት እንደ «እንቅስቃሴ» ተቆጥሮ በጥልቀት የተሰበከበት አጋጣሚ አለ።

ታዲያ ጌታ ኢየሱስ ወደ ፊት ተመልሶ በሚመጣ ጊዜ በብዙ «አማኞች» ዘንድ እንኳ እንደማያገኘው የጠረጠረው እምነት ምን ዓይነት ይሆን? በመሠረቱ እሱ ከአማኞች ሁሉ የሚፈልገው እምነት፣ ዳግመኛ በክብር እንደሚመጣ አውቀው፣ በመምጣቱ ተስፋ የተቃኘና የተዘጋጀ ሕይወት ይዘው እንዲጠባበቁት ነው። አብርሃም ለምሳሌ የእምነት አባት ሆኖ የሚጠቀስና እምነቱም በእግዚአብሔር ዘንድ ጽድቅ ሆኖ የተቆጠረለት ሰው እንደነበር ይታወቃል፤ ታዲያ በምድር ላይ በኖረባቸው ዓመታት፣ ራሱን እንደ እንግዳና መጻተኛ በመቁጠር

[72] ሉቃ18:8። የሰው ልጅ በምድር በመጣ ጊዜ እምነትን ያገኝ ይሆን?

በስደትና በድንኳን የኖረው፣ እግዚአብሔር የሠራትን አገርና ከተማ ገና ወደፊት እንደምትገለጥ ተስፋ አድርጎ የሚጠባበቅ በመሆኑ እንደነበር ይነገርለታል።[73] ልክ እንዲሁ፣ ማንኛውም ሰው *«ለዚህች የምትኖር አገርም ሆነ ከተማ የለኝም»* ብሎ እያሰበ ገና የምትመጣዋን በናፍቆት የሚጠባበቅ ከሆነ፣ የሕይወት ሥርዓቱ ፍጹም እንደሚቀየር አያጠራጥርም። በዚህ ምድር ኑሮው እንግድነት እንጂ ነዋሪነት የማይሰማው ሰው፣ የዚህ ዓለም ሰዎች ትኩረት የሚሰጧቸው ብዙ ነገሮች ያን ያህል እንደማይመስጡትም ግልጥ ነው። ይህም ትክክለኛ የሕይወት ሥርዓት በመሆኑ እንደዚህ ላለው ሰው፣ ከጌታ ዘንድ ወደፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶ ይጠብቀዋል።

[73] ዕብ11:8-12።

መቅጠቅጥ
መሰብሰብ

ስለ የመጨረሻው ዘመንም ሆነ ስለንጥቀት የሰማሁት፣ ከዓመታት በፊት፣ በአንድ ኢትዮጵያዊ መጋቢ በውጪ አገር ተሰብኩ፣ በአራት ክፍሎች ተዘጋጅቶ ከቀረበ የኦድዮ ካሴት ነው። በወቅቱ በሥጋም ሆነ በመንፈሳዊ ዕድሜዬ ገና ልጅ ስለነበርኩ የነዚህን ነገሮች ሚስጥር ምንነት ለመረዳት እጅግ ግራ ተጋብቼ እንደነበር አስታውሳለሁ። እንዲያም ሆኖ ግን በዚያን ጊዜ ከሰማሁት የተነሣ፣ ንጥቀት በታላቁ መከራ እኩሌታ እንደሚሆን በማመን ቀጥዬ፣ አንዳንዴም ይኼንኑ ደፍሬ አስተምር ነበር። ይሁን እንጂ ከጊዜ በኋላ ስለዚህ ጉዳይ የሚናገሩ የተለያዩ ትምህርቶችን ጉዳዬ ብዬ ማጥናት ስጀምር ግን አመለካከቴ ቀስ በቀስ እየተቀየረ መጣ። ይህ ዓይነቱ አጋጣሚም በእኔ ብቻ ሳይሆን፣ በብዙ አገልጋዮች ላይ የሚያጋጥም የአቋም መለዋወጥ እንደሆነ ተረድቻለሁ።

በቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች መኻል፣ ንጥቀትን በተመለከተ ያለው ልዩነት የሚመነጨው በአብዛኛው ኹነቱ ከሚከሰትበት የጊዜ ሰሌዳ አንጻር እንደሆነ ከዚህ በፊት ተመልክተናል። በመሆኑም አንዳንዶች ንጥቀት፣ ከታላቁ መከራ በፊት ነው ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ በታላቁ መከራ መኻል፣ አለያም ከታላቁ መከራ በኋላ ነው፤ በማለት ያምናሉ። ለምሳሌ እኔ ቀደም ብዬ አቋሜን እንደገለጥኩት፣ ንጥቀት ከታላቁ መከራ በፊት እንደሚሆን ነው የማምነው። ከዚህ በኋላ ባሉት ክፍሎችም እንዲህ እንዳምን ምክንያት የሆኑኝን የመጽሐፍ ክፍሎች በማስደገፍ አቋሜን የበለጠ ግልጥ ለማድረግ እሞክራለሁ። ታዲያ እግረ መንገዴን ከዚህ ጋር ተያይዘው የሚነሡ መሠረታዊ ጉዳዮችን በመጠኑ እዳስሳለሁ።

ጌታ ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ሃያ አራት ስለመጨረሻው ዘመን ባስተማረ ጊዜ፣ በተለይ ቁጥር ሃያ ዘጠኝ ላይ የተናገረው በዛሬው ጊዜ በንጥቀት መቼነት ከሚያወዛግቡ ክፍሎች አንዱ ሆኖ

ይጠቀሳል። አንዳንድ ሰዎችም ይኼን ክፍል ንጥቀት ከታላቁ መከራ በኋላ እንደሚሆን ለሚያነሡት መከራከሪያ ዋነኛ ማስረጃ አድርገው ያነሡታል።[74] ሆኖም ክፍሉ ስለቤተ ክርስቲያን መነጠቅ እንደሚወራ እርግጠኛ ሆኖ መናገር አይቻልም። እንዲያውም ስለሌላ ተመሳሳይ ዘመንና ጊዜ የሚናገር መስሎ ነው የሚታየው። በእርግጥ በዚያ ክፍል፣ ቁጥር ሃያ ሰባት ላይ ጌታ፣ ስለራሱ መምጣት ተናግሮ ሲያበቃ «ከእነዚያ ከመከራው ቀናት በኋላ» ማለቱ ጊዜው በሰባኛው ሱባኤ መጠናቀቂያ አካባቢ ወይም የእነዚያ ሰባት የመከራ ዓመታት ፍጻሜ ሲቃረብ እንደሆነ ያመለክታል። በዚያን ጊዜ፣ ክርስቶስ ከሰማይ በደመና በታላቅ ክብር ሲመጣ የምድር ወገኖች ሁሉ እንደሚያዩትና እንደሚያለቅሱ ተመልክቷል። ነገር ግን እነዚህ የእሱ መምጣት «ወዮ» የሚያሰኛቸው ሰዎች እነማናቸው? የሚለው ጉዳይ በትኩረት መታየት ያለበት ይመስላል። ከዚህ በተቃራኒው የእሱ መምጣት «ለመሰብሰባቸው» ምክንያት በመሆኑ ደስ የሚላቸው ሰዎች፣ በወቅቱ በምድር መኖራቸው ደግሞ የዚያን ዘመን ኹነት ውስብስብነትና ሚስጥራዊነት የበለጠ ያጎላዋል።

ሆኖም ንጥቀት ከመከራው በኋላ እንደሚሆን በሚያምኑ ሰዎች ይህ ክፍል የመጠቀሱ ምክንያት፣ ጌታ በሚመጣበት ጊዜ መላእክቱን ከታላቅ የመለከት ድምፅ ጋር እንደሚልካቸውና እነርሱም ምርጦቹን ከአራቱም ነፋሳት፣ ከሰማያት ከአንዱ ዳርቻ ወደሌላው ዳርቻ እንደሚሰበስቡለት በመናገሩ ምክንያት ነው። ነገር ግን በዚያን ጊዜ የሚነፋው መለከት የትኛው መለከት ነው?[75] የሚለውና «ምርጦች» የተባሉት እነማን ናቸው? የሚለው ጉዳይ አከራካሪ ነው። ለምሳሌ *«ንጥቀት ከሰባኛው ሱባኤ በኋላ ነው»* የሚሉ ሰዎች መለከቱ፣ ጳውሎስ በመጀመሪያው የቆሮንቶስ መልዕክቱ 15ኛ ምዕራፍ የገለጠውና በቤተ

[74] ማቴ 24:27-29። መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ ምዕራብ ድረስ እንደሚያበራ፣ የሰው ዕጅ ስመጣም እንደዚሁ ይሆናል። በድን ባለበት ስፍራ ሁሉ አሞሮች ይሰበሰባሉ። ወዲያውኑ ከእነዚያ ከመከራው ቀናት በኋላ፣ ፀሐይ ትጨልማለች፣ ጨረቃ ብርሃኗን ትከለክላለች፣ ከዋክብት ከሰማይ ይረግፋሉ፣ የሰማይ ኃይላትም ይናጋሉ።

[75] 1ኛ ቆሮ 15:51፣52። ሁላችን አናንቀላፋም፣ ነገር ግን ሁላችን እንለወጣለን። ይህም የሚሆነው የመጨረሻው መለከት ሲነፋ ድንገት በቅጽበተ ዓይን ነው።

ክርስቲያን ንጥቀት ሰዓት የሚነፋው «የመጨረሻው መለከት» እንደ ሆነ ሲሞግቱ፣ በወቅቱ እንደሚሰበሰቡ የተነገረላቸው ምርጦች ደግሞ «ቤተ ክርስቲያን ናት» ብለው ያስተምራሉ። ሆኖም በማቴዎስ ወንጌል የተጠቀሰው «መለከት» እና ጳውሎስ ከንጥቀት በፊት እንደሚነፋ የተናገረው «መለከት» አንድ ዓይነት ስለመሆናቸው ተጨማሪ ማስረጃ ማቅረብ የሚቻል አይመስልም። ከዚህ የተነሣ በመጨረሻው ሰዓት በመላእክቱ የመለከት ድምፅ እንደሚሰበሰቡ የተጠቀሱት ምርጦች «ቤተ ክርስቲያን» ስለመሆንዋ እርግጠኛ ለመሆን ያስቸግራል። ምክንያቱም በጳውሎስና በጌታ ትኩረት መኻል መሠረታዊ የሚባል ልዩነት መኖሩ በግልጥ የሚታይ በመሆኑ ነው። በመሠረቱ ጳውሎስ ስለመነጠቅ የጻፈ ሲሆን፣ ኢየሱስ ግን የተናገረው ስለመሰብሰብ ነው። ከዚህ አንጻር ከተመለከትነው ደግሞ በመነጠቅና በመሰብሰብ መኻል «መሠረታዊ» ሊባል የሚችል ልዩነት እንዳለ እንረዳለን። በተጨማሪም የጳውሎስ መልዕክት ስለሙታን ትንሣኤ የሚናገር ሲሆን፣ የኢየሱስ ትምህርት ግን ስለዚህ ጉዳይ ያነሣው ነገር የለም። ደግሞም ጳውሎስ «በዚያን ጊዜ የሚጠፋው የማይጠፋውን፣ የሚሞተው የማይሞተውን ሲሰብስ ይገባዋል» በማለት ስለመለወጥ ያስተማረ ሲሆን፣ ኢየሱስ ግን ስለዚህ ነገር ምንም አላለም።

ከላይ ከተነሡት አሳቦች አንጻር *«ኢየሱስ በትምህርቱ የተናገረውና ጳውሎስ በመልክቱ የጠቀሰው መለከት፣ ለአንድ ዓይነት ተግባርና ጊዜ የሚውሉ እንዳልሆኑ ለመገንዘብ እንዲሁም በመሰብሰብና በመነጠቅ መኻል ተጨማሪ ልዩነት እንዳለ ለመረዳት፣ ጌታ ኢየሱስና ጳውሎስ ስለእነዚያ አበይት የትንቢት ፍጻሜ ወቅቶች በተናገሩ ጊዜ የተጠቀሙባቸውን ቃላት መመርመር ጠቃሚ ነው»* የሚሉ ሰዎች አሉ፤ እነዚህ ሰዎች አሳባቸውን ሲያስረዱ *«በግሪኩ ቋንቋ ሁለቱን አሳቦች ለመግለጥ የዋለውን ቃል በራሱ ልዩነታቸውን ለመረዳት ተጨማሪ መረጃ ሊሰጠን ይችላል»* ይላሉ። *«በዚሁ መሠረት ጌታ ኢየሱስ፣ በማቴዎስ ወንጌል ላይ ለተናገረው አሳብ በጥቅም ላይ የዋለው የግሪኩ ቃል 'ኢፒሱናጎ' የሚለው ሲሆን፣ ቃሉ የተበታተነውን የመሰብሰብና አንድ የማድረግ ተግባርን የሚገልጥ ነው። በአንጻሩ ጳውሎስ በቆሮንቶስ መልዕክቱ የተጠቀመው 'ሐርፓዞ' የሚለው*

ቃል፣ አንድን ነገር በኃይል ነጥቆ በመውሰድ የራስ ማድረግን የሚያመለክት ነው» በማለት ያስረዳሉ።[76]

በተጠቀሱት ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ላይ እንደተመለከተው ጌታ ኢየሱስ በመጨረሻው ጊዜ ስለሚሆን የሕዝብ መሰብሰብ ሲናገር ጳውሎስ ደግሞ ስለሕዝቡ መነጠቅ ነው የጻፈው። ነገሩ እንዲያ ከሆነ ደግሞ በመነጠቅና በመሰብሰብ መኻል ዓይነተኛ ልዩነት ያለ መስሎ ይታያል።

ስለሚነጠቁትና ስለሚሰበሰቡት ሰዎች ስናነሣ ልዩነታቸው በሌላም መልኩ ሊገለጥ የሚችል እንደሆነ እንመለከታለን። በዚሁ መሠረት አማኞች የሚነጠቁት ታላቁ መከራ ከመሆኑ በፊት ባለ ጊዜ ሲሆን፣ በወቅቱ በሕይወተ ሥጋ የተገኙት በቅጽበት ተለውጠው፣ ያንቀላፉት ደግሞ ከሙታን መኻል ተቀስቅሰው፣ ጌታን በአየር ለመቀበል ከሄዱ በኋላ፣ ለሰባት ዓመት በበጉ ሠርግ ላይ ቆይተው ከእሱ ጋር አብረው ወደ ምድር የሚመጡ ናቸው። ከሰባው ሱባኤ በኋላ እንደሚሆን የሚጠበቀው መሰብሰብ ግን፣ በታላቁ መከራ ዘመን በማንነታቸው ምክንያት የሚደርስባቸውን ጽኑ መከራ፣ ስደትና ስቃይ የታገሱ፣ እንዲሁም እግዚአብሔር ራሱ በሚያደርግላቸው ጥበቃ ተሸሽገው የተረፉ እስራኤላውያንን የሚመለከት ነው።

ይሁንና እነዚህ ምርጦች የተባሉት እስራኤላውያን ስለመሆናቸው ማስረጃው ምንድነው? የሚል ጥያቄ መነሣቱ አይቀርም። እንደ እውነቱ ከሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔር ምርጦች እንደ ሆኑ የተጠቀሱ ከአንድ በላይ የሆኑ ማንነቶች ይገኛሉ። በዚሁ መሠረት ራሱ ክርስቶስ፣ ቤተ ክርስቲያን፣ እስራኤልና ቅዱሳን መላእክት በተለያዩ ስፍራዎች ምርጦች ተብለው ተጠርተዋል።[77] እንዲህ ከሆነ ደግሞ በማቴዎስ ወንጌል እንደሚሰበሰቡ የተጠቀሱት ምርጦች ማንነት ለመረዳት በአውደ ምንባቡ ላይ ትኩረት ማድረግ

[76] ግሪክ፣ አዲስ ኪዳን በመጀመሪያ ወደ ሰው ልጅ በደረሰበት ጊዜ በጥቅም ላይ የዋለ ቋንቋ እንደሆነ ዕብ ይሳዕ። episunago-harpazo www.layhands.com bay Dave

[77] ኢሳ፡1-13።1ኛጴጥ2:6:ኢየሱስ። 1ኛጢሞ5:21:መላእክት። ኢዮ45:4:እስራኤል።ቆሳ3:12:ቤተክርስቲያን

ተገቢ ይሆናል። ከዚህ አንጻር ብዙም ሳንመራመር በዚያው የምንባብ ክፍል፣ ጌታ ኢየሱስ ዋና ተናጋሪ በመሆኑና የመላእክቱም ድርሻ በግልጥ በመታወቁ፣ ትኩረታችንን በቀሩት በሁለቱ ላይ ብቻ እንድናደርግ ያስገድደናል። በመሆኑም ጌታ ኢየሱስ በዚያው ምዕራፍ ወንጌል በዓለም ሁሉ ከተሰበከ በኋላ «ከዚያም መጨረሻው ይመጣል» በማለቱና በተለይ ከቁጥር አስራ አምስት ጀምሮ በአይሁድ ላይ ልዩ ትኩረት ማድረጉ፣ እንዲሁም እስራኤልን ብቻ የሚመለከቱ ሰንበትን ስለመሳሰሉ ጉዳዮች ማውሳቱ[78] ትንቢቱ ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ ለእስራኤል የተናገረ መሆኑን እንድንቀበል ይገፋፋናል።

ንጥቀት፣ ቤተ ክርስቲያንን እንጂ እስራኤልን የሚመለከት ስለመሆኑ እርግጠኛ መሆን አስቸጋሪ ነው። ይህ ሲባል ግን ከእስራኤላውያን መካል ከቤተ ክርስቲያን ወገን ሆነው የሚነጠቁ መኖራቸውን መካድ አይደለም። ይሁን እንጂ በዚህ ክፍል ውስጥ ከቤተ ክርስቲያን ጋር በንጽጽር የቀረበችው እስራኤል፣ በቀድሞ ዘመን እንደነበረችው እስራኤል፣ እንደ አገርና ሕዝብ የተገለጠች መሆኗን ማስተባበል አይቻልም። ከዚህም በላይ በእግዚአብሔር ምርጫም ሆነ እነርሱ ራሳቸው እንደሚያምኑት እስራኤላውያን ከሌላው ሕዝብ የተለዩ «ምርጥ ሕዝብ» መሆናቸው የታወቀ ነው። ከዚህ አንጻር «ምርጠቹ» የሚለው ቃል እነሱን እንደሚመለከት ማሰባችን አግባብነት አለው። በተጨማሪም በዘመን መጨረሻ ስለሚሆን የእስራኤል መሰብሰብ የተነገሩ ትንቢቶች ይኼን እምነታችንን የበለጠ ያጠናክሩልናል።[79] ለምሳሌ በትንቢተ ሕዝቅኤልና በትንቢተ ዘካርያስ እንደተጻፈው፣ እስራኤላውያን እንደሚበታተኑ ብቻ ሳይሆን ከአራቱም ማዕዘን እንደገና እንደሚሰበሰቡ ቃል ተገብቶላቸዋል።[80] ነገር ግን አንዳንዶቹ የትንቢት ተስፋዎች የእስራኤላውያኑን መሰብሰብ፣ ከቁጣው ወይም ከታላቁ መከራ ዘመን በፊት እንደሚሆን የተነገሩ በመሆናቸው ከላይ ላነሣነው አሳብ ማጠናከሪያ ከመሆን ይልቅ ተቃራኒውን አሳብ

[78] ማቴ24:20እንግዲህ ሸሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት ቀን እንዳይሆን ጸልዩ፤
[79] ሐዋ10:44።
[80] ሕዝ5:8-13።ዘካ2:6-7።ሕዝ20:33-38።22:17-22። ሶፎ2:1-2።

የሚደግፉ መስለው ሊታዩ ይችላሉ። ይሁን እንጂ ለእስራኤል የተነገሩ ሌሎች ትንቢቶችና ተስፋዎች፣ እስራኤል ከመከራው በፊት እንደ አገር መሰብሰቧን እንጂ፣ የቀድሞ ዘመን መንፈሳዊ ይዘቷንና ቅርጿን የሚያመለክቱ ባለመሆናቸው በአሁኑና ወደፊት በሚሆነው ነገር መካል የሚያወዛግቡ ሆነው አይታዩም።

እንደሚታወቀው ከጥንት ጀምሮ ለእስራኤላውያን የተነገሩ ብዙ ተስፋዎች እስከ አሁን ገና አልተፈጸሙም። ከታላቁ መከራ በኋላ የሚሆነው የእስራኤል መሰብሰብ ግን በእስራኤላውያን ዘንድ ለዘመናት ሲናፈቁ የቆዩ ተስፋዎች ሁሉ በሙላት የሚፈጸሙበት ዘመን ነው። በመሆኑም በዚያ ዘመን የመለከት ድምፅ ሲነፋ፣ እስራኤላውያን ከአራቱም ማዕዘን ከያሉበት ይሰበሰባሉ። ኢሳይያስም ስለእነዚያ ቀናት ደጋግሞ የተናገረ ሲሆን፣ ከእነዚህ መካል በብዙ ሃይማኖተኞች ዘንድ በመንግሥተ ሰማያት እንደሚሆን የሚታለመው የኢሳይያስ አስራ አንድ የትንቢት ቃል የሚፈጸመው በዚያ ዘመን ነው። ያም ዘመን እውን በሆነ ጊዜ እንዲህ ይሆናል፣

በቅድስቲቱ ከተማ ሆኖ ዓለምን ሁሉ የሚገዛ፣ እውነተኛና ጻድቅ ንጉሥ በምድር ሁሉ ላይ ይነግሣል፤ እሱም፣ ዓይኑ አንዳየች አይፈርድም፣ ጆሮው እንደሰማችም አይበይንም። ለድኾችና ለምስኪኖች ጽድቅንና ፍትህን ያደርጋል። ስለዚህም በእርሱ ዘመን ተኩላ ከበግ ጠቦት ጋር ይኖራል፤ ነብርም ከፍየል ግልገል ጋር ይተኛል፤ ጥጃ፣ የአንበሳ ደቦልና የሰባ ከብት በአንድነት ይሰማራሉ፤ ትንሽ ልጅም ይመራቸዋል፤ ላምና ድብ በአንድነት ይወጣሉ፣ ይገባሉ፤ ልጆቻቸውም አብረው ይተኛሉ፤ አንበሳም እንደ በሬ ገለባ ይበላል፤ ጡት የሚጠባ ሕፃን በአደገኛ የእባብ ጕድጓድ አፍ ላይ ይጫወታል፤ ጡት የጣለም ሕፃን እጁን በእፉኝት ጕድጓድ ይከታል። ውኃ ባሕርን እንደሚሸፍን፣ ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን በማወቅ ትሞላለችና፣ በዚያን ዘመን ማንም በማንም ላይ ጒዳት ወይም ጥፋት አያደርስም፤ <u>በዚያን ቀን እግዚአብሔር፣ እስራኤላውያን ከተሰደዱበት አገር ሁሉ መልሶ፣ ወደ ተስፋይቱ ምድር ያመጣቸዋል፤</u> የተበተኑትን የይሁዳ ሕዝብ ከአራቱም የምድር ማእዘን ይሰበስባቸዋል። በዚያ ጊዜ አስቀድሞ ለአብርሃም ቃል እንደተገባለት ከኤፍራጥስ ወንዝ እንሥቶ እስከ ግብፅ

ደረቅ ወንዝ፣ የእስራኤል ልጆች፣ ይሰበሰባሉ::[81] ታላቁ መከከተም ደንፋል፣ በአሦር የጠፉትና በግብፅ የተሰደዱትም መጥተው፣ በተቀደሰው ተራራ በኢየሩሳሌም እግዚአብሔርን ያመልካሉ::[82]

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን ከተነጠቀች በኋላ በሚከተሉት ሰባት የችግርና የስቃይ ዓመታት የሚደርስባቸውን ጽኑ መከራና ስደት ታግሰው ያለፉ እስራኤላውያን ዳግም የሚሰበሰቡት በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ይመስላል::

ስመንግሥታት ምልክትን ያቆማል፣ ከእስራኤልም
የተሰደዱትን መልሶ ያመጣቸዋል፣ የተበተኑትን የይሁዳ
ሕዝብ፣ ከአራቱ የምድር ማእዘን ይሰበስባል::[83]

[81] ኢሳ11:1-12:: በዚያን ቀን፣ ጌታ አዳን ዘርግቶ እንደ ገና የተረፈውን የሕዝቡን ቅሬታ ከአሦር፣ ከታችኛው ግብፅ፣ ከሳይኛው ግብፅ፣ ከኢትዮጵያ፣ ከኤላም፣ ከባቢሎን፣ ከሐማትና ከባሕር ጠረፍ ምድር ይሰበስባል::

[82] ኢሳ27:12-13:: በዚያ ቀን ከኤፍራጥስ ወንዝ አንሥቶ እስከ ግብፅ ደረቅ ወንዝ፣ እግዚአብሔር አህሉን ያወቃል፣ አናንተም የእስራኤል ልጆች ሆይ፣ አንድ በአንድ ትሰበሰባላችሁ:: በዚያ ቀን ታላቅ መሰከት ይነፋል፣ በአሦር የጠፉትና በግብፅ የተሰደዱትም መጥተው፣ በተቀደሰው ተራራ በኢየሩሳሌም እግዚአብሔርን ያመልካሉ::

[83] ኢሳ11:12::

የሰይጣን ወደ ምድር መጣል

አርሱም ወደ ምድር ተጣለ፣ የአርሱም
መላዕክት ከአርሱ ጋር አብረው ተጣሉ::[84]

ቤተ ክርስቲያን ወደ ሰማይ በምትነጠቅበት ጊዜ፣ ሰይጣን ደግሞ ወደ ምድር የሚጣልበት ሥርዓት ወደፊት እንደሚሆኑ ከሚጠበቁ የመጨረሻው ዘመን ትዕይንቶች መኻል እጅግ የሚናፈቅ ነው:: ይህም ከታላቁ መከራ ጥቂት ቀደም ብለው ከሚሆኑ አበይት ክንውኖች አንዱ ነው:: ሆኖም ሰይጣን ወደ ምድር ከመጣሉ በፊት ከመልአኩ ሚካኤልና ከሠራዊቱ ጋር በሰማይ ወይም በአየር ላይ የበረታ ጦርነት ያደርጋል:: በጦርነቱ ሰይጣንና መላእክቱ በሚካኤልና በመላእክቱ ይሸነፋሉ:: ከዚያ በኋላ በሰማይ ስፍራ ስለማይኖራቸው በቀጥታ ወደ ምድር ይጣላሉ::

ሰው ስለእርሱ ለማወቅ የሚፈልገውን ያህል፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰይጣን ብዙ ነገር አለመባሉ የሚገርም ነው:: ይህ ብቻ ሳይሆን በአንዳንድ ሰዎች «ስለሰይጣን የተነገሩ ናቸው» ተብለው የሚታሰቡ፣ አንዳንድ የቅዱሱ መጽሐፍ ክፍሎች፣ በሌሎች ዘንድ እምብዛም ተቀባይነት የሌላቸው ወይም አወዛጋቢ ሆነው የሚገኙበት አጋጣሚ አለ::[85] ያም ሆነ ይህ፣ በዘመን ፍጻሜ በሚሆኑ ትዕይንቶች ሰይጣን ዋነኛ ተዋናይ እንደሚሆን በግልጥ የተነገረ በመሆኑ፣ ሊስተባበል የማይቻል ሀቅ ነው:: ምንም እንኳ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ሰይጣን ጥልቅና ዝርዝር ነገር ባይጻፍም፣ በተወሰኑ ቦታዎች፣ ስለእሱ ማንነት፣ ስለቀድሞ ተግባሩ፣ አሁን ስለሚሠራው ሥራና ወደፊት ሊያደርግ ስላለው ነገር፣ በማያሻማ ሁኔታ ተነግሮለታል::

[84] ራእ12:9::

[85] ሕዝ28:1-19:: ኢሳ14:12:: አንተ የንጋት ልጅ፣ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፣ አንዳት ከሰማይ ወደቅህ!

አያሌ የመጽሐፍ ቅዱስ መምህራን ከእነዚህ ክፍሎች በመነሣት፣ ሰይጣን አስቀድሞ በእግዚአብሔር ክብር እንደነበረና ሲፈጠርም የመልአክ ተፈጥሮና ባሕርይ የነበረው ስለመሆኑ ያስተምራሉ። ዳሩ ግን በአንድ የሆነ ወቅት ለእግዚአብሔር ትክክለኛ አምልኮና ክብርን ስላልሰጠ፣ ከክብሩ ተዋርዶ ወድቋል። ቆይቶም በሆነ አጋጣሚ በገነት ተገኝቶ አዳምና ሔዋንን አሳታቸው። ከዚህም ሌላ፣ በኢዮብ መጽሐፍ ላይ እንደተጠቀሰው በእግዚአብሔር ፊት ደጋግሞ እየቀረበ *«በምድር ላይ ሉንተን ከልቡ የሚያመልክ አንድ ሰው እንኳ የለም»* ይለው እንደ ነበርና እግዚአብሔር ግን በኢዮብ ላይ በነበረው እምነት ከሰይጣን ጋር ሲወራረድበት ይታያል። በዘካርያስ መጽሐፍ ላይ ደግሞ ካህኑን ኢያሱ ሊያሳጣውና ሊከሰው በፈለገ ጊዜ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ብርቱ ተግሳጽ እንደተቀበለ ተጽፏል።[86]

በአዲስ ኪዳን መግቢያ ላይ፣ ኢየሱስ በጸምና በጸሎት የቆየባቸውን አርባ ቀናት በፈጸመ ጊዜ፣ ሰይጣን ወደእርሱ በመቅረብ በልዩ ልዩ ፈተና የፈተነው ሲሆን፣ ጌታ ግን ከመጽሐፍት በመጥቀስ በሁሉም ረትቶታል።[87] ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ ባገለገለባቸው የተወሰኑ ዓመታትም አያሌ ሰዎችን ከተያዙበት እስራት ነፃ በማውጣት በሰይጣን መንግሥት ሕልውና ላይ ነግሦ ታይቷል።[88] አጋንንቱም በታላቅ ድምፅ እየጮኹ *«ጊዜአችን ሳይደርስ ልታጠፋን መጣህን?»* ይሉት ነበር። ምንም እንኳ በእርሱ ላይ አንዳች ሥልጣን ያልነበረው ቢሆንም እስከተወሰነለት ጊዜ ድረስ፣ የዚህ ዓለም ገዢ እንደ ሆነ ጌታ ኢየሱስ ተናግሯል።[89] ለምሳሌ በይሁዳ በኩል አድሮ ኢየሱስ ክርስቶስን፣ ለካህናት አለቆች ተላልፎ እንዲሰጥና እንዲገደል ያደረገ እሱው ነበር፤ ይሁን እንጂ ኢየሱስ በተሰቀለ ጊዜ በዓለምና በሰው ላይ የሆነው፣ ሰይጣን ካሰበው ፍጹም ተቃራኒ በመሆኑ ለዘመናት ሲያልመው የኖረውን ማሳካት ሳይችል ቀርቷል።

[86] ኢዮብ ም፩ እና ም፪። ዘካር፫፡፩-፪።
[87] ማቴ፬፡፩-፲፩። ማር፬፡፩-፲፫።
[88] ማቴ፰፡፳፰-፴፬።፲፩፡፲፬-፳፭።፲፪፡፳፪-፳፱።ማር፫፡፳፫-፴፯።፭፡፩-፲፯።ሉቃ፰፡፳፮-፳፯።
[89] ዮሐ፲፪፡፴፩።፲፬፡፴። ማቴ፰፡፳፱። የእግዚአብሔር ዕድ ሆይ፣ ከእኛ ምን ጉዳይ አለህ?

ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሠራው ሥራ ሰይጣን፣ ለዘመናት ሰዎችን ለመቃወምና ለመክሰስ ሲጠቀምበት የነበረ የዕዳ ጽሕፈት ከነሕግጋቱ ተደምስሶ፣ ከመንገድ እንዲወገድ ተደርጓል። ሞትን ድል አድርጎ በተነሣ ጊዜም የኃጢአት መውጊያውን ገፎ ባዶ እጁን ሰዶታል። መች ይህ ብቻ! የአለቅነቱንና የባለሥልጣንነቱን ማዕረግ በመግፈፍ በመስቀሉ ድል ነስቶ በአደባባይ እያዋረ እንዲታይ አድጎታል[90] እጅግ የሚደንቀው ግን፣ የዚህ ዓለም ገዢ የተባለው ሰይጣንና ከጀሌዎቹ አንዳቸውም ክርስቶስ ሊያደርግ ያለውን አለመረዳታቸው ነው።[91]

> ከዚችም ዓለም ገዦች አንዱ እንኳ ይህን ጥበብ
> አላወቀም፣ አውቀውስ ቢሆኑ የከብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር፤

ተመልከቱ! ክርስቶስ በተለይ ለእኛ ከአሕዛብ ወገን ለሆንን አማኞች እግዚአብሔር ከዘመናት በፊት አስቀድሞ ለክብራችን የሰወረው የእግዚአብሔር ጥበብ ሚስጥር ነው። ይኼም ሚስጥር አሁን በቅዱሳን ሐዋርያቱና ነብያቱ የተገለጠውን ያህል ባለፉት ዘመናት ለማንም አልተገለጠም። ሚስጥሩም አሕዛብ በወንጌል አማካኝነት ከእስራኤል ጋር አብረው ወራሾች፣ አብረው የአንዱ አካል ብልቶች፣ እንዲሁም በክርስቶስ ኢየሱስ በሆነው ተስፋ አብረው ተካፋዮች መሆናቸው ነው። በአሁኑ ጊዜ የሆነው የእግዚአብሔር አሳብም፣ ላለፉት ዘመናት ከፍጥረታት ሁሉ ተሰውሮ የነበረው የዚህ ሚስጢር አሠራር በቤተ ክርስቲያን በኩል ብዙ ገጽታ ያለው የእግዚአብሔር ጥበብ በሰማያዊ ስፍራ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት ይታወቅ ዘንድ ነው።

መንፈስ ቅዱስ ከመሰጠቱ በፊት፣ ያለተስፋና ያለእግዚአብሔር የነበሩት አሕዛብ፣ ዛሬ በየስፍራው የሰይጣንን መንግሥትና ሥርዓት ለማፍረስ ኃይል የሆነላቸው ከዚህ ሚስጥር መገለጥ የተነሣ ነው።[92] ይኼም ሚስጥር የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእርሱ በሚያምኑ ሰዎች ውስጥ ሁሉ መሆኑ ነው።

[90] ቆሳ፪፡፲፬፤፲፭። ፩ኛቆር፲፭፡፶፭፤፶፮። ሞት ሆይ መንደፊያህ የት አለ?
[91] ፩ቆር.፪:፰
[92] ሮሜ፲፮፡፳፭-፳፮። ቆር፪፡፯፤፰። ኤፌ፫፡፫-፱። ቆሳ፩፡፳፮፤፳፯።

ከዚያን ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ፣ ሰይጣን በአየር ላይ እንዲቆይ ጥቂት ጊዜ ተሰጥቶታል። በእርግጥ በዚህ ዘመን እሱ በእግዚአብሔር ፊት ቀርቦ አማኞችን የሚከስበት ዕድሉ ጠባብ መስሎ ቢታይም፣ ከዚህ ተግባሩ ሙሉ ለሙሉ እንደታቀበ እርግጠኛ መሆን የሚቻለው ግን በመጨረሻው ዘመን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ምድር ከተጣለ በኋላ ነው። ሆኖም በዚህ ዘመን ያሻውን ሁሉ እንዳይሠራና በወደደው ጊዜ በሙላት እንዳይገለጥ የሚከለክለው ኃይል አለ። ይኼም ከልካይ በቤተ ክርስቲያን በኩል በሥልጣን የሚጠራው የጌታ ኢየሱስ ስም እንዲሁም በውስጥዋ የሚሠራው የእግዚአብሔር መንፈስ ነው። ይሁን እንጂ አሁንም እንኳ የዐመፅ ሚስጥር በስውር እየሠራ እንደ ሆነ መካድ አይቻልም፣ ለዚህም በዚህ ዘመን በተለያየ መንገድ ከእውነተኛው መንገድ አስቶ፣ ወደ ጥፋት የሚያጣድፋቸውን ሰዎች በዋቢነት መጥቀስ ይቻላል።[93]

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተመለከተው፣ የሰይጣን አሠራር የራሱ የሆነ አወቃቀር ያለውና የሥልጣን ተዋረዱም የተደራጀ ነው። በዚህ መሠረት ቢያንስ ሦስት ዓይነት እርከኖችን የሚከተል ይመስላል። ቀዳሚዎቹ፣ የጨለማ ዓለም ገዢዎች ሲባሉ፣ ከእነርሱ ቀጥሎ ያሉት ደግሞ ኃይላት ይሰኛሉ፣ የቀሩት የእርኩሳን መናፍስት ጭፍሮች ወይም ሠራዊቶች ናቸው። ሰይጣን ሰዎች ለእውነት እንዳይታዘዙና በክርስቶስ ብቻ ወደሆነው ድነት እንዳይደርሱ በብዙ ይተጋል። ከዚህ የተነሣ በክርስቶስ ያልሆኑ ሁሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተጽዕኖው ሰለባ ሆነው ይኖራሉ። ከመጀመሪያው ጀምሮ በተንኮልና በሽንገላ የሚሠራ እንደ መሆኑ፣ አማኞች እንኳ በምድር በሚቆዩባቸው ዓመታት በተንኮሉና ማታለሉ ተጽዕኖ ስር እንዳይወድቁ መጠንቀቅ ይገባቸዋል። ደግሞም ከቆው ቀን ሲመጣ መቋቋም እንዲችሉ፣ የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ መልበስ ይጠበቅባቸዋል።[94] አማኞች ዘወትር ሳይዘናጉ ይኼን የሚፈጽሙ ከሆነ፣ በየትኛውም ጊዜ ጸንተው መቆም ይችላሉ።

[93] 2ኛተሰ2፡6፣7።
[94] ኤፌ6፡11፣12።2ኛቆር4፡3። 2ኛቆር11፡3። ኤፌ6፡13-17።

ታላቁ መከራ ከመሆኑ አስቀድሞ ቤተ ክርስቲያን በምትነጠቅበት ቅጽበት ሰይጣን ደግሞ ወደ ምድር ይጣላል። ይህም በሰማይ በሚሆን ጦርነት ሚካኤልና መላእክቱ ከዘንዶውና ከመላእክቱ ጋር ከተዋጉ በኋላ የሚፈጸም ነው። በዚያን ጊዜም ዘንዶው ከነመላእክቱ ድል ስለሚመታ በሰማይ የነበረውን ስፍራ በግድ ይለቃል። ዓለምን ሁሉ ሲያስት የኖረው ታላቁ ዘንዶ ወይም «የጥንቱ እባብ» የተባለው ሰይጣን ወይም ዲያቢሎስ ወደ ምድር ይጣላል።

የሰይጣን በዚህ ሁኔታ ወደ ምድር መጣል፣ ለዘመናት የእግዚአብሔርን ማዳን ሲጠባበቁ ለኖሩ አማኞች ታላቅ የምስራች ነው። በወቅቱ በሰማይ ከሚሆነው አስደናቂ ነገር የተነሣ በዚያ የሚገኙ ሁሉ እጅግ ደስ ይላቸዋል። ይኼ በሰማይ የሚሆነው ታላቅ ነገር ደግሞ፣ የበጉ ሠርግ እንደ ሆነ ከዚህ በፊት ያየነው ነው። ያን ጊዜም ከሰማይ «አሁን የአምላካችን ማዳን፣ ኃይልና መንግሥት፣ የክርስቶስ ሥልጣንም መጥቶአል። ቀንና ሌሊት በአምላካችን ፊት ሲከሳቸው የነበረው የወንድሞች ከሳሽ ተጥሏልና። እነርሱም በበጉ ደም፣ በምስክርነታቸውም ቃል ድል ነሡት፤ እስከ ሞት ድረስ ሰነፍሳቸው አልሳሱም። የሚል ድምፅ ይሰማል።[95]

ዳሩ ግን ሳይነጠቁ በምድር ለሚቆዩ ሰዎች ዘመኑ፣ የወዮታ ዘመን ይሆናል። ምክንያቱም ዲያቢሎስ ጥቂት ዘመን ብቻ እንደቀረው አውቆ በታላቅ ቁጣ ወደእነሱ የሚወርድበት ዘመን ስለሆነ ነው። ዘንዶውም ወደምድር እንደተጣለና ቤተ ክርስቲያንንም ሊያገኛት እንደማይችል ሲያውቅ፣ እንዲሁም የቀረው ጊዜ አጭር መሆኑን ሲረዳ፣ ከድሮ ጀምሮ ጠላቱ የሆነችውንና ወንዱን ልጅ የወለደችውን «ሴት» ማሳደድ ይጀምራል። ሴቲቱም በበረሀ ወደተዘጋጀላት ስፍራ በርራ መሄድ እንድትችል ሁለት የታላቁ የንስር ክንፎች ይሰጣታል። ይህም የሆነው በዚያ ከእባቡ ፊት ርቃ፣ ለሦስት ዓመት ተኩል ለሚሆን ጊዜ በእንክብካቤ እንድትኖር ነው። ይህቺ በዘንዶው ብርቱ ፈተናና ስደት የሚገጥማት ሴት «እስራኤል» እንደሆነች ከዚህ በፊት ማውሳታችንን ያስታውሷል። በወቅቱ ሰይጣን እስራኤል፣ በጎርፍ

[95] ራእ12፡10-12።

ተጠራርጋ እንድትወሰድ፣ እንደ ወንዝ ያለ ውኃ ከአፉ ይተፋል። ምድር ግን አስራኤልን ትረዳታለች፣ አፏንም ከፍታ ዘንዶው ከአፉ ያፈሰሰውን ወንዝ ትውጠዋለች። በዚህ ጊዜ ዘንዶው እጅግ ተቆጥቶ ከቀሩት ልጆችዋ ጋር ሊዋጋ ይሄዳል። እነርሱም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የሚጠብቁና የኢየሱስን ምስክር አጥብቀው የያዙ ናቸው።[96]

ዘንዶው ወደ ምድር የሚጣልበት ይኼ ጊዜ ደግሞ ዓለም ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ በአስቸጋሪነቱ አቻ የማይገኝለት ጊዜ ሲሆን «ታላቁ መከራ» ወይም «የያዕቆብ የመከራ ዘመን» በመባል ይታወቃል። በነዚያ ዘመናትም ዘንዶው፣ በእርሱ ኃይልና ሥልጣን በሚሠሩ በሁለት ሰዎች ውስጥ ሆኖ ምድርን በሙላት ይገዛል። እነርሱም «ሐሰተኛው ክርስቶስ እና ሐሰተኛው ነብይ» በመባል የሚታወቁት ናቸው። በወቅቱ ምድር ከዚያ በፊት ዐይታ የማታውቀው ዓይነት ታላቅ መከራ፣ ስቃይና ችግር ለማየት ትገደዳለች። ቤተ ክርስቲያን ግን ተነጥቃ ስለምትወሰድ፣ ሰይጣን ለጊዜው ከልካይ የሌለው መስሎ ይታያል። በምድር ላይ ለሚደርሰው ጥፋትና መከራ ሁነኛ ተዋናይ እርሱው ይሆናል። ለዚህም የጥልቁ ጉድጓድ መልአክ የተባለውና በዕብራይስጥ «አብዶን» በግሪክ ደግሞ «አጵልዮን» የሚባለው የአጥፊው ሠራዊት ንጉሥ ዋነኛ ተጠቃሽ ነው።[97]

ቤተ ክርስቲያን ከተነጠቀች ከጥቂት ጊዜአት በኋላ፣ ጌታ ኢየሱስ ከቅዱሳኑ ጋር ወደምድር ይመለሳል። ሰይጣንም የምድር ነገሥታትን አስተባብሮ ከእርሱ ጋር ለመዋጋት ይሞክራል። ዳሩ ግን በአጭር ጊዜ ውስጥ አሳፋሪ ሽንፈት ይከናነብና ምድርን ሁሉ ለነገሥታት ንጉሥ፣ ለጌቶች ጌታ ለሆነው ለኢየሱስ ክርስቶስ ይለቃል። በዳንኤል መጽሐፍ ላይ እጅ ሳይነካት ከተራራው ላይ ተፈንቅላ እንደመጣችው ታናሽ ድንጋይ፣ የኢየሱስ መንግሥት የዓለም መንግሥታትን ሁሉ ፈጭታና መታሰቢያቸው እስከማይገኝ ድረስ አስወግዳ፣ ብቻዋን ለዘላለም ትመሠረታለች። ሰይጣን ዲያቢሉስም ተይዞ ለሺ ዓመት

[96] ራእ12:1217።ዲያቢሉስ ጥቂት ዘመን ብቻ እንደቀረው ስላወቀ፣በታላቅ ቁጣ ተሞልቶ ወደ እናንተ ወርዷልና . . .
[97] ራእ9:11።

ያህል ይታሠራል። ከእሱ ጋር አብረው ሲሠሩ የነበሩት፣ ሐሰተኛው ክርስቶስና ሐሰተኛው ነብይ ደግሞ ወደዘላለማዊ እሳት ወይም ወደ ገሃነመ እሳት ይጣላሉ።

ሺህ ዓመቱ ሲፈጸም ሰይጣን ለጥቂት ጊዜ ይፈታል። በዚያን ጊዜም የዐመጻ ተግባሩን ለመቀጠል ይሞክራል፤ ነገር ግን አይሳካለትም። እናም እንደገና ተይዞ በገሃነመ እሳት ውስጥ ይጣላል። እግዚአብሔር የእርሱ ለሆኑት ምርጠቹ ዓለም ሳይፈጠር ያዘጋጃትን መንግሥት ሲያወርስ፣ በአንጻሩ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከሰይጣን ጋር በግብር የተባበሩና ምርጫቸው ያደረጉት ሁሉ እርሱን ተከትለው ለዘላለም በገሃነመ እሳት ውስጥ ይጣላሉ።[98] ይህ ሁሉ የሚሆነው በታላቁ የነጩ ዙፋን ፍርድ ወቅት ነው።

[98] ራእ19:11-20:10።

ምዕራፍ ፲፬

ታላቁ መከራ

የፍርሀትና የሽብር ጩኸት ተሰምቶአል ሰላምም የለም። አስቲ ጠይቁ፤ ተመልከቱም፤ ወንድ መውለድ ይችላል? ታዲያ ወንድ ሁሉ ምጥ እንደያዛት ሴት፣ እጁን በሆዱ ላይ አድርጎ፣ የሰውስ ሁሉ ፊት ጠቁሮ የማየው ስምንድን ነው? ያ ቀን ምንኛ አስጨናቂ ይሆናል! እንደዚያም ያለ አይኖርም፤ ስያዕቆብ የመከራ ጊዜ ነው፤ ነገር ግን ይተርፋል።[99]

ታላቁ መከራ የሚባለው በሰባኛው ሱባኤ ውስጥ እንዲሆን የተቀጠረ፣ አሰቃቂ የመከራና የችግር ወቅት ነው። ይህም በተለይ ከሰባኛው ሱባኤ አጋማሽ በኋላ እንደሚሆን የሚጠበቅ ቢሆንም፣ ሰባኛው ሱባኤ ከገባ ጀምሮ አብሮ የሚቆጠር ጊዜ ነው። ሆኖም በዚህ ወቅት ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ስለማትኖር ወይም ተነጥቃ ጌታን በአየር ለመቀበል ወደ ሰማይ ስለምትሄድ ይህ መከራ እርሷን የሚመለከት አይደለም። በአንጻሩ ዘመኑ ለእስራኤል የመከራ ወቅት እንደሚሆን ይጠበቃል። እንዲያውም በአንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ዘመኑ «የያዕቆብ መከራ» ተብሎ የተጠራው እስራኤልን በተለይ የሚመለከት ስለሆነ ይመስላል። ከዚህ በተጨማሪ ወቅቱ፣ የጭንቀት ጊዜ፣ የበቀል ቀን፣ የጌታ ቀንና የእግዚአብሔር የቁጣ ቀን ተብሎ ተጠርቷል።[100] ሆኖም በእነዚያ በፍጻሜው ዘመን በሚቆጠሩ ሰባት ዓመታት ውስጥ በምድር ላይ የሚሆነው መከራ ምን ያህል አስከፊና አሰቃቂ ሊሆን እንደሚችል ቀድሞ መገመት እንኳ አይቻልም።

[99] ኢር30፡7።
[100] ኢር30፡6-8። ዘጸ4፡30።ኢሳ34፡8።ዳን12፡1።1ኛተሰ5፡2። ሶፎ1፡18።ሮሜ2፡5።

ከታላቁ መከራ
በፊት ያለ የመከራ ጊዜ

. . . ይህ ሁሉ የምጡና የጣሪ መጀመሪያ ነው፣

እኔን ከመውለዷ በፊት የነበሩት ጥቂት ወራት፣ እጅግ አስጨናቂ ጊዜአት ሆነውባት እንደነበር እናቴ ነግራኛለች። ከአራት ዓመት በፊት፣ ታላቅ እኅቴን ስትወልድ፣ ትንፋሽዋን ሳትመልስ ለሰዓታት በማማጥዋ፣ በጤናዋ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶ ነበር። ይኼን ደኅና አድርገው የተረዱት ሐኪሟ ሕይወቷን የምትፈልግ ከሆነ፣ ያለምንም ማመንታት ጽንሱን ከሆድዋ ማስወጣት እንዳለባት አስጠነቀቋት። እሷም ብትሆን አምጣ ለመውለድ የሚያስችል አስተማማኝ የጤንነት ሁኔታ ላይ እንዳልነበረች ታውቅ ነበር። ሆኖም ግና፣ ለገና አራተኛ ልጅዋ «ወንድ ይሆንልኝ ይሆናል» ብላ ተስፋ አድርጋ ስለሳላች ብቻ፣ የሐኪሙን ቃል ለመቀበል እንቢ ብላ እነዚያን ረጅም ወራት በሰቀቀን ለማሳለፍ ተገደደች። እንደ ዕድል ሆኖ፣ እሷም ምንም ሳትሆን፣ እኔም ወንድ ሆኜ ተወለድኩላት። በእርግጥ እኔ የምጥ ጣር ምንነትን ያወቅሁት በገዛ እናቴ ነው።

✡ 🕮 ✡

ኢየሱስ ታላቁ መከራ ከመምጣቱ በፊት ያለውን ጊዜ በተመለከተ ለደቀ መዛሙርቱ ሲያስተምር፣ ጊዜው የምጥ ጣር ጊዜ እንደሚሆን መናገሩ የወቅቱን አስጨናቂነት የሚገልጥ ሲሆን፣ ታላቁ መከራ ከመሆኑ በፊት ባለው ያልተወሰነ ዘመን፣ ከእርሱ ጋር ሲነጻጸር ቀላል የሚመስል የመከራ ወይም የጭንቅ ጊዜ እንደሚኖር ይጠቁማል። ኢየሱስም ስለ ታላቁ መከራ በተናገረበት ወቅት «በዚያን ጊዜ፣ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ አስከ ዛሬ ድረስ ሆኖ የማያውቅ፣ ከዚያም በኋላ የሚስተካከለው የለለ፣ ታላቅ መከራ ይሆናል። ቀኖቹ ባያጥሩ ኖሮ ሥጋ ሰባሽ ሁሉ ባልተረፈ ነበረ፤ ስስተመረጡት ሲባል ግን አነዚያ ቀኖች ያጥራሉ» ብሎ ነበር። ከዚህ በፊት እንደተመለከትነው ዘመኑ ለእስራኤል ከተቀጠሩት ሱባኤዎች በስልሳ

ዘጠነኛውና በሰባኛው ሱባኤ መኻል የሚገኝ የቤተ ክርስቲያን ዘመን እንደሆነ ነው የሚታመነው። ከዚህ አንጻር ይህ ያለንበት ዘመን ከታላቁ መከራ አስቀድሞ ያለና ቤተ ክርስቲያንም በልዩ ልዩ መከራ የምታልፍበት ዘመን ነው፣ ለማለት ይቻላል። ደግሞም ኢየሱስ፣ በእነዚያ ዘመናት ስለሚሆኑ ምልክቶች ሁሉ ከዘረዘረ በኋላ «ነገር ግን መጨረሻው ገና ነው. . . ይህ ሁሉ የምጡና የጣረ መጀመሪያ ነው» ብሎ ማስጠንቀቁ፣ ይኼ ከታላቁ መከራ በፊት የሚሆነው ዘመን፣ እርጉዝ ሴት ወደ ተፋፋመው ምጥ ከመግባቷ በፊት ያለውንና ልጁም መወለዱ ላይቀር «መጣሁ፤ ቀረሁ» እያለ የሚያስፈራራበትን የምጥ ጣር መጀመሪያን የሚመስል ነው።

ስለዚህ አማኞች ከታላቁ መከራ በፊት በዓለም ሁሉ የሚሆነውን የመከራ ጊዜ፣ አበይት ምልክቶች በትኩረት የሚያጠኑ ከሆነ፣ ዘመኑ ወደ ፍጻሜው ምን ያህል እየቸኮለ እንደሆነ ለመገንዘብ ይችላሉ። ከዚህ አንጻር ያለንበትን ዘመን፣ በታሪክና በትንቢቱ ቃል አስተውለን ስንመለከተው ወደተፋፋመው ምጥ ምን ያህል እየዘለቅን እንደሆነ በቀላሉ እንረዳለን። በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 ላይ ኢየሱስ፣ ስለእነዚያ የመከራ ቀናት ምንነት የሚጠቁሙ መሠረታዊ ነገሮች ተናግሯል። በዚሁ መሠረት ከቁጥር 4 እስከ ቁጥር 14 ያለው፣ በቤተ ክርስቲያን ዘመን ስለሚሆን መከራ ሲናገር፣ ከቁጥር 15 እስከ ቁጥር 31፣ በታላቁ መከራ ዘመን ስለሚሆኑ ጉዳዮች ይዘረዝራል። እርግጥ ነው፣ በታላቁ መከራ ውስጥ ከሚሆኑ አበይት ምልክቶች የሚበዙት፣ በቤተ ክርስቲያን ዘመን ጭምር የሚሆኑ በመሆናቸው ግራ የሚያጋቡ መስለው ይታያሉ። ሆኖም ምልክቶቹ በትኩረት ከተጠኑ አንድነትና ልዩነታቸው ያን ያህል የሚያወዛግብ አይደለም። በዚሁ መሠረት አስቀድሞ የሚሆኑትን ምልክቶች በአራት ከፍሎ ማየት ይቻላል። ከዚህ ቀጥሎ እያንዳንዳቸውን በዝርዝር ለመመልከት እንሞክራለን።

ሐሰተኞች ሃይማኖትን፣
መሲሃችንና ጓደኞችን...

ማንም አንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ፤ ብዙዎች «እኔ ክርስቶስ ነኝ» በማለት በስሜ ይመጣሉና፤ ብዙዎችንም ያስታሉ።[101]

ከጥቂት ዓመታት በፊት ጓደኞቼ የሚካፈሉበት የመድሃኔ ዓለም ጽዋ ማኅበር ነበራቸው፤ በኅብረቱ አባል ከነበሩ ልጆች አብዛኛዎቹ ሃያ ዓመት እንኳ ያልሞላቸው ወጣቶች የነበሩ ሲሆን፣ በመንፈሳዊ ሕይወታቸውም ያልበሰሉ ነበሩ። ታዲያ ከማኅበርተኞቹ አንዱ፣ ድንገት አእምሮው ስለተነካ፣ የሆነ ያልሆነ ነገር መዘላበድ ጀመረ፤ ከዚህ ውስጥ በተለይ አንድ ቀን ያደረገው ዛሬም ድረስ ባስታወስነው ጊዜ ፈገግ ያሰኘናል። ልጁ ድንገት ተነሥቶ «እኔ ኢየሱስ ነኝ» ማለት ጀመረ፤ ከዚያም ከጽዋው ኅብረት አባላት አስራ ሁለቱን ጠቅሶ «*ደቀ መዛሙርቴ እንድትሆኑኝ መርጫችኋለሁ*» አላቸው። ቀጠለና አንዱን «*አንተ ጴጥሮስ ነህ*» አለው። ይኼን ሁሉ እየተሳቀቁ ያዩ እናቱም ደንግጠው «*ምነው ልጄ፣ ምን ነካብኝ*» ቢሉት «*ድንግል ማርያም ካንቺ ጋር ምን አለች? ጊዜዬ እኮ ገና አልደረሰም*» ብሏቸው ቁጭ አለ።

✡ 🕮 ✡

ባለንበት፣ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ብዙዎች «*እኔ ክርስቶስ ወይም መሲሁ ነኝ*» በማለት እንደሚመጡ ኢየሱስ በተደጋጋሚ ተናግሯል። በታላቁ መከራ ጊዜም ልክ እንደዚሁ ይሆናል። ነገር ግን በታላቁ መከራ ዘመን የሚነሣው «ክርስቶስ ነኝ» ባይ አንድ ሲሆን፣ በእጁ የሚያደርገው ምልክትና ድንቅም የተመረጡትን እንኳ ሊያስት እስከሚችል ድረስ የተለየ ጉልበት ያለው ነው። ይህ ነገር ደግሞ በዳንኤል መጽሐፍ ላይ ከተጻፈውና በተቀደሰው ስፍራ ከሚቆመው «የጥፋት እርኩሰት» ጋር በቀጥታ የተቆራኘ እንደሆነ ግልጥ ነው።

[101] ማቴ 24:5።

ከታላቁ መከራ በፊት ባለው ዘመን እውነተኛ ክርስቲያኖች በዓለም ሁሉ እጅግ የተጠሉ ስለሚሆኑ እስከ ጊዜው ድረስ ልዩ ልዩ ፈተና፣ ስደትና መከራ እየተቀበሉ ይቆያሉ። በዚያ ላይ ሐሰተኞቹ «ነብያትና መሲሆች» አመጣጣቸው በብዙ ምልክቶችና ድንቃ፣ ድንቅ የታጀበ ስለሚሆን፣ ብዙ ሰው እውነቱ የቱ እንደሆነ ለመለየት ይቸገራል። አንዳንዶችም ሃይማኖታቸውን እስከወዲያኛው በመካድ ወዳጆቻቸውን እንኳ አሳልፈው የሚሰጡበት ሁኔታ እንደሚኖር ይጠበቃል።

በነዚያ ዘመናት ከየስፍራው የሚነሡ ሐሰተኛ ነብያትና አስተማሪዎች ሕዝቡን ከእውነተኛው መንገድ ስለሚያስቱ እግዚአብሔርን መፍራት ከምድር ላይ ይጠፋል። መልካም የሥነ ምግባር እሴቶች እየላሸቁ ስለሚሄዱ፣ ብዙ ሰው እንደ አንሰላ መኖር ይጀምራል። በምድር ላይ ክፋት ስለሚበዛ ሰዎች ለገዛ ቤተሰቦቻቸው የሚኖራቸው ፍቅር እንኳ እጅግ ይቀዘቅዛል። ወላጆችም ለልጆቻቸው ፍቅር የሌላቸው ሲሆኑ፣ ልጆችም ወላጆቻቸውን የማይታዘዙና አክብሮት የማይታይባቸው ሆነው ያድጋሉ። በተለይም መጨረሻው እየቀረበ ሲመጣ ቀኖቹ እጅግ የሚያስጨንቁ ይሆናሉ።[102]

ግለኝነት እጅግ ይገናል፤ ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱበት መጠን በየጊዜው ይጨምራል፤ እያንዳንዱ ሰው ፍላጎቱን ለሚሟላት ሊኖረው የሚገባ ዋነኛ ነገር እሱ ብቻ እንደሆነ አድርጎ ስለሚቆጥር፣ ለገንዘብ ያለው ፍቅር ይንራል። ይህ ብቻ ሳይሆን የመጨረሻው ዘመን ሰዎች፣ ትምክህተኞች፣ ትዕቢተኞች፣ ተሳዳቢዎች፣ የማያመሰግኑ፣ ቅድስና የሌላቸው፣ ለዕርቅ የማይሸነፉ፣ ሐሜተኞች፣ ራሳቸውን የማይገዙ፣ ጨካኞች፣ መልካም የሆነውን የማይወዱ፣ ከዳተኞች፣ ችኩሎች፣ በከንቱ በትዕቢት የተወጠሩ፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ። ታዲያ ከሁሉ አስገራሚው ነገር፣ ብዙ ሰዎች የሃይማኖት መልክ ያላቸው ሆነው ኃይሉን ግን ጨርሶ የካዱ ሆነው መገኘታቸው ነው። ይኼ ሁሉ የሥነ ምግባር ዝቅጠትና ኃይል ማጣት ደግሞ የሚከሰተው በየጊዜው ከሚገለጡ ሐሰተኛ ሃይማኖቶች፣ ሐሰተኛ

[102] 2ኛጢሞ1-5።

ነብያትና ሐሰተኛ አስተማሪዎች የተነሣ ነው። መቼም ቢሆን የሐሰተኞች ትንቢትና ትምህርት በከንቱ እንደሚያጓጓ ነገር ግን ውኃ እንደሌለበት ባዶ ደመና ብቻ ነው። ይኼም ነገር ብዙ ሰው እውነተኛና ርትዕት በሆነችው እምነት ጨርሶ ተስፋ ቆርጦ ቸልተኛ እንዲሆን የሚጋብዝ ሲሆን፣ ከዚያ ሲያልፍ የእግዚአብሔርን ኃይል እንዲክድና አጭበርባሪ እንዲሆን የሚያበረታታ ነው።[103]

ከየትኛውም ዘመን ይልቅ፣ በአሁኑ ጊዜ በዓለማችን ላይ እጅግ ብዙ እምነት ወይም ሃይማኖቶች እንዳሉ እያየን ነው። እያንዳንዱም ሃይማኖት የራሱ የሆነ መሠረተ እምነት ያለው ሲሆን፣ ነብያቱና አስተማሪዎቹም *«ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚያደርሰው እውነተኛ መንገድ ይኸውና»* በማለት ይናገራሉ። ከነዚህ ውስጥ የሚበዙት ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን በከፊል የሚቀበሉ ቢሆኑም፣ ከአብዛኛዎቹ ቅጥር ግቢ ግን ክርስቶስ ተገፍቶ በውጪ ነው ያለው። ሆኖም ይኼን የሚያስተውል በዚያ አለመኖሩ የመጨረሻው ዘመን ድንዛዜ ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ የሚያሳይ ነው።

[103] 2ኛ2:2-21።

ጦርነትና
የጦርነት ወሬ

104

ስለ ጦርነትና ጦርነትን የሚያናፍስ ወሬ ትሰማላችሁ፤ ...
ሕዝብ በሕዝብ ላይ፣ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣል።

ኢየሱስ፣ እርሱ ከመምጣቱ በፊት ባሉት ዘመናት፣ የጦርነት ዜና ተደጋግሞ እንደሚሰማና ሕዝብ በሕዝብ፣ መንግሥት፣ በመንግሥት ላይ እንደሚነሣ ተናግሯል። በመሆኑም በዚህ ዘመን፣ የእነዚህ ነገሮች በተደጋጋሚ መከሰት የሚሰጠን የተለየ ትርጉም አለ ማለት ነው። ባለፉት መቶ ዓመታት የታዩ ምልክቶች ቀኑ ምን ያህል እንደቀረበ የሚያስረዱ ናቸው። በተለይ በ1914 የተቀሰቀሰው የ1ኛው የዓለም ጦርነት፣ ለዚህ ዓይነተኛ ምልክት ሆኖ የሚጠቀስ ነው። ጦርነቱ ለምድር፣ አዳዲስ ነገሮች ይዞላት እንደመከሰቱ፣ ጦርነቱ የተደረገበት ብቻ ሳይሆን፣ ከጦርነቱ በኋላ ያሉት ዓመታት ትኩረት ይሰባሉ።

በወርሀ ጁን 1914 «አርክዱክ ፍራንዝ ፈርዲናንድ» የተባለ የኦስትሪያው ልዑል «ጋቭሪሉ ፕሪንሲፕ» በተባለ አክራሪ ሰርቢያዊ እጅ ይገደላል። ወዲያው፣ አስትሪያ በሰርቪያ ላይ ጦርነት ስታውጅ፣ የሁለቱ ወዳጅ የሆኑ መንግሥታት በየፊናቸው ከወዳጆቻቸው ጎን ቆመው ለመፋለም ይሰናዳሉ። በዚያው ሰሞን ጀርመን ደግሞ ቤልጂምን፣ ፈረንሳይንና ሉክዘምበርግን መውረሯ፣ አስትሮ-ሀንጋሪም በሰርቢያ ጥቃት ስለ ተፈጸመባት፣ እንዲሁም ራሺያ፣ ፕሩሺያን መተንኮስዋ፣ ለጦርነቱ መቀስቀስና መስፋፋት ምክንያት እንደሆነ ይነገራል። ከ1914 እስከ 1918 ድረስ የቆየው የ1ኛውን የዓለም ጦርነት ልዩ የሚያደርገው፣ ከኢየሱስ ትንቢት በኋላ፣ ዓለም እንዲህ ያለ ሙሉ ጦርነት ዓይታ የማታውቅ በመሆንዋ ነው። እርግጥ ነው፣ ከዚያ በፊትም ቢሆን በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች በርካታ ጦርነቶች መደረጋቸው አይካድም፤ ሆኖም በምንም መመዘኛ ከ1ኛው የዓለም ጦርነት ጋር

[104] ማቴ 24:6-7::

የሚስተካከሉ አልነበሩም። ጦርነቱ እስከ 2ኛው የዓለም ጦርነት ድረስ «የዓለም ጦርነት» ሲባል የቆየ ሲሆን፣ ከዚህም ሌላ «ታላቁ ጦርነት» እና «የጦርነቶች ሁሉ እናት» ተብሎ ይጠራ ነበር። በጊዜው የነበሩትን ልዕለ ኃያላን መንግሥታት ያሳተፈው የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት በሁለት ቡድኖች በተከፋፈሉ አገሮች መካል የተደረገ ሲሆን ራሺያ፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ጣሊያን «ትሪፐል ኢንቴንቴ» ተሰኝተው በአንድ ወገን፣ ራሳቸውን «ሴንትራል ፓወር»[105] በማለት የሚጠሩት ጀርመን፣ አስትሮ ሀንጋሪና ኦቶማን ቱርክ፣ በሌላኛው ወገን ተሳትፈውበታል። በወቅቱ 70 ሚሊዮን ወታደሮች በጦርነቱ ግንባር የተሰለፉ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ 60 ሚሊዮኑ አውሮፓውያን ነበሩ። በጦርነቱ ያለቀው ሕዝብም ከ7 እስከ 15 ሚሊዮን እንደሚሆን ይገመታል።

ጦርነቱ ሲቀሰቀስ እንግሊዝ ወዲያው ከፈረንሳይና ከራሺያ ጋር ስትወግን፣ ኦቶማን ቱርክ በ1914 ማብቂያ ላይ፣ ኢጣሊያ በ1915፣ ሮማኒያ ደግሞ በ1916፣ ወደ ጦርነቱ ተቀላቅለዋል። በወቅቱ ከእንግሊዝ ጋር በነበራት ወዳጅነት ምክንያት በገፍ ትልከው የነበረውን የጦር መሣሪያ ለማገድ ጀርመን በተደጋጋሚ በመርከቦቿ ላይ በወሰደችው ጥቃት የተማረረችው አሜሪካም፣ በ1918 በጀርመን ላይ በይፋ ጦርነት አወጀች። ሆኖም የአሜሪካ ኮንግረስ በፕሬዝዳንት «ውድሮው ዊልሰን» የቀረበለትን በጦርነቱ የመግባት ጥያቄ ተቀብሎ ያጸደቀው፣ ኤፕሪል 16 ቀን 1917 ነበር።[106] በጊዜው ከፍተኛ የጦር ኃይልና የሕዝብ ብዛት የነበራቸው ራሺያና ጀርመን የጦርነቱ ዋነኛ አቀንቃኞች ሆነው መገኘታቸው ለጦርነቱ አድማስ መስፋትና ረጅም ጊዜ መፍጀት የነበረው አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚታይ አልነበረም። ከዚህም በላይ እያንዳንዱ አገር ይከተለው የነበረው «ኢፔሪያላዊ» የተስፋፊነት ፖሊሲ፣ ለጦርነቱ መራዘም ምክንያት በመሆን አገልግሏል። የ1ኛው የዓለም ጦርነት፣ ዓለም አቀፋዊ እንዲሆን ካደረጉት ሌሎች ምክንያቶች አንዱ በፈረንሳይና በእንግሊዝ ቅኝ

[105] Triple Entente – Central Power.
[106] http//en.wikidia.org/wiki/weapons-of-world-war-I

ግዛት ስር በመላው ዓለም የሚገኙ የልዩ ልዩ አገር ሕዝቦች በቀጥታ ያሳተፈ በመሆኑ ነው። በነገራችን ላይ ያን ዓይነት ጦርነት ከዚያ በፊት ሆኖ የማያውቅ ሲሆን፣ ለማንም ግልጥ ሊሆን በሚችል መልኩ፣ ሕዝብ በሕዝብ ላይ፣ መንግሥትም በመንግሥት ላይ የተነሣበት ዘመን እንደነበር ጥርት ብሎ ይታያል።

ከዚህም ሌላ፣ በጦርነቱ አውድማ ከዚያ ዘመን በፊት በጥቅም ላይ ያልዋሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ለመጀመሪያ ጊዜ ታይተዋል። ምንም እንኳ ከዘመናችን የቴክኖሎጂ ዕድገት አንጻር እጅግ ኋላ ቀር ሆነው ቢታዩም፣ በወቅቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋሉት፣ የጦር አውሮፕላኖች ታንኮች፣ መድፎች፣ ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች፣ ሰርጓጅ መርከቦች፣ ልዩ ልዩ ቀላል የነፍስ ወከፍ መሣሪያዎች፣ የመርዝ ጋዝና የመሳሰሉት እንደ ልዩ ትንግርት የታዩበት ዘመን ነበር። ጦርነቱ ፍጹም አውዳሚ የነበረ ከመሆኑም በላይ፣ በመቶዎች ለሚቆጠሩ መንደሮች ሙሉ ለሙሉ መውደም ምክንያት ሆኗል።

በ1917 በራሺያ የ«ጥቅምቱ አብዮት» ፈንድቶ የ«ቮልሼቪክ» ፓርቲ፣ የ«ዛሩ»ን ዘውዳዊ አገዛዝ ገርስሶ ሥልጣን ላይ መውጣቱ፣ ራሺያ በጦርነቱ እንዳትቀጥል ምክንያት ከመሆኑ በላይ፣ ዓለም አዲሱን የኮሚኒስት ርዕይዎት የተዋወቀችበት ዘመን ነበር። ከዚህ በተጨማሪ በጦርነቱ እጅግ ተወጥራ የነበረችው እንግሊዝ በጭንቋ ሰዓት በተለይ በፓለስቲን ምድር የነበሩ አይሁዳውያንን ከጎኗ ለማሰለፍ ስትል በዚያ ዓመት ያወጀችው «የባልፎር መግለጫ» እስራኤል ለምትባለዋ አገር ዳግም እውን መሆን ሁነኛ ሰነድ በማስገኘቱ፣ ያን ዘመን በተለየ አቅጣጫ እንድናየው ያደርገናል። ከእነዚህ ጉልህ ክስተቶች በመነሣት ጦርነቱን፣ ኢየሱስ ለተናገራቸው ትንቢቶች ዋነኛ ምልክት አድርገን ብንቆጥረው አላጋነንም።

በሌላም በኩል ጦርነቱ ለ2ኛው የዓለም ጦርነት መቀስቀስ ምክንያት እንደ ሆነ ይጠቀሳል። ደግሞም ከ1ኛው የዓለም ጦርነት በኋላ እስከ አሁን የተደረጉ ጦርነቶች ምን ያህል ለቁጥር የሚታክቱ እንደሆኑ ስናስተውል፣ መጨረሻው እጅግ እንደቀረበ ይሰማናል። ለዚህም፣ በአውሮፓውያን ቅኝ ግዛት ስር ለዘመናት ሲማቅቁ የነበሩ አገሮች

ነፃነታቸውን ለመጎናጸፍ ያደረጉትን መራራ ትግል እንዲሁም የተመኙትን ነፃነት ካገኙ በኋላ፣ ቅኝ ገዢዎቻቸው ትተውላቸው በሄዱት መርዝ ምክንያት በጎሳ፣ በዘርና በሃይማኖት ተቧድነው አሰልቺ፣ አስከፊና ረጃጅም ጦርነቶች ሲያደርጉ መቆየታቸውን ማየት በቂ ነው። እንደው በአፍሪካ ውስጥ ስለሆነው ብቻ እንኳ ብናወሳ በአንጎላ፣ በሞዛምቢክ፣ በናሚቢያ፣ በኢትዮጵያ፣ በኮንጎ፣ በሩዋንዳ፣ በሶማሊያ፣ በአልጄሪያ፣ በቡሩንዲ፣ በግብጽ፣ በታንዛኒያ፣ በሱዳን፣ በቻድ፣ በሞሮኮ፣ በኡጋንዳ፣ በሊቢያ፣ በናይጄሪያ፣ በኮትዲቯር፣ በደቡብ አፍሪካና በሌሎችም አገሮች የተከሰቱ የእርስ በእርስ ጦርነቶችን መጥቀስ ይቻላል። ከዚህ በተረፈ በተለያየ የዓለም ክፍሎች በተደረጉ የመንግሥት ግልበጣዎች ቁጥራቸው የበዛ ሕዝቦች ደማቸው ደመ ከልብ ሆኖ ቀርቷል።

በተጨማሪ ከ1917 በኋላ የተከሰተውን የኮሚኒስት ሥርዓት ተከትሎ በሆነው የቀዝቃዛው ጦርነት ምክንያት፣ አንዱ የምዕራብ፣ ሌላው የምሥራቅ ደጋፊ ሆኖ ዓለም የታወከችበት ኹነት ጎልቶ የሚጠቀስ ነው። የኮሚኒስቱ ጎራ መሪ የነበረችው ሶቪየት ኅብረት ስትፈራርስ ደግሞ በአውሮፓ፣ በተለይም በቀድሞዋ ዩጎዝላቪያ የተደረጉ ዘግናኝ ጦርነቶች እንደ ሁነኛ ምሳሌ የሚጠቀሱ ናቸው። መቼ ይኼ ብቻ፣ ከነዚያ ዓመታት ወዲህ፣ በአገሮች መኻል፣ በርካታ ታላላቅ ጦርነቶች ተደርገዋል። ከእነዚህም ውስጥ፣ በኢራንና በኢራቅ፣ በእንግሊዝና በአርጀንቲና፣ በህንድና በፓኪስታን፣ በራሺያና በአፍጋኒስታን፣ በአሜሪካና በቬትናም፣ በደቡብ ኮሪያና በሰሜን ኮሪያ፣ በኢራቅና በአሜሪካ፣ በኢትዮጵያና በኤርትራ፣ በኢትዮጵያና በሶማሊያ፣ በኤርትራና በየመን፣ በካሜሮንና በናጄሪያ፣ በአረቦችና በእስራኤል፣ በሰሜን የመንና በደቡብ የመን፣ ወዘተ... የተደረጉት ጦርነቶች ሁሉ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነቶች በኋላ የተደረጉ ናቸው።

ረሀብና
የምድር መናወጥ

በተለያየ ስፍራም ራብና የመሬት መንቀጥቀጥ
ይሆናሉ፤ ይህ ሁሉ ግን የምጡ መጀመሪያ ነው።[107]

እንደ እውነቱ ከሆነ የ1ኛው የዓለም ጦርነት ጦስ በዚህ ብቻ ያበቃ አልነበረም። ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ጦርነቱ ለሁለተኛው የዓለም ጦርነት መቀስቀስ ምክንያት መሆኑ እንዳለ ሆኖ፣ በሁለቱ ጦርነቶች መካል ባሉት ዓመታት፣ ተደጋጋሚ የምድር መናወጥ፣ ረሀብና ቸነፈር፣ አሰቃቂ በሽታና ወረርሺኝ ተከስቷል። ለአብነት ያህል በ1918 እና በ1919፣ በኢንፊሉኢንዛ በሽታ ብቻ፣ ከ20 እስከ 40 ሚሊዮን የተቆጠረ ሕዝብ እንዳለቀ ሲገመት፣ ይኼም በጦርነቱ ከሞተው በብዙ እጥፍ ይሆናል። ከዚህ ሌላ በሁለቱ ጦርነቶች መካል ከ24 በላይ ታላላቅ የረሀብ ጊዜአት በዓለም ዙሪያ ተከስተው፣ የብዙ ሰዎችን ሕይወት ነጥቀዋል። በዚያ ላይ በእነዚሁ ዓመታት በሬክተር ስኬል ሲለኩ፣ መጠናቸው ከ7.0 እስከ 7.9 የሚደርሱና ብዛታቸው ከ239 በላይ የሆኑ ከባድ የምድር መናወጦች የደረሱ ሲሆን፣ ከ8.0 በላይ የሆኑና እጅግ በጣም ከባድ የሚባሉ 50 የምድር መናወጦች በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ድንገት ደርሰው የሚሊዮኖችን ሕይወት እንደ ቀላል ነገር ቀጥፈዋል። ከነዚህ መካል በ1960 በቺሊ የደረሰው መናወጥ እስከ ዛሬ ከደረሱት የመሬት መናወጦች ሁሉ ከፍተኛው ሲሆን፣ በጊዜው በሬክተር ስኬል 9.5 ድረስ ተለክቷል።

ምንም እንኳ የኢየሱስ ትንቢት በእነዚያ ዓመታት በተለየ ሁኔታ ሲፈጸም ቢታይም፣ ከዚያ በፊትም ሆነ በኋላ ምልክቶቹ መታየት እንደቀጠሉ ናቸው። ሌላው ቀርቶ ባለፈው ዓመት ይኼን ርዕሰ ጉዳይ እየጻፍኩ በነበርኩበት ሰሞን ማለትም፣ ከፌብሩዋሪ 27 እስከ ማርች 13፡ 2010 ባሉት አስራ አምስት ቀናት ውስጥ ብቻ ከ300

[107] ማቴ 24:7

በላይ የሚሆኑ የመሬት መናወጦች በዓለም አካባቢ መድረሳቸውን ልዩ ልዩ የዜና አውታሮች ሲዘግቡ ነበር። በዚህ ጊዜ ከደረሱት መናወጦች ውስጥ ከ84 በላይ የሚሆኑት በቺሊ የደረሱ መሆናቸው ደግሞ ለዚያች አገር ሰዎች ምንያህል አስደንጋጭ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል። በእርግጥ አብዛኛዎቹ መናወጦች የደረሱት ሰው ከሚኖርበት በጣም በራቀ ስፍራ ስለሆነና ምንም ጥፋት ስላላደረሱ ያን ያህል ተጋነው አልተወራላቸውም። ነገር ግን በሃይቲ፣ በቺሊና በቱርክ የደረሱት መናወጦች፣ በመቶ ሺዎች የተቆጠረ የሰው ሕይወት በመንጠቃቸው፣ አሰቃቂነታቸው ታላቅ ሆኖ አልፏል። ከዚህ በተጨማሪ በቅርቡ ማለትም 2011 በገባ በ3ኛው ወር በጃፓን ደርሶ፣ በሬክተር ስኬል ከ9.0 በላይ የተለካው መናወጥ ያስከተለው ቀውስ፣ እስከ አሁን ከ20ሺ በላይ ሰዎችን ለሕልፈተ ሕይወት የዳረገ መሆኑ ሲረጋገጥ፣ የወደመው ሀብትና ንብረት በቢሊዮን ዶላር የሚገመት ሆኗል። ከሁሉም ይልቅ አሳሳቢው ነገር ደግሞ በመናወጡ ጊዜ አደጋ ከደረሰባቸው የኑክሊየር ማመንጫዎች ያፈተለከው «ራዲዮ አክቲቭ» በብዙ ሺ ሜትር ርቀት ላይ ለሚገኙ ሰዎች ጭምር አደጋ መፍጠሩ እየተነገረ መሆኑ ነው። በዚህም ምክንያት በአሁኑ ሰዓት ጉዳዩ የጃፓንና የጃፓናውያን ብቻ ሳይሆን፣ የመላው ዓለም እንደ ሆነ እየታየ ነው።

ከዚህ በተለየ ምልክቶቹን እንደ ኢትዮጵያዊ ሆነን ስናያቸው፣ የተለየ ትርጉም የሚሰጡን ይመስለኛል። ለአብነት ያህል ላለፉት ሠላሳና አርባ ዓመታት በዚህች ደኻ አገር ላይ የደረሰው የረሀብ ሰቆቃ፣ ለሁለት መንግሥታት ሥልጣን መልቀቅ ዋነኛ ምክንያት ሆኖ የሚጠቀስ ነው። ያሁኑ ዘመን መሪዎቻችንም ሥልጣን ላይ በወጡበት ዓመት፣ ሕዝባቸውን በቀን ሦስት ጊዜ እንደሚያበሉ ቃል የገቡ ቢሆንም፣ የሥልጣን ዘመናቸው ሃያ ዓመት በደፈነበት በዚህ ጊዜም እንኳ ሚሊዮኖች ገና እየተራቡ መሆናቸውን ለመካድ አልቻሉም። በአንድ ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ይኼንኑ ጉዳይ አስመልክተው «ክርስቲያን ሞኒተር» ከተባለ መጽሔት ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ሲናገሩ «ከአስር ዓመት የሥልጣን ዘመኔ በኋላም ምግብ

መለመኔ ያሳፍረኛል፣ ነገር ግን ሁኔታውን መቀየር እንደሚቻልና እንደሚቀየርም አምናለሁ፣ አለያ ግን እስከ አሁን የሠራሁት ሁሉ ትርጉም አይኖረውም» ብለው እንደነበር ማንበቤን አስታውሳለሁ፣ አቶ መለስ ጨምረው ሲናገሩ ምንም እንኳ ኢትዮጵያ ነፃነቷንና ክብሯን ጠብቃ የኖረች አገር ብትሆንም በአሳፋሪ ልመና ምክንያት ለዓመታት የገነባችው ኩራቷ እንደ ተሸረሸረ አልሸሸጉም። ደግሞም በበረሀ በትግል ላይ በነበሩበት ወቅት ከረሀብ የተነሣ አንዲት ወጣት ከቀናት በፊት የሞተች ላም አጥንት ስትግጥ ማየታቸውንና በወቅቱ ይኼ ነገር በወደፊቷ ኢትዮጵያ እንደማይደገም ለራሳቸው ቃል እንደገቡ አስታውሰው ነበር።

✡ 🕮 ✡

ልጅ ሆኜ በአንድ የስዕል ውድድር ተካፍዬ ማሸነፌን አስታውሳለሁ፤ ትዝ እንደሚለኝ፣ ስዕሉ ከላይ የታንክና የወታደር ምስል ያለው ሆኖ፣ ከታች ደግሞ አንድ ገበሬ፣ በበሬ ሲያርስ የሚታይበት ነው። ሆኖም አሁን ላይ ሆኜ ሳስበው፣ በወቅቱ አሸናፊም ሆነ ተሸላሚ ያደረገኝ ከታች የተጻፈው መፈክር እንጂ፣ የስዕሉ ውበት ወይም ጥራት አይመስለኝም። መፈክሩ እንዲህ ይነበባል *«ረሀብን ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮንም በቁጥጥራችን ስር እናደርጋለን!»*

ይህ ከሆነ ብዙ ዓመት አለፈ፤ እኔም አድጌ ዛሬ ላይ ደረስኩ፤ ያኔ አስብ የነበረውን ደግሜ ለማሰብ ቻልኩ፤ ምንም እንኳ የሳልኩትና ያልኩት «የማይሆን ነገር» ለሽልማት ቢያበቃኝም፣ እውነታው ግን ከዚያ ፈጽሞ የተለየ እንደ ሆነ አሁን አስተዋልኩ። በእርግጥ ማንም ሥጋ ለባሽ ረሀብንም ሆነ ተፈጥሮን በቁጥጥሩ ስር ማድረግ የሚችል የለም። በዚያ ላይ ኢየሱስ በመጨረሻዎቹ ዘመናት በዓለም ዙሪያ ረሀብ እንደሚሆን በመናገሩ፣ የየትኛውም አገር መሪ ሁኔታውን እንዲህ በቀላሉ ሊቀይረው ወይም ከመሆን ሊያቆመው የሚችል አይደለም። በእርግጥ እዚህ ላይ እየተናገርኩ ያለሁት ከሰው አቅም በላይ ስለሚሆነው ትንቢታዊ ረሀብና ችግር እንጂ በስንፍና ምክንያት ስለሚሆነው እንዳልሆነ ሊሰመርበት ይገባል።

የመንግሌል በዓለም ዙሪያ መሰበክ

[108]

ለሕዝብ ሁሉ ምስክር እንዲሆን፣ ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፤ ከዚያም መጨረሻው ይመጣል።

ለአንድ አፍታ አካባቢያችንን በአንክሮ ብናስተውል፣ አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ በየቀኑ በአምላክ ስም አዳዲስ ሃይማኖቶች እየተፈጠሩ እንደሆነ እናያለን። አብዛኛዎቹም ሃይማኖቶች የራሳቸውን እምነት ትክክለኛነት በማስተማር አቋማቸውን ከማስረዳት ይልቅ፣ ሰርክ ስለ ሌላው ሃይማኖት ስህተት እየተናገሩ ሲያጥላሉ ነው የሚታወቁት። አንዳንዶቹም በተከታዮቻቸው ውስጥ መራር ጥላቻ ሲዘሩ ይቆዩና አጋጣሚ ወይም ምቹ ጊዜ ሲያገኙ ለጥፋት ይነሣሉ። ከዚህ አንጻር የክርስትናን መሠረታዊ ትምህርት ለማፋለስ ሲሉ ብቻ የራሳቸውን መጽሐፍ ወዲያ ትተው፣ መጽሐፍ ቅዱስን አጣመው የሚሰብኩ ሃይማኖቶች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከተ መጥቷል። በዚህ በኩል በአገራችንም ሆነ በመላው ዓለም ያለው የእስልምና አክራሪነት እንቅስቃሴን እንደ አንድ አብነታዊ ማስረጃ አድርገን መጥቀስ ብንችልም፣ በክርስትና ስም የሚንቀሳቀሱ ዳሩ ግን የክርስቶስ ኢየሱስ ተቃዋሚ የሆኑ በርካታ የሃይማኖት ተቋማትን ሳይጠቅሱ ማለፍ አግባብ አይሆንም። ይሁን እንጂ ከዚህ ተግባር ፈጻሚዎች መኻል አንዳቸውም፣ የየዕለቱ ሥራቸው ለትንቢቱ መፈጸም የሚያደርገውን አስተዋጽኦ የተረዱ አይመስሉም። አስደሳቹና አስደናቂው ነገር፣ በመጨረሻው ዘመን ለሕዝብ ሁሉ ምስክር እንዲሆን የክርስቶስ የወንጌል ቃል በዓለም ሁሉ እየተሰበከ መሆኑ ነው። ጳውሎስ በአንድ ወቅት አጋጥሞት ስለነበረው ነገር ለፊሊጵስዮስ ሰዎች ባወጋ ጊዜ «አንዳንዶች ከቅናትና ከፉክክር የተነሣ፣ ሰሎች ግን ከበጎ ፈቃድ የተነሣ ክርስቶስን ይሰብካሉ። ታዲያ ችግሩ ከምኑ ላይ ነው? ቁም ነገሩ በቅናትም ይሁን በማስመሰል

[108] ማቴ 24:9-14።

በማንኛውም መንገድ ክርስቶስ መሰበኩ ነው። በዚህም እጅግ ደስ ይሰኛል።»[109] ብሎ ነበር። በእርግጥም በተለየ ዓይን ካየነው ወንጌል በዚህ መልክ መሰበኩ «እጅግ ደስ የሚያሰኝ» ባይሆን እንኳ ያን ያህል የሚያስከፋ ጉዳይ ግን አይደለም።

በሌላም በኩል፣ ምንም እንኳ ለሰይጣናዊውና ምግባረ ብልሹ ለሆነው ዓለም ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ቢሆንም፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂው አሁን የደረሰበት ደረጃ፣ ለወንጌል አገልግሎት እያበረከተ ያለው ተግባር በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ለአብነት ያህል አስቀድሞ በጽሑፍ ብቻ ተገድቦ የኖረው ወንጌል፣ ዛሬ ከአዲዮ ቪዥዋል ቴክኖሎጂ መፈጠር ጋር አብሮ እያደገና እየተስፋፋ ይገኛል። ከዚህ ባለፈ የዲጂታል ሳተላይትና የኢንተርኔት ቴክኖሎጂ መፈጠርን ተከትሎ «ወንጌል በየትኛውም የዓለማችን ክፍል ሁሉ ተሰብኳል» ለማለት የሚያስችል ደረጃ ላይ እየተደረሰ ነው። ለምሳሌ በቅርብ ቀን አንድ «የታላቁ ተልዕኮ አገልግሎት በኢትዮጵያ» አገልጋይ የሆነ ሰው እንደ ነገረኝ ከሆነ፣ አገልግሎታቸው በቅርብ ዓመታት የከፈተውን ድረ ገጽ፣ በየቀኑ በመቶ ሺ የሚቆጠሩ በዓለም ዙሪያ ያሉ የተለያየ እምነት ተከታዮች እንደሚጎበኙት ተረድቻለሁ። ታዲያ ይኼ አስደናቂ ነገር አይደለምን? የጌታ ትንቢት እየተፈጸመና መምጫው እየቀረበ ስለመሆኑ ከዚህ የተሻለ ምን ማስረጃ መጥቀስ ይቻላል?

የአዲዮ ቪዥዋል አገልግሎቶችንም በተመለከተ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን፣ በተለይም የኢየሱስን ሕይወት በሚተርኩ ወንጌላት ላይ ተመሥርተው እየተሠሩ ያሉ ፊልሞች አስተዋጽዖ በጣም የሚገርም ነው። ምንም እንኳ በፊልሞቹ ላይ የኢየሱስንና የተከታዮቹን ገጸ ባሕርይ ወክለው ከሚጫወቱ ተዋናዮች አብዛኛዎቹ ጌታ ኢየሱስን ያላወቁና በእርሱም የማያምኑ መሆናቸው ቢታወቅም፣ እግዚአብሔር ግን ቴክኖሎጂውን ለበጎ ሥራውና ለትንቢቱ ፍጻሜ እንዴት እየተጠ ቀመበት እንደሆነ በግልጥ ይታያል። ለዚህም ማስረጃ ካስፈለገ በየቀኑ እነዚህን የሆሊውድ ፊልሞች በማየት ብቻ ጌታ ኢየሱስን

[109] ፊል1:12-18።

የሕይወታቸው ጌታና አዳኝ አድርገው የተቀበሉ በርካታ ሰዎችን ለአብነት መጥቀስ ይበቃል። ለምሳሌ በቅርብ ዓመታት ውስጥ «ሚል ጊብሰን» በተባለ ታዋቂ የሲኒማ ባለሞያ ተዘጋጅቶ የቀረበውና እጅግ ተደናቂነትን ያተረፈው «ዘ ፓሽን ኦፍ ዘ ክራይስት» የተሰኘው ፊልም በብዙ የዓለም ክፍሎች መታየቱ፣ ለዚህ እንደ አንድ ማስረጃ የሚጠቀስ ነው። በእርግጥ አንዳንዶቹ ፊልሙ እንዲታይ የፈቀዱት የክርስቶስ ፍቅር ግድ ብሎአቸው ሳይሆን፣ የአይሁዳውያኑን ጭካኔ ለማሳየት ወደው እንደነበር ግልጥ ነው። ሆኖም ይኼም ነገር እንኳ ፊልሙ በዓለም ዙሪያ እንዲታይ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ እንደነበረው በጓሳ ላይ ታይቷል። ሌላው ቀርቶ አክራሪ በሆኑ የሙስሊም አገራት ውስጥ ሳይቀር የመታየት ዕድል ያገኘው፣ አገራቱ ለአይሁዳውያኑ ትንሽ አገር ካላቸው ጥላቻና «ሁሌም እንዲሁ ጨካኝ ናቸው» ለሚል መሰሪ ፕሮፓጋንዳ ፊልገውት ነው። ይሁን እንጂ እየሆነ ያለው ነገር ሁሉ ክትንቢት አንጻር ሲመረመር፣ በአጋጣሚ የሆነ ሳይሆን፣ አስቀድሞ በጌታ ኢየሱስ በተነገረው መሠረት የተፈጸመ ነው።

ይህ ብቻ ሳይሆን በዚህ የዘመን መጨረሻ የክርስቶስን ወንጌል እንዲያጣምሙ ሰይጣን የላካቸው አንዳንድ ሰዎች የቅዱሱን መጽሐፍ ቃል በራሳቸው መንገድ እያቀረቡ ብዙዎችን ወደ ጥፋት እየነዷቸው እንደ ሆነ ይታያል። ከእነዚህም የጥፋት መልዕክቶች መካል በተለይ ባለፉት ዓመታት ከፍተኛ «አድናቆትን» አትርፎ በየሲኒማ ቤቶቹ ሲታይ የነበረውና በአጸያፊ መልዕክቶች የተሞላውን የዳን ብራውኑን «ዘ ዳቬንቺ ኮድ» የተሰኘውን ፊልም በዋቢነት መጥቀስ ይቻላል። ሆኖም በእነዚህ ክፉ የሰይጣን ሥራዎች ውስጥ እንኳ ወንጌል በዓለም ዙሪያ እየተሰበከ መሆኑ አስደናቂ ነው። በእርግጥ በዚህ መጨረሻው ዘመን ማንም ሰው አልሰማሁም እስከማይል ድረስ በተለያየ መንገድ ወንጌል ወደ ሰው ልጆች እየደረሰ ነው። ይህ ደግሞ የጌታ ኢየሱስ ዳግመኛ መምጣት እጅግ እንደተቃረበ የሚያመለክት ነው።

በተጨማሪም ከየትኛውም ጊዜ ይልቅ፣ በዚህ ዘመን መጽሐፍ ቅዱስ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች ተተርጉሞ በዓለም ዙሪያ ለሚገኙ ሕዝቦች ተሰራጭቷል። እግዚአብሔርም ለዚሁ ተግባር ባሰነሣቸው ባሪያዎቹ

በኩል ሌላውቀርቶ ጥብቅ ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ተጽእኖ ባለባቸው አገሮች ሳይቀር እየተሰራጨ ይገኛል። ከዚህም በላይ መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ በጣም ቀላል በሆነ መንገድ በድምፅና በጽሑፍ በእያንዳንዱ ሰው እጅ እንዲደርስ ሆኖ ተዘጋጅቷል። በመሆኑም በዛሬው ጊዜ ሰዎች በኮምፒውተራቸውና በሞባይል ስልካቸው ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲኖራቸው ከፈለጉ ሁሉም ነገር ተሰናድቶ ይጠብቃቸዋል። ይኼም ለመጨረሻው ዘመን ታላቅ ምልክት ነው።

በእርግጥ ያለንበት ዘመን በክርስትና ስም የሚጠሩ፣ ዳሩ ግን ከስሙ በቀር ለዛውም ሆነ ቃናው የሌለባቸው በሺ የሚቆጠሩ «ሃይማኖቶች» ሚሊዮኖችን ተከታይ ማድረጋቸውን ለታዘበ ሁኔታው እጅግ ተስፋ የሚያስቆርጥና አስደንጋጭ መስሎ ሊታየው ይችላል። ይሁን እንጂ በእነዚያ ስፍራዎች እንኳ የእውነትን ቃል የተረዱ የክርስቶስ ትሩፋን መገኘታቸውን ላስተዋለ ግን፣ የትንቢቱ ቃል ወደፍጻሜው እንዴት እየተጓዘ እንደሆነ እያየ መገረሙ አይቀርም።

ልብ በሉ፣ ክርስቶስ የወንጌሉ ቃል በዓለም ሁሉ እንደሚሰበክ የተናገረው የዛሬ ሁለት ሺ ዓመት፣ በኢየሩሳሌም ከተማ ነበር። ትንቢቱን በዚያ ዘመን የሰማ ማንም ሰው ደግሞ፣ ዛሬ እየተፈጸመ ባለበት መንገድ ይፈጸማል ብሎ እንደማይገምት የታወቀ ነው። እኛ ግን አስቀድሞ ጌታ እንደተናገረው ሁሉም ነገር እየተፈጸመ መሆኑን እያየንና እየሰማን ነው።

መጻኖችሁ ወደ እናንተ እጅግ ቀርቧል[110]

ጌታ ኢየሱስ «አነዚህ ነገሮች መሆን ሲጀምሩ መዳናችሁ ወደ አናንተ አጅግ ቀርቧልና ቀጥ ብሳችሁ ቀሙ፤ ራሳችሁንም ወደ ላይ ቀና አድርጉ» ብሎ መክሯል። ይህም ከመምጣቱ አስቀድሞ ስለሚፈጸሙ ነገሮች እንደ ሆነ ግልጥ ነው፤ በእርግጥ በዛሬው ጊዜ፣ ከመምጣቱ አስቀድሞ እንደ ሚሆኑ ከተናገራቸው ትንቢቶች አብዛኛዎቹ ተፈጽመዋል። የቀሩት ጥቂት ነገሮችም፣ ድንገት እንደሚሆኑ የሚጠበቁ ከመሆናቸውም ሌላ ጌታ በሚመጣበት ጊዜ የሚፈጸሙ በመሆናቸው፣ ያለነው በዘመን አላቂ ወይም እንጥፍጣፊ ላይ መስሎ ይታያል። ምንም እንኳ የመሲሁ ዳግም የመምጫ ቀንና ሰዓት አስልቶ በዚህ ጊዜ ነው ማለት ፈጽሞ ባይቻልም ከተሰጡት ምልክቶች አንጻር ጊዜው እጅግ እንዳለቀና እንደተፈጸመ ተረድቶ መናገር ግን ይቻላል። በእርግጥ የሰው ሁሉ መዳን ፍጹምና ሙሉ የሚሆነው፣ ጌታ በክብር ሲመጣና ቤዛነቱን ከእርሱ ሲቀበል ነው። በአሁኑ ጊዜ የዳነ ሰው፣ በተስፋ ድኗል እንጂ፣ ፍጹም የሆነው ደኅንነቱ ገና ወደፊት የሚፈጸም ነው። ማንም ሰው በምድር የለበሰው ሥጋ በሚመጣው ዓለም አይለብስም፤ ይህ የሚፈርሰው በማይፈርሰው፣ የተዋረደውም በከበረው ሊተካ ግድ ነው። በጊዜው አዲስ ሥርዓት የሚሆንባት ሰማይና ምድር ከላይ ከሰማይ ትወርዳለች። በዚያም ሐዘን፣ ለቅሶ፣ መርገም ... ለዘላለም የለም። አማኝ ሰው እስከ መጨረሻው መጽናት የሚገባው በእምነት ያገኘውን መዳን፣ ክርስቶስ ሲመጣ ፍጹም ሆኖ እንዲያገኘው ነው።[111]

ደግሞም ቀጥ ብሎ ቆሞ ወደ ላይ መመልከት ያስፈለገው፣ እስከ ጌታ መምጣት ቀን ድረስ በምድር የሚሆኑ ምልክቶች፣ የሰውን ሁሉ እምነት የሚፈትኑና የሚያናውጡ ስለሆኑ ነው። ይልቁኑም ይህቺ ምድር መፍረስ ስትጀምር፣ ለዘላለም የምትኖር መስላ ለመታየት

[110] ሉቃ21:28።
[111] ሮሚ8:24።1ኛቆሮ15:35-49። ራእ21:1-4።

የተጻያዩ ማታለያዎችን ይዛ የምትገለጥ በመሆኑ የማንንም ልብ ለመፈታተን መሞከሯ አይቀርም። ኢየሱስም «ራሳችሁን ወደ ሳይ ቀና አድርጉ» ማለቱ፣ አማኙ በዚህ ምድር የሚሆነው ማናቸውም ነገር እንዳይዘው የሚያስጠነቅቅ ብቻ ሳይሆን፣ ምን ማድረግ እንዳለበት እንዲያውቅና በጸሎት ተግቶ እንዲጠባበቅ የሚያሳስብ ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር መንግሥት ጉዳይ የአማኝ ሁሉ ዋና የጸሎት አጀንዳና ማዕከል መሆን እንደሚገባው የሚያስገነዝብ ነው።

በመሠረቱ ኢየሱስ ይህቺ ዓለም ወደፊት ምን እንደምትመስል በግልጥ ነግሮናል። ስለዚህ እኛ ባለንበት አካባቢ ሁኔታዎች ሰላም ቢመስሉን እንኳ፣ ለጥቂት ጊዜ እንጂ ለዘለቄታው የሚቀጥል እንዳልሆነ ማወቅ አለብን። ደግሞም አማኞች በዚህ ምድር ሲኖሩ እንደ እንግዳና መጻተኛ እንጂ፣ የምር የሚኖሩ መሆን የለባቸውም። መቼም ጊዜ ቢሆን ይኼ ዓለም አላፊና ጠፊ መሆኑን አትዘንጉ። ማንም ሰው ከሚጠፋው ዓለም ጋር አብሮ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር ለተሻለ ክብር በልጁ እንደዋጀውም አትርሱ።

ባለንበት ዘመን ጌታ፣ በመጨረሻው ወቅት እንደሚሆኑ ከተናገራቸው ምልክቶች አብዛኛዎቹ፣ ተፈጽመዋል ወይም እየተፈጸሙ ነው። የምልክቶቹን ምንነት ተረድተው፣ የትንቢቱን ቃል ፍጻሜ የሚጠባበቁ ሰዎች ቁጥር፣ በጣም ጥቂት መሆን ግን እጅግ ያስገርማል። ለነገሩ ጌታ «የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር ላይ አምነት ያገኛ ይሆን?» ያለው፣ ቀድሞውኑ ይኼን ስለሚያውቅ አይደለምን? በዛሬው ዘመን ላይ ሆነን የቀረችንን «ጥቂት ነገ» ስንመለከታት የከፋ እንጂ፣ የተሻለ ነገር ለማየት አልቻልንም። ይኼም የ«ምጡ ጣር» መጀመሪያ የተባለው ዘመን በየዕለቱ ምን ያህል አስከፊ እየሆነ እንደሄደና ወደ ዋናው ምጥ መጣደፉን የሚያመለክት ነው። ለአብነት ያህል በዚህ ዘመን እየሆኑ ያሉ አንዳንድ ነገሮችን ስንመለከት ወደማይቀረው ዘመን እየተጣደፍን እንደሆነ ያሳዩናል።

በዓለም ውስጥ በየዕለቱ የሚደረጉ የመንግሥት ግልበጣ፣ ጅምላ ጭፍጨፋና የእርስ በእርስ ጦርነት፣ ለጥቂት ቀናት ብቻ የዜና ማሰራጫዎች ርዕሰ ወሬ ከመሆናቸው በቀር ወዲያው መረሳታቸው

ይደንቃል። አንዱ ሕዝብ በሌላኛው ሕዝብ ላይ ተነሥቶ አሰቃቂ ጥፋትና እልቂት እንዲያደርግ የሚያስችለውን ድንገተኛ አቅም ማን እንደሚፈጥርለት ወይም እንደሚያድለው የሚያውቅ የለም። በዚያ ላይ በአንድ ጊዜ ፍንዳታ ሚሊዮኖችን ሊያጠፉ የሚችሉ ጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎችን በቀላሉ ከቦታ ወደ ቦታ ለማዘዋወር መቻሉ ሳያንስ፣ እነዚህ የጦር መሣሪያዎች፣ ኃላፊነት በማይሰማቸውና ለሰው ልጅ ቅንጣት ታክል ክብርና ርህራሔ በሌላቸው የምድር ገዢዎች እጅ መገኘታቸው አሳሳቢ ነው። ከዚህ ውጪ መደበኛ በሚባሉት የጦር መሣሪያዎች በሚደረጉ ጦርነቶች እንኳ የሚያልፈው የሰው ሕይወት ቁጥር ቀላል የሚባል አይደለም።

በሌላ በኩል ወደ አየር በሚለቀቁ በካይ ጋዞች ምክንያት ምድራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ፣ ለኑሮ የማትመች አስቸጋሪ ስፍራ እየሆነች ነው። በተለይም ከፋብሪካዎች፣ ከተሽከርካሪዎችና ከልዩ ልዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች የሚወጣው «ካርበን» በከባቢ አየር ውስጥ ያለውን የኦዞንን መጠን ስላሳሳው፣ ፀሐይ ያለከልካይ ወደ ምድር የምትደርስበትን ሁኔታ አስከትሏል። ሁኔታው የዓለማችንን የሙቀት መጠን እጅግ ከፍ በማድረጉ፣ በየቀኑ መጠኑ ቀላል የማይባል የበረዶ ግግር እንዲቀልጥ እያደረገ ነው። በዚህ ምክንያት የአየር መዛባት እየተከሰተ፣ በልዩ ልዩ ቦታ የጎርፍና የማዕበል አደጋ እያደረሰ ነው። በአንጻሩ ከፀሐዩ ግለት የተነሣ ከወንዞችና ከሐይቆች የሚተነው ውኃ ከወትሮው ይልቅ እጅግ ብዙ ሆኗል፤ ይኼ ደግሞ በቀድሞ ዘመን የውኃ መገኛና ስፍራ የነበሩ ወንዞች፣ ኩሬዎችና ሐይቆች እንዲደርቁ መንስኤ እየሆነ ነው።

የምድርና የሕዝቦችዋ ስቃይ ግን በዚህ የሚያበቃ አይደለም። በየዕለቱ አዳዲስ የተፈጥሮ አደጋዎች በተለያዩ የምድራችን ክፍሎች ሲደርሱ እንሰማለን። በአየር ንብረት መዛባት፣ በብዙ ቦታዎች ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ ባለመዝነቡና በበረሀ መስፋፋት የተነሣ በየቀኑ አዳዲስ ረሀብተኞች እንደ አሸን እየፈሉ ነው። ምንም እንኳ የዓለም ሳይንሲስቶችና የአካባቢ ጥበቃ ተከራካሪዎች፣ የጉዳዩን አሳሳቢነት ተረድተው ለመንግሥታት መሪዎች ደጋግመው ቢያስታውቁም፣

የመወሰን አቅሙን በእጃቸው የያዙት ፖለቲከኞች ግን ከገቡበት የእኔ እበልጥ፣ እኔ እበልጥ ፉክክር እንዲሁም አማራጭና ዋስትና ከማጣት የተነሣ፣ እስከ አሁን መፍትሄ ሊሆን የሚችል ተግባራዊ እርምጃ ለመውሰድ ወደ ውሳኔ መድረስ የቻሉ አይመስሉም። እንዲያውም ጉዳዩን አስመልክቶ በተለያዩ ጊዜአት የተደረጉ ስምምነቶች የታሰበው ያህል ውጤት እንዳላስገኙ ነው የሚነገረው። ከእነዚህም «ብዙም አልተሳኩም» ከሚባሉት ስብሰባዎች በተለይ በጃፓን ኪዮቶ፣ በዴንማርክ ኮፐን ሐገን፣ በሜክሲኮ ካንኩን፣ የተደረጉትን ለአብነት ያህል መጥቀስ ይበቃል። ዓለም ግን አሁንም ተስፋ ስላልቆረጠች፣ ደግሞ ለሚቀጥለው ዓመት በጉዳዩ ላይ ለመነጋገር በደቡብ አፍሪካ ደርባን ጽኑ ቀጠሮ ይዛለች። ነገር ግን ወደ አየር ከሚለቀቀው በካይ ጋዝ 41.7 በመቶ የሚሆነውን ድርሻ የሚወስዱት፣ አሜሪካና ቻይና እስከአሁን ወደ ስምምነቱ ለመቅረብ ያሳዩት ተነሳሽነት ብዙም ተስፋ የሚሰጥ አይደለም ይባላል።

በደኻውና በሀብታሙ መኻል ያለው የኑሮ ደረጃ እጅግ መለያየትም ሌላው አሳሳቢ ነገር ነው። የዚህ ዓለም ሀብት በአብዛኛው በጥቂት ባለጠጎች ቁጥጥር ስር ያለ ሲሆን፣ ዛሬም ድረስ ቢሊዮኖች ከድህነት ወለል በታች እየዋኙ ነው። ከዚህ አንጻር በዚህ ዓለም የኑሮ ሥርዓት መቼም ቢሆን ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል የሚኖር አይመስልም። የጌታ ኢየሱስ የትንቢት ቃል ግን ወደ ፍጻሜው እየቸኮለ ነው።

ከዚያ በኋላ መጨረሻው ይመጣል።[112]

ወሬው ሁሉ የሚያስፈራ፣ የሚሆነው በምድር ዙሪያ
እየከፋ ሲሄድ ጊዜው መሸሸጊያ ኢየሱስ ነው
ለእኛ ግን መሸሸጊያችን፣ እግዚአብሔር ነው
/ዘማሪ፣ ደረጀ ከበደ/

[112] ማቴ24:14።

የታላቁ መከራ ወበይት ምልክቶች

113

አባቡም ሴቲቱ በወንዝ አንድትወሰድ ሲያደርግ ወንዝ የሚያህልን ውኃ ከአፋ በስተኋላዋ አፈሰሰ። ምድሪቱም ሴቲቱን ረዳቻት፣ ምድሪቷም አፏን ከፍታ ዘንዶው ያፈሰሰውን ወንዝ ዋጠችው። ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቆጥቶ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት የሚጠብቁትን ከዘርዋ የቀሩትን ሲዋጋ ሄደ በባሕርም አሸዋ ላይ ቆመ።

እንደ ዳንኤል ትንቢት ከሆነ ታላቁ መከራ የሚጀመረው የሚመጣው አለቃ ከእስራኤልና ከቀረው ዓለም ጋር ያደረገውን ጽኑ ቃል ኪዳን በሚያፈርስበት አጋጣሚ ነው። ኢየሱስም በዳንኤል የተጻፈውን ጠቅሶ በዚያን ጊዜ አንባቢው ያስተውል ዘንድ አሳስቧል። ከዚህ አንጻር የጥፋት እርኩሰት በቤተ መቅደሱ ውስጥ የሚቆምበትና በእስራኤል እንዲሁም በሚመጣው የዓለም መሪ መኻል የሚደረገው ስምምነት የሚፈርስበት አንድ የጊዜ ሰሌዳ የሚከተል መሆኑን እንረዳለን።

በዚያ ዘመን ዘንዶው /ሰይጣን/ ሴቲቱን /እስራኤልን/ ለማጥፋት የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም። በወቅቱ ሴቲቱ በጎርፍ እንድትወሰድ ወንዝ የሚያህል ውኃ፣ ከአፉ ተፍቶ ከበስተኋላዋ እንደሚያፈስ ተጠቅሷል። ምናልባትም ይኼ እንደ ታላቅ ወንዝ የተጠቀሰው ውኃ፣ ከአያሌ አገሮች የተውጣጣ ቁጥሩ ብዙ የሆነ ሠራዊት ሊሆን ይችላል ተብሎ ይታሰባል። እኔም ብሆን እንዲሁ የሚሆን ይመስለኛል። ምድሪቱም ሴቲቱን ትረዳታለች፣ አፍዋን በመክፈት ዘንዶው ከአፉ ተፍቶ ያፈሰሰውን ውኃ ትውጠዋለች። በእርግጥ ትርኢቱ ምን እንደ ሆነ ደፍሮ ለመናገር አስቸጋሪ ቢሆንም፣ እግዚአብሔር፣ እስራኤልን ታምራዊ በሆነ መንገድ እንደሚታደጋት ግን ግልጥ ነው።

ከዚያ በኋላ ዘንዶው በሴቲቱ ላይ ተቆጥቶ ከዘርዋ ተርፈው የቀሩትን ሊዋጋ ይሄዳል። እነርሱም በአስቸጋሪ ጊዜአት እንኳ የእግዚአብሔርን

[113] ሪእ13:15-18። ማቴ24:15።

ትዕዛዝ የጠበቁና ስለኢየሱስ በታማኝነት የሚመሰክሩ ሰዎች ናቸው። ምናልባትም ከእነዚህ ሰዎች አንዳንዶቹ በየስፍራው ተበትነው ያሉ አይሁዳውያን ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ በታላቁ መከራ ወቅት የጌታ ኢየሱስን አዳኝነት አምነው የሚቀበሉ ወይም ሳይነጠቁ ቀርተው፣ የሆነውን ሁሉ ካዩ በኋላ በንሰሃ ወደ ጌታ የተመለሱ ሊሆኑ ይችላሉ።

በሌላም በኩል ዮሐንስ ራእይውን በተመለከተበት ሰባተኛ ምዕራፍ ላይ ማንም ሊቆጥራቸው የማይችል እጅግ ብዙ ሰዎችን የተመለከተ ሲሆን፣ እነርሱም ከነገድ፣ ከወገንና ከቋንቋ ሁሉ የተውጣጡ ሆነው፣ ነጭ ልብስ የለበሱ፣ የዘንባባ ዝንጣፊ በእጃቸው የያዙና በዙፋኑ ፊት ቆመው በታላቅ ድምፅ እየጮኹ በጉን የሚያወድሱ ነበሩ። ታዲያ ከሽማግሌዎቹ አንዱ ወደ ዮሐንስ መለስ ብሎ «እነዚህ ነጭ ልብስ የለበሱ እነማን ናቸው? ከወዴትስ መጡ?» ብሎ ሲጠይቀው፣ ዮሐንስ ማንነታቸውን ፈጽሞ እንደማያውቅ ግራ በተጋባ ስሜት ተናግሯል። ቀጥሎም ከሽማግሌዎቹ አንዱ፣ ሰዎቹ ታላቁን መከራ አልፈው የመጡ እንደ ሆኑ ለዮሐንስ አስረድቶታል። ከዚህ አንጻር በታላቁ መከራ ውስጥ የሚያልፉ ሰዎች፣ በዘር አይሁዳዊ ባይሆኑም እንኳ፣ ከሴቲቱ ዘር የሚቆጠሩ መስለው ይታያሉ።

ሆኖም በብዙ የነገረ መለኮት ተማሪዎች ዘንድ፣ ይኼ የታላቁ መከራ ዘመን ከመግባቱ አስቀድሞ ቢያንስ ሁለት ቅድመ ሁኔታዎች የግድ መሟላት አለባቸው ተብሎ ይታመናል። አንደኛው ቅድመ ሁኔታ፣ እስራኤል እንደ አገር ተመሥርታ፣ ኢየሩሳሌምን በቁጥጥርዋ ስር ማድረጓ፣ እንዲሁም ቤተ መቅደሱን ለመሥራት የሚያስችል ሁኔታ ላይ መገኘቷ ሲሆን፣ ሁለተኛው ቅድመ ሁኔታ ደግሞ፣ ሮም ሁነኛ ሚና የምትጫወትበትና አስር አገሮችን በአባልነት የሚያጠቃልል ጎብረት ተፈጥሮ፣ መንግሥታቱ አንድ መሪ የሾሙ እንደሆነ ነው። ከነዚህ ምልክቶች የተነሣ፣ ይኼ ያለንበት ዘመን ሁሉ ነገር ተጠናቆ የመጨረሻውን ፊሽካ መነፋት የሚጠባበቅ መስሎ የሚታይ ሆኖአል።

> በዚያን ጊዜ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ አስከዛሬ ድረስ ያልሆነ፣ ወደፊትም የማይሆን ታላቅ መከራ ይሆናል። እነዚያ ቀናት ባያጥሩ ኖሮ በምድር ላይ አንድም ሰው በሕይወት አይገኝም ነበር

በቅርቡ ከአንድ ወዳጄ ጋር ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች አንስተን ስንነጋገር *«ታላቁ መከራማ አሁን ገብቶ ያለም እንዴ? ከዚህ የበለጠ መከራ ምን ሊመጣ ይችላል?»* በማለት አሳቡን ገለጠ። እርግጥ ነው፣ እስከ ዛሬ በዓለም የደረሰው መከራ ከበቂ በላይ ሆኖ ሳለ፣ ስለ ሌላ አሰቃቂ የመከራ ዘመን ማውራት ደስ ላያሰኝ ይችላል። ደግሞም ወደፊት ስለሚሆኑ ታላቅ የመከራ ጊዜአት ስናወራ እነዚያን ያለአንዳች በደል በናዚ ጀርመን የተገደሉ ከስድስት ሚሊዮን በላይ አይሁዳውያንን ረስተን አይደለም። ከዚህም በላይ በተለያዩ ጊዜአት በዓለማችን የደረሱ አስከፊ ጦርነት፣ ረሀብ፣ የመሬት መንቀጥቀጥና በሽታ ያለቀውን ሕዝብ አልዘነጋንም። ያስ ወዳጄ፣ እስከ አሁን በምድር ከደረሰው መከራ ሌላ፣ የታላቅ የመከራ ዘመን እንደሚመጣ ሲሰማ ባይዋጥለት ምን ይደንቃል? ኢየሱስ ግን ስለታላቁ መከራ ሲያስረዳ፣ ከዚያ በፊት ሆኖ እንደማያውቅና ከዚያም በኋላ ጨርሶ እንደማይሆን መናገሩ የመከራውን አሰቃቂነት ከወዲሁ እንገነዘባለን። እንዲያውም *«ቀናቱ ስለተመረጡት ሰዎች ሲባል ባያጥሩ ኖሮ ሥጋ የለበሰ ሰው በምድር አይገኝም ነበር»* ነው ያለው።

ጌታ ኢየሱስም ሆነ ነብያቱ፣ በታላቁ መከራ ስለሚሆኑ ነገሮች ለማስረዳት የተጠቀሙባቸው ቃላት፣ የወቅቱን መከራ ከባድነት የሚያሳዩ ብቻ ሳይሆኑ ትዕይንቶቹን በሰው ቋንቋ ለመግለጥ ምን ያህል አስቸጋሪ መሆናቸውን የሚያሳዩ ናቸው። ለምሳሌ ኢየሱስ የተናገረውን ወንጌላዊው ማቴዎስ ሲጽፈው «ከዚያች ወራትም መከራ በኋላ

[114] ማቴ 24:21፣ 29።

ወዲያው ፀሐይ ይጨልማል፤ ጨረቃም ብርሃኗን አትሰጥም፤ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፤ የሰማይ ኃይላት ይናወጣሉ» ነበር ያለው:: ለመሆኑ ይኼ ኹነት፣ ምን እንደሚመስል ከቶ በምን ቋንቋ ቢነገር ይገባን ይሆን?

ደግሞስ፣ በየአብያተ ክርስቲያናቱ መድረክ በአብዛኛው ስለ«ድል» እና ስለ«ብልጥግና» ብቻ ተጋኖ በሚወራበት በዚህ «ደግ» ዘመን ከፈታችን ስላሉ ከባድ የመከራ ጊዜአት እየተናገሩ አሜንታን መጠበቅ ከየዋህነት በላይ ሳይሆን ይቀራል? ዮሐንስ ግን ከምዕራፍ 4 እስከ ምዕራፍ 19 ድረስ የሚናገረው ስለእነዚያ አሰቃቂ የመከራ ዓመታት ብቻ ነው:: በተለይም ከሱባኤው አጋማሽ ጀምሮ እንደ ሚሆን የሚጠበቀው ዘመን በራእይው ሁነኛ ስፍራ ያገኘ ነው:: በዚሁ መሠረት በራዕይው አራተኛ ምዕራፍ፣ የመጀመሪያ ቁጥር «ና ወደዚህ ውጣ! ወደ ፊት የሚሆኑትን ነገሮች አሳይሃለሁ» ተባለ፤ ወዲያው በዙሪያው ካሉ ፍጡራን ለእግዚአብሔር የሚቀርብለትን አምልኮና ውዳሴ ሲመለከት ሳለ፣ በመጽሐፉ አምስተኛ ምዕራፍ መግቢያ፣ በዙፋኑ ከተቀመጠው እጅ ላይ ያለ፣ በውስጥና በውጭ የተጻፈበትና በሰባት ማኅተም የታሸገ መጽሐፍ፣ እንዲሁም «ማኅተሞችን መፍታትና መጽሐፉን መክፈት የተገባው ማን ነው?» ብሎ፣ አንድ ብርቱ መልአክ በታላቅ ድምፅ ሲናገር እንዳየ ይገልጣል:: ዳሩ ግን በሰማይም ሆነ በምድር መጽሐፉን የሚከፍትና ውስጡን የሚመለከት ስላልተገኘ፣ ዮሐንስ እጅግ ምርር ብሎ አለቀሰ:: በዚያን ጊዜ ከሽማግሌዎች አንዱ «አታልቅስ፤ ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ፣ የዳዊት ስር ድል ነሥቷልና፤ እርሱ መጽሐፉንና ሰባቱን ማኅተሞች መክፈት ይችላል» በማለት እንዳጽናናው ይናገራል::

ዮሐንስ ከዚህ በኋላ ባለው የራእይው ስድስተኛ ምዕራፍ፣ በጉ ሰባቱን ማኅተሞች በየተራ መፍታት እንደ ጀመረ ተመልክቷል:: በዚሁ መሠረት የመጀመሪያዎቹን አራቱ ማኅተሞች ሲፈታ፣ መልካቸው የማይመሳሰል አራት ፈረሶችን አየ:: በኋላም በትርጉም እንደተረዳው እነርሱ ፍርድን፣ ጦርነትን፣ ረሀብንና ሞትን የያዙ ከመሆናቸውም በላይ፣ በምድር ላይ ይመጣ ዘንድ ያለውን ክፉ ነገር የሚያመለክቱ ናቸው:: የሚገርመው ነብዩ ዘካርያስ፣ ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት እነዚሁኑ የሚመሳሰሉ ፈረሶች በራእይ አይቶ የነበረ መሆኑ ነው::

ታዲያ በወቅቱ በምድር ከሚሆነው ኹከትና ሽብር የተነሣ ሰላም እጅግ ብርቅ ትሆናለች:: በዚያ ላይ አምስተኛውና ስድስተኛው ማኅተም ሲከፈት፣ የሰማዕታቱ ጩኸት መሰማቱና ታላላቅ የተፈጥሮ አደጋ መከሰቱ፣ በወቅቱ በምድር የሚሆነው ስቃይና ሰቆቃ ምን ያህል አሰቃቂ እንደ ሆነ የሚጠቀም ነው::[115]

ሰባተኛው ማኅተም ሲከፈት፣ ሰባት መለከቶች ከውስጡ ይወጣሉ፤ እነሱም ቀጥለው የሚመጡትን ሌሎች የጥፋት ዓይነቶች የሚጠቁሙ ናቸው:: ለዚሁ ተግባር የሚላኩት ሰባት መላእክትም መለከታቸውን መንፋት በጀመሩ ጊዜ አሰቃቂ ጥፋት በምድር ላይ ይሆናል:: ከዚህ አንጻር የመጀመሪያው መልአክ መለከቱን ሲነፋ፣ ደም የተቀላቀለበት እሳትና በረዶ ወደ ምድር ስለሚጣል፤ የምድር ሚሶ ይቃጠላል፤ የለመለመ ሳር ሁሉ በእሳት ይነዳል:: ሁለተኛው መለከት ሲነፋ በእሳት የሚቃጠል ትልቅ ተራራ የሚመስል ነገር፣ ወደ ምድር ይጣላል፤ የባሕርም ሚሶ ደም ይሆናል፤ በባሕር ውስጥ ከሚኖሩ ሕይወት ካላቸው ፍጥረቶች ሚሶው ይሞታሉ፤ ከመርከቦችም አንድ ሦስተኛው ይወድማሉ:: ሦስተኛው መልአክ መለከቱን ሲነፋ፣ እንደ ችቦ የሚቃጠል ታላቅ ኮከብ፣ በወንዞች ሚሶና በውኃ ምንጮች ላይ ከሰማይ ስለሚወድቅ፣ የውኃው አንድ ሦስተኛ መራራ ይሆናል፤ በመራራው ውኃ ጠንቅም ብዙዎች ይሞታሉ:: አራተኛው መልአክ መለከቱን ሲነፋ የፀሐይ፣ የጨረቃና የኮከቦች ሁሉ አንድ ሦስተኛ ይመታል፤ በመሆኑም የእነርሱ አንድ ሦስተኛ ይጨልማል፤ በዚህ ዓይነት የቀንና የሌሊት አንድ ሦስተኛና ያለ ብርሃን ይሆናሉ::[116]

ከዚህ በኋላ ዮሐንስ፣ አንድ ንስር በሰማይ መኻል ሲበር ተመለከተ:: ንስሩም በታላቅ ድምፅ እየጮኸ «የቀሩት ሦስት መላዕክት መለከት ሲነፉ ስለሚመጣው የመለከት ድምፅ በምድር ላይ ለሚኖሩ ሰዎች ወዮ ወዮላችሁ! ወዮ ወዮላችሁ!» ሲል ሰማ:: ይኼም ቀጥሎ በምድር ላይ የሚሆነው ነገር እጅግ የሚያስፈራ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው::

---

[115] ዘካ6:2፣3:: የመጀመሪያው መጋለ፣ ሁለተኛው ዳሪ፣ ሦስተኛው አምባላይ፣ አራተኛውም ዝጉርጉር ፈረሶች ነበሯቸው፤
[116] ራእይ ምዕ 8::

የዮሐንስ ራእይ፣ ዘጠነኛ ምዕራፍ፣ አምስተኛው መልአክ መለከቱን ሲነፋ በምድር የሚሆነውን ነገር በመናገር ይጀምራል። ዮሐንስ ከሁሉ አስቀድሞ ከሰማይ ወደ ምድር የሚወድቅ አንድ ኮከብ ያያል፤ ለኮከቡም የጥልቁ መክፈቻ ቁልፍ ተሰጠውና ከፈተው፤ ከጉድጓዱም እንደ ምድጃ እሳት ጢስ የሚመስል ወጣ፤ ከጉድጓዱ በሚወጣው ጢስ ምክንያት አየሩና ፀሐይ ይጨልማሉ። አንበጣዎችም ከጢሱ ውስጥ ወደ ምድር ይወጣሉ፤ እንደ ምድር ጊንጥ የሆነ ኃይልም ይኖራቸዋል። እነሱም በምድር የበቀለ ሣርና ቅጠልን ሳይሆን፣ በግንባራቸው ላይ የእግዚአብሔር ማኅተም የሌለባቸውን ሰዎች ነው የሚነዱት። ሆኖም ለአምስት ወር ለማሰቃየት እንጂ፣ የመግደል ሥልጣን አልተሰጣቸውም፤ የሚያደርሱት ጉዳት ግን፣ ሰው በጊንጥ ሲነድፍ እንደሚሰማው ዓይነት ነው። ከዚህ የተነሣ በእነዚያ ቀናት ሰዎች ሞትን ይፈልጋሉ፤ ነገር ግን ሞት ከእነርሱ ይሸሻል።[117]

አንበጣዎቹ ለጦርነት የተዘጋጁ ፈረሶች ይመስላሉ፤ ፊታቸው የሰው መልክ የሚመስል ሲሆን፣ የሴት ጠጉር የመሰለ ጠጉር አላቸው። ጥርሳቸው ከአንበሳ፣ የክንፎቻቸው ድምፅ ወደ ጦርነት ከሚሄዱ ከብዙ ፈረሶችና ከሠረገላዎች ድምፅ ጋር ይመሳሰላል። የብረት ጥሩር ለብሰዋል፤ እንደ ጊንጥ ጅራትና መንደፊያ አላቸው፤ ሰዎችን ለአምስት ወር የሚነዱበትን ኃይል የሚሸከሙት በጅራታቸው ነው። ንጉሥ ይኖራቸዋል፤ እርሱም የጥልቁ ጉድጓድ መልአክ ነው፤ ስሙም በዕብራይስጥ «አብዶን» በግሪክ «አጶሎን» የሚሰኝ ሲሆን፣ ትርጉሙም ደምሳሽ ማለት ነው። ይኸውም የመጀመሪያው «ወዮ» ነው፤ ደግሞም ሌላ «ወዮ» ገና ይመጣል።

ስድስተኛው መልአክ መለከቱን በሚነፋ ጊዜ እስከዚያ ቀን ድረስ በታላቁ የኤፍራጥስ ወንዝ ታስረው የቆዩ አራት መላዕክት እንዲፈቱ ትዕዛዝ ይሆናል፤ እነዚህ ለዚያ ሰዓትና ለዚያ ቀን የተዘጋጁት አራቱ መላዕክት የሰዎችን አንድ ሦስተኛ እንዲገድሉ ነው፣ የሚፈቱት፤ የፈረሰኞቹ ሠራዊት ብዛት ብቻ ሁለት መቶ ሚሊዮን ይሆናል።

[117] ራእ9:1-11።

ዮሐንስ በራእይ የተመለከታቸውን ነገሮች ሁሉ «እንዲህና እንዲያ ናቸው» ብሎ በእርግጠኝነት ለመናገር ከባድና አስቸጋሪ ነው። ሆኖም በራእይው የተጠቀሱ አንዳንድ ስዕላዊ መግለጫዎችን በዘመናችን ካለው ነባራዊ ሁኔታና ከመጽሐፍ ቅዱስ ሌሎች ክፍሎች ጋር በማነጻጸር ብንመረምር አንዳች መረዳት ሊያስገኝልን ይችላል የሚል አሳብ አለኝ። እንዲያ ከሆነ ደግሞ ለምን የተወሰኑ ትዕይንቶችን ምንነትንና ማንነት አብረን አንመረምርም? ምናልባት ለአንዳንድ ሰው የማያሳምን ትንታኔ መስሎ ይታይ ይሆናል፤ እኔ ግን ይህ አቋም ራሱ መልካም እንደ ሆነ ነው የማስበው፤ ምክንያቱም በእኔ አሳብ የማይስማማ፣ ቢያንስ ሊሆን ስለሚችለው ነገር ለመመርመር ዕድል ይሰጠዋል፤ የሚል እምነት ስላለኝ ነው።

በቅድሚያ፣ 5ኛው መለከት ሲነፋ ከሰማይ ወደ ምድር የወደቀውን ኮከብ ምንነት እንመርምር፤ በእርግጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኮከብና መላእክት ተያይዘው የተጠቀሱበት ስፍራ አለ። ለምሳሌ በኢዮብ መጽሐፍ ላይ በቀጥታ ለመላእክት ሲጠቀስ፣[118] በኢሳይያስ ትንቢት ደግሞ ለሰይጣን እንደተነገረ በሚታመነው ክፍል ተመሳሳይ አሳብ ይገኛል።[119] ከዚህ በተለየ በራእይ መጽሐፍ አስራ ሁለተኛ ምዕራፍ፣ ወደ ምድር እንደሚጣል የተተነበየለት ዘንዶው ወይም ዲያቢሎስ፣ አወዳደቁ በምዕራፍ ዘጠኝ ካለው ምልክት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ይታያል። እርግጥ ነው ዮሐንስ ሰይጣን ወደ ምድር እንደሚጣል በግልጥ የሚነግረን አስራ ሁለተኛው ምዕራፍ ላይ ነው፤ ነገር ግን በሁለቱ ምዕራፎች የታዩት ምልክቶች መመሳሰል፣ ዮሐንስ በራእይ ያየውን ነገር በጥቅልና በዝርዝር ከፋፍሎ፣ እንዲህ ገልጦት ይሆናል ብለን እንድናስብ ያደርገናል። ይሁን እንጂ ከሰማይ የወደቀው ኮከብ የጥልቁ ጉድጓድ መክፈቻ ወስዶ ጉድጓዱን በከፈተው ጊዜ የሚሆኑት ነገሮች እምብዛም ግልጥ ያልሆኑና ግራ የሚያጋቡ ናቸው። እናም ከዚህ በመነሣት አንዳንድ አሳቦችን በጥያቄነታቸው ብቻ ብንተዋቸው ጥሩ መስሎ ይታየኛል።

[118] ኢዮ38:7። . . . የንጋት ከዋክብት በዘመረቡበት ጊዜ፣መላእክትም ሁሉ ባሉበት ጊዜ...,
[119] ምንም እንኳ በዚህ ክፍል ያለው አሳብ ሰማን እንደተጠቀሰ አውዛጋቢ ቢሆንም . . .

ለመሆኑ፣ የወደቀው ከከብ፣[120] የጥልቁን ጉድጓድ ሲከፍት፣ ከውስጡ ከታላቅ እቶን እንደሚወጣ ያለ ጢስ መታየቱና ምድርን ማጨለሙ፣ በዚያ ዘመን ከመከራው ጽናት የተነሣ በምድር ላይ የሚሆነውን የጨለማ ጊዜ የሚያመለክት ይሆን? ወይስ ሌላ ሚስጥር ይኖረዋል? ከጢሱ የወጡት አጥፊ ፍጥረታትስ ተምሳሌትነታቸው፣ በወቅቱ ለሚሆነው አውዳሚ ጦርነት ይሆን? ደግሞስ፣ የለመለመ ተክልና ዛፍ ወደጎን ትተው፣ የእግዚአብሔር ማኅተም በግንባራቸው የሌለባቸውን ሰዎች ብቻ እንዲጎዱ የተፈቀደላቸው እነዚያ ፍጡራንስ ምን ይሆኑ? በእነዚያ ዘመናት በአጥፊው እንዳይጎዱ፣ እግዚአብሔር ለባሪያዎቹ ልዩ ጥበቃ የሚያደርገውስ እንዴት ነው? ከባድ ጥያቄ!

ከዚህ በተረፈ ዮሐንስ፣ በራእይው ውስጥ ለጦርነት የተዘጋጁ ፈረሶች የሚመስሉ አንበጦችን ማየቱ፣ ግራ የሚያጋባ ነገር ነው። ማንም ሰው በቀላሉ እንደሚረዳው፣ ፈረስ በመሬት፣ አንበጣ ደግሞ በአየር የሚበሩ ፍጥረታት ናቸው። ደግሞም ፈረስ ግዙፍ፣ አንበጣ ግን ትንሽ ፍጥረት ነው፤ በጥንት ዘመን ፈረስ ለጦርነት እጅግ የሚፈለግ ሲሆን፣ አንበጣ ግን ሰብል በማጥፋቱ ብቻ ነው የሚታወቀው። በመሆኑም እነዚህ ሁለት የተለያዩ ፍጥረታት ባሕርያቸው ሳይጣላና ሳይቃረን በአንድ ሆኖ ለዮሐንስ በራእይ የተገለጠበት ሁኔታ በጣም አስገራሚ ነው። ሆኖም ዮሐንስ፣ በዚያ ዘመን በአስገራሚ መልክ ያያቸው ፍጥረታት፣ በአሁኑ ጊዜ በሥራ ያሉትን አንዳንድ የቴክኖሎጂ ውጤቶች መስለው የሚታዩበት ሁኔታ አለ። ለምሳሌ ዮሐንስ፣ የፈረስን ጦረኝነት ከአንበጣ በራሪነት ጋር ቀላቅሎ ለመግለጥ የሞከረው ፍጡር *«ምናልባት በዘመኑ፣ አንድ ለመረዳት አስቸጋሪ የሆነ ፍጡር ታይቶት፣ አሱን እንዲህ ገልጦት ሊሆን ይችላል»* ብለን እንድናስብ ያደርገናል። ከዚህ አንጻር እነዚህ በፈረስና በአንበጣ ድብልቅ ተፈጥሮአዊ ባሕርይ ተመስለው የቀረቡት ፍጥረታት በአሁኑ ጊዜ በጥቅም የዋሉትን የጦር አውሮፕላኖችን ወይም ሔሊኮፕተሮችን የሚገልጡ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይጠረጠራል። ደግሞስ *«በራሳቸው ላይ*

[120] ኢሳ14፡12።አንተ የጎጋት ልጅ፣ አጥቢያ ከከብ ሆይ፣ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ! አንተ ቀድሞ መንግሥታትን ያዋረድህ፣ እንዴት ወደ ምድር ተጣልህ!

የወርቅ አክሊል የመሰለ ነገር ደፍተው አየኋቸው» ብሎ የገለጣቸው፣ የሔሊኮፕተሮቹን አናት ወይም አብራሪዎቹ በበረራ ወቅት በራሳቸው ላይ የሚደፉት ጥሩር ይሆን እንዴ? እንድንል ያደርገናል። እንደ ሴት ጠጉር መስሎ የሚታየው ነገርም፣ በሔሊኮፕተሮቹ አናት ላይ ካለው ተሽከርካሪ ክንፍ ጋር አንድ መስሎ ይታያል፤ «የአንበሳ ጥርስ ይመስላል» የተባለውም፣ በጉያቸው የያዟቸውን ሚሳይሎች፣ የብረት ጥሩሩም ሰውነታቸው የተለበጠበትን ብረት ለበስ አካል የሚገልጥ ሊሆን ይችላል።

ከዚህ ቀጥሎ ዮሐንስ፣ ድምፃቸው ወደ ጦርነት እንደሚገሰግስ እንደ ብዙ ፈረሶችና ሠረገላዎች ያለ ድምፅ ሰምቷል፤ ይኼም ድምፅ፣ ብዙ ሔሊኮፕተሮችና የጦር አውሮፕላኖች በአንድነት ሲጓዙ ከሚያሰሙት ጋር የሚመሳሰል ይመስላል። ከጅራታቸው ስር ያለውና ሰዎችን ለአምስት ወራት የሚያሰቃይበት ነገርም፣ ምናልባት በሚሳይሎቹ ውስጥ ያለውን የባዮሎጂካል ወይም የኬሚካል መርዝ፣ ወይም የሌላ ዓይነት የጦር መሣሪያ ንጥረ ነገር ባህርይ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል። በተለይም ሁኔታው ጊንጦች ሰዎችን ሲነድፉ ከሚሰማው ስሜት ጋር መያያዙ፣ ከላይ ከተጠቀሱት የጦር መሣሪያዎች ባህርይ ጋር እጅግ የሚመሳሰል ነገር አለው።

ሆኖም ይህ ሁሉ የመጀመሪያው «ወዮ» ነው። ደግሞም በአንጻራዊነት ሲታይ፣ ከዚያ በኋላ ከሚሆነው መከራ ይልቅ ቀላል የሚባል ነው። እናም የስድስተኛው መለከት መነፋት ተከትሎ የሚሆነው ሁለተኛው «ወዮ» በኤፍራጥስ ወንዝ ታስረው የቆዩ ክፉ መላእክት የሚፈቱበት በመሆኑ አሰቃቂነቱ ታላቅ ነው። በወቅቱ በሚሆነው ጦርነት ከምድር ሕዝብ አንድ ሦስተኛው የሚያልቅ መሆኑ በራሱ፣ ዘመኑ ምን ያህል አስጨናቂ እንደሚሆን ያመላክታል። እነዚህ ክፉ መላእክትም ቁጥሩ ከሁለት መቶ ሚሊዮን በላይ የሆነ ሠራዊት ከኤፍራጥስ[121] ወንዝ አካባቢ እንደሚያስከትቱ ይጠበቃል።

[121] ዘፍ15፡18። የአዬሬጥስ ወንዝ ኢራቅና ሶሪያን የመሳሰሉ አገራትን አቋርጦ የሚያልፍ ወንዝ ሲሆን፣ እግዚአብሔር ለአብርሃም በገባለት ተስፋ መሠረት የእስራኤል የገዛት ወሰን የተሰካው ከግብፅ ወንዝ አስከዚህ ወንዝ ድረስ ነው።

ከዚህ ባሻገር ግን ዮሐንስ በራእይው የተመለከታቸውንና የገለጣቸው ፍጡራን ምንነት ወይም ማንነት የማንንም ትኩረት የሚስቡ ናቸው። በመጀመሪያ በሚሆነው «ወዮ» በትዕይንቱ ሁነኛ ስፍራ የነበራቸው ፈረሶች ቀድሞ በተገለጡበት ሳይሆን መልክና ተግባራቸው ሌላ ሆኖ መገኘቱ አስገራሚ ነው። እስቲ ከዚህ በፊት እንዳደረግነው ይኼን ድንቅ ስዕላዊ መግለጫ፣ ካለንበት ዘመን ቴክኖሎጂ ጋር እያነጻጸርን እንመርምር።

በወቅቱ ዮሐንስ ያያቸው ፈረሶች፣ አፋቸው እንደ አንበሳ ሲመስል፣ ከውስጣቸው እሳት፣ ጢስና ዲን ይወጣ ነበር። ከአፋቸው በሚወጣው በእነዚህ ሦስት ነገሮች ማለትም በእሳቱ፣ በጢሱና በዲኑ ምክንያት አንድ ሦስተኛው የሰው ዘር ሲገደል እንዳየም ነግሮናል። በዚህ ላይ ጨምሮ ሲያስረዳ፣ የፈረሶቹ ኃይል በአፋቸውና በጅራታቸው ላይ ሆኖ ጅራታቸውም እባብ ይመስል እንደነበር ተናግሯል። አውዳሚ ጉዳት የሚያደርሱት በራሳቸው በኩል እንደሆነ ሳይጠቅስ አላለፈም። እኛም ሥራዬ ብለን ስለእነዚህ ምስሎችና ትዕይንቶች ስንመራመር በዘመናችን በጥቅም ከዋሉት አውዳሚ የረጅም ርቀት ተምዘግዛጊ ሚሳይሎች ጋር የሚመሳሰል ምስል እናገኛለን፣ በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ መንግሥታት እጅ የሚገኙት ሚሳይሎች በረቀቀ ቴክኖሎጂ የተሠሩ እንደመሆናቸው፣ ፍጥነት፣ ብቃትና አውዳሚነት አስደንጋጭ ነው። በዚህ ላይ ሚሳይሎቹ፣ የኑክሊየርም ይሁን ሌላ ዓይነት አውዳሚ አረራቸውን የሚያኖሩት «በራሳቸው» ወይም በአሞጠሞጠው የፊት ክፍላቸው መሆኑንና የሚወነጨፉትም ከጅራታቸው ላይ ባለ የሮኬት ኃይል እንደሆነ ያስተውሏል። በተጨማሪም ሚሳይሎቹ ዒላማቸውን ለማግኘት «በራሳቸው» ላይ በተገጠመላቸው «ኮምፒዩተራይዝድ» ጠቋሚ መሣሪያ የሚመሩ በመሆናቸው «ራሳቸው»[122] ወይም «አናታቸው» የሚያወድሙበት ብቻ ሳይሆን የሚያስቡበት ዋና የኃይላቸው መገኛ ነው። በዚሁ መሠረት ኃይላቸው «በአፋቸውና በጅራታቸው» ላይ ነው የመባሉ ሚስጥር፣ ይኼንኑ ለማመልከት ታስቦ ይመስላል።

[122] ራእ9:19። ራስም ስላሳቸው ጉዳት የሚያደርሱት በአርሱ ነበር።

ይህ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በመጨረሻው ዘመን በምድር፣ በሚሆነው ጦርነት የኑክሊየር፣ የአቶሚክ፣ የባዮሎጂካል፣ የኒትሮንና የኬሚካል የጦር መሣሪያዎች በጥቅም ላይ መዋላቸውን እንድንጠረጥር ግድ ይለናል። ደግሞስ እንዲያ ካልሆነ በምድር ከሚኖረው ሕዝብ፣ አንድ ሦስተኛውን በአንዴ እምሽክ የሚያደርግ ሌላ ምን ታምር ሊፈጠር ይችላል? ይህም በአሁኑ ጊዜ እንኳ ቢሰላ፣ ዓለም «አለኝ» ብላ ካስቀጠረችው ስድስት ቢሊየን ሕዝብ መኻል፣ ሁለት ቢሊየኑን ያህል መሆኑ አይደለምን? በእርግጥ በአሁኑ ወቅት የኑክሊየርና የአቶሚክ የጦር መሣሪያ የታጠቁ አገሮች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው። ምንም እንኳ በ2ኛው የዓለም ጦርነት መጨረሻ ሰዓት ዓለም የዚህን መሣሪያ ክፋትና አውዳሚነት፣ የአሜሪካ ቢ 52 አውሮላኖች በጃፓኖቹ የሂሮሽማና የናጋሳኪ ከተሞች በጣሏቸው ቦንቦች በኩል ውጤቱን ደጎና አድርጋ ያየች ብትሆንም፣ እስከ አሁን ከማምረትና ከማከማቸት አልታቀበችም። ይህ ብቻ ሳይሆን በ1940ዎቹ አጋማሽ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ አይታው የማጥፋት አቅሙን ያደነቀችለት ቦንብ፣ በዚህ ወቅት ካለው ጋር ሲነጻጸር፣ አውዳሚነቱ እዚህ ግባ የሚባል እንዳልሆነ ሁሉም ያውቀዋል። እንዲያውም በአሁኑ ጊዜ፣ የዓለምን አንድ ሦስተኛ ብቻ ሳይሆን፣ ሙሉ ለሙሉ ሊያወድም የሚችል ቦንብ በበርካታ አገሮች እጅ ይገኛል።

ስለዚሁ ጉዳይ በ1991 የአሜሪካ የኤታማዦር ሹም የነበሩት ሰው፣ በወቅቱ ከተከሰተው የኢራቅና የቀረው ዓለም ፍጥጫ አንጻር ሲናገሩ *«ሶቪየት ኅብረት አሜሪካንን ሙሉ ለሙሉ ለማውደም የሚያስፈልጋት ሠላሳ ደቂቃ ብቻ ነው»* ብለው እንደነበር ይጠቀሳል። በመሆኑም እስከ አሁን ዓለም ይኼ አውዳሚ የጦር መሣሪያ በጥቅም ላይ እንዳይውል የዘየዷችው ብልሃት፣ የኑክሊየር የጦር መሣሪያ ያላቸው አገሮች በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ የጸጥታው ምክር ቤት ውስጥ የቋሚ አባልነት ወንበር እንዲኖራቸው በማድረግ፣ ከእነርሱ በቀር ሌሎች አገሮች መሣሪያውን እንዳያመርቱ መቆጣጠር ነበር። ሆኖም በአሁኑ ጊዜ ከጸጥታው ምክር ቤት ቋሚ አባል አገሮች፣ ማለትም ከእንግሊዝ፣ ከአሜሪካ፣ ከሩሲያ፣ ከቻይናና ከፈረንሳይ፣ በተጨማሪ

ህንድና ፓኪስታን የመሣሪያው ባለቤት እንደ ሆኑ በይፋ ታውቋል። ከእነርሱ ሌላ እስራኤል፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ኢራንና ሰሜን ኮሪያን የመሳሰሉ ሌሎች አገሮች፣ በይፋ ባይናገሩም መሣሪያውን በእጃቸው እንዳስገቡት ስለሚጠረጠር፣ ሁኔታው ከማንም ቁጥጥር ውጪ እየሆነ ለመሄዱ አንዱ ማሳያ ተደርጎ ይጠቀሳል። ከዚህም ሌላ *«ሶቪዬት ኅብረት እንደ ቀልድ ስትፈራርስ፣ ከአንዳንድ የቀድሞ ግዛቶቿ መሣሪያው በአግባቡ ስላልተሰበሰበ ምናልባት በአንዳንድ አሸባሪዎች እጅ ገብቶ ይሆን?»* የሚለው ስጋት እስከ ዛሬ ብዙዎችን ያስበረግጋቸዋል። ምክንያቱም አንዳንዶቹ አውዳሚ መሣሪያዎች በቀላሉ፣ በትናንሽ ሳጥኖች እንኳ ሊጓጓዙ የሚችሉ ሆነው ስለተሠሩ ነው። እናም ዓለም፣ ዘመኑ ሲደርስ በጥቅም ልታውለው ያቆየችውና ራሷን በራስዋ ለማጥፋት ያሰናዳቻቸው የጥፋት መሣሪያዎችን ታቅፋ መኖር የጀመረችበትን ዓመት ካከበረች እነሆ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ሆነው። በእርግጥ ነገ ምን እንደሚሆን ከፈጣሪ በቀር ማንም የሚያውቅ የለም።

<u>ማሳሰቢያ፡</u> ከዚህ በላይ ከምስሎቹ በመነሣት የቀረቡት አስተያየቶች «ነገሩ እንዲህ ይሆን?» ከሚል ግምታዊ አስተያየት የመነጩ እንጂ፣ በእርግጠኛነት የምንናገራቸው አይደሉም። ከዚህ አንጻር አንባቢዎቼ ንጽጽሩን ሲያነቡ፣ እጅግ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አበክሬ አሳስባለሁ።

ሁለቱ ምስክሮች

123

በራእይው እኩሌታ፣ ዮሐንስ የሐዘን ልብስ ለብሰው ለአንድ ሺ ሁለት መቶ ስልሳ ቀን፣ ትንቢት የሚናገሩ ሁለት ሰዎችን አይቷል። እነርሱም በጌታ ፊት የሚቆሙ ሁለቱ የወይራ ዛፎች ወይም ሁለቱ ምስክሮች ናቸው፤ ማንም እነርሱን ሊጎዳ ቢፈልግ እሳት ከአፋቸው ወጥቶ ጠላቶቻቸውን ያቃጥላል፤ እነርሱን ሊጎዳ የሚፈልግ ሁሉ የሚሞተው በዚህ ዓይነት ነው። ትንቢት በሚናገሩባቸው በነዚያ ቀናት፣ ዝናብ እንዳይዘንብ ሰማይን የመዝጋት፣ ውኃዎችን ወደ ደም የመለወጥና በማንኛውም ዓይነት መቅሰፍት ምድርን የመምታት ሥልጣን አላቸው።

ምስክርነታቸውን ከጨረሱ በኋላ ግን ከጥልቁ ጉድጓድ የሚወጣው አውሬ ተዋግቶ ያሸንፋቸዋል፤ ይገድላቸውማል፤ ሬሳቸውም «ሰዶም» ወይም «ግብጽ» በምትባል በታላቂቷ ከተማ አደባባይ ይጋደማል፤ ይህች ከተማ የእነርሱ ጌታ የተሰቀለባት ናት። ከልዩ ልዩ ወገንና ነገድ፣ ከልዩ ልዩ ቋንቋና ሕዝብ የሆኑ የዓለም ሕዝቦች ለሦስት ቀን ተኩል ለሚያህል ጊዜ ሬሳቸውን እየተመለከቱ ይቆያሉ፤ ደግሞም ማንም ሬሳቸውን እንዳይቀብር ይከለክላል። ሁለቱ ነብያት የምድር ሰዎችን አስጨንቀው ነበርና፣ በምድር የሚኖሩ ሁሉ በነብያቱ ሞት እጅግ ደስ ይላቸዋል፤ በዓልም ያደርጋሉ፤ ስጦታም ይለዋወጣሉ። ነገር ግን ሦስት ቀን ተኩል ካለፈ በኋላ ሕይወትን የሚሰጥ እስትንፋስ ከእግዚአብሔር ዘንድ መጥቶ ወደ ሬሳዎቹ ይገባል፤ በሁለት እግራቸውም ቆመው ይታያሉ፤ በሚመለከቷቸውም ሰዎች ዘንድ ታላቅ ፍርሀት ይሆናል። ቀጥሎም ሁለቱ ነብያት ጠላቶቻቸው ሁሉ በግልጥ እየተመለከቱአቸው በደመና ወደሰማይ ሲወጡ፣ በዚያኑ ሰዓት በዓለም ላይ ታላቅ የምድር መናወጥ ይሆንና የከተማይቱ አንድ አስረኛ ያወድማል፤ ሰባት ሺ ሰዎችም ይሞታሉ፤ ከሞት

123 ራእ11:1-14።